የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ

የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት



# ጥናቶች ከያዕቆብ መልእክት ውስጥ

ቅጽ 100 ቁ. 4

መስከረም - ታህሳስ 2017 ዓ.ም.

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ

## የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት

# ጥናቶች ከያዕቆብ መልእክት ውስጥ

# ከመስከረም-ታህሳስ 2017

በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ተሐድሶ እንቅስቃሴ የጄነራል ኮንፍራንስ የሰንበት ትምህርት ክፍል በየሦስት ወሩ የሚታተምና በሪፎርሜሽን ሄራልድ የሕትመት ማህበር የሚሰራጭ ነው 5240 Hollins Road, Roanake-Virginia 24019-5048, U.S.APeriodical Postage Paid at Roanoke, Virginia 24022-999Website: www.sdarm.org
E-mail:info@sdarm.org

### 4ኛ ሩብ ዓመት

የሰንበት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ያለ አንዳች ተጨማሪ ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስና በትንቢት መንፈስ ላይ ፍጹም የየዕለት ጥናት ነው። ጥያቄዎቹም በተቻለ መጠን አጭርና ግልጽ እንዲሆኑ ታስበዋል። በአንዳንድ ምክንያቶች መሠረታዊ ሐሳቡ ግልጽ ሆኖ እንዲስተዋል ሲባል ቅንፎች እንዲገቡ ተደርጓል። ጠለቅ ላለ ጥናት ከመሠረታዊ ምንጮች መረጃዎችን መጠቀም በጥብቅ ይመከራል።

# የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች
# የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት
# ጥናቶች ከያዕቆብ መልእክት ውስጥ
# ከመስከረም-ታህሳስ 2017

## ይዘቶች


1. የእግዚአብሔር መልእክት በያዕቆብ ............... 5
2. የመቋቋሚያ ጥበብ ................................. 10
3. ፈተናን መጋፈጥ ................................... 15
4. እምነትን በተግባር ማዋል ......................... 20
5. አድልኦን ማሸነፍ .................................. 26
6. እምነት በተግባር ................................... 31
7. አንደበታችንን ከመክፈታችን በፊት መጸለይ 36
8. ስለ ምን ማሰብ እንዳለብን መምረጥ .......... 41
9. የየዋህነት ጥበብ ....................................... 46
10. የአመለካከት ችግሮችን ማሸነፍ ............... 52
11. ትሑት አይታን መቀበል ........................ 57
12. በመንግሥተ ሰማያት ላይ ማተኮር ........... 62
13. በእምነት መጽናት ................................ 67

# መቅድም

የያዕቆብ መልእክት ቀጥተኛ ነው። በውስጡ ያሉትን መልእክቶች ምን ያህል አስፈላጊ ናቸውን! ስለዚህ፣ ለሚቀጥሉት ሶስት ወራት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የያዕቆብ መልእክት ያጠናሉ። በዚህ ጥናት ስለአንደበት (በጥሩም ሆነ በክፉ)፣ በእምነት ለእግዚአብሔር ስለመታዘዝ፣ የጸሎት ሃይል እና ከኤልያስ ምሳሌ የሚገኙ ጠቃሚ ነጥቦች ጥቂቶቹ ቁልፍ ርዕሶች ናቸው። ዛሬ ይህ ሁሉ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?

“የዚህ ዘመን ኃጢአት የእግዚአብሔርን ግልጽ ትእዛዛት ችላ ማለት ነው። ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ የሚመራ ኃይል በጣም ትልቅ ነው።”—Testimonies for the Church, vol. 3, p. 483.

ሆን ብለው የአምላክን መርሆች እየጣሱ ቅዱሳን ሊሆኑ እንደሚችሉ በማመን ራሳቸውን አያታልሉ። የታወቀውን ኃጢአት መደበቅ የመንፈስን የምሥክርነት ድምጽ ጸጥ ያደርገዋል እና ነፍስን ከእግዚአብሔር ይለያል። ‘ኃጢአት ሕግን መተላለፍ ነው።’ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውምም። 1ኛ ዮሃንስ 3:16።”—The Great Controversy, p. 472.

“ዛሬ የከባድ ተግሣጽ ድምፅ ያስፈልጋል። ሕዝቡን ከእግዚአብሔር የለዩአቸው ከባድ ኃጢአቶች ናቸውና። ክህደት በፍጥነት ፋሽን እየሆነ ነው። ‘ይህ ሰው በላያችን እንዲነግሥ አንፈልግም’ የሚለው የሺህዎች ቋንቋ ነው። ሉቃስ 19፡ 14 ብዙውን ጊዜ የሚሰበኩት ለስላሳ ስብከቶች ዘላቂ ስሜት አይፈጥርም፤ መለከት ቁርጥ ያል ድምጽ እየሰጠ አይደለም። ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ግልጽ በሆነ፣ ስለታም እውነት በልባቸው አልተቀረጡም።

“እውነተኛ ስሜታቸውን እንድገልጹ ቢጠየቁ ብዙ ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች፣ እንዲህ በግልጽ መናገር ምን ያስፈልጋል? ይሉ ይሆናል። እንዲሁም መጥምቁ ዮሐንስ ለፈሪሳውያን፡- እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ ከሚመጣው ቊጣ እንድትሸሹ ማን አስጠነቀቃችሁ? ሉቃስ 3፡7 ሄሮድስን ከወንድሙ ሚስት ጋር መኖር ክልክል እንደሆነ በመንገር የሄሮድያዳ ቁጣን ማስንሳትስ ለምን አስፈለገ? የክርስቶስን መንገድ ጠራጊ የሆነው በግልፅ በመናገሩ ህይወቱን አጥቷል። በኃጢአት ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ሳያስከፋቸው አብሮ መሄድ ያልቻለው ለምንድን ነው?

“ስለዚህ የአምላክ ሕግ ታማኝ ጠባቂዎች ሆነው መቆም ያለባቸው ሰዎች ፖሊሲ ታማኝነት እስኪተካ ድረስ፣ ኃጢአትም ሳይቀጣ እንዲቀር እስኪፈቀድ ድረስ ለምን ዝም ይላሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የታማኞች ተግሣጽ ድምፅ የሚሰማው መቼ ነው?”—Prophets and Kings, pp. 140, 141.

እንዲያውቁ ፣ ክርስቲያናዊ ጠባይ እንዲኖራቸውና በእውነት እንዲነጹ በቂ ዝግጅት ተደርጎላቸዋል።”—Testimonies for the Church, vol. 2, p. 644.

በእርግጥም የአምላክን እርዳታ እንፈልጋለን፤ እንዲሁም “ለማንኛውም በእምነት ለሚጸልዩት ጸሎት ሁሉ መልስ እንደሚሰጥ በግልጽ እርግጠኞች ነን። መልሶቹ እኛ እንደጠበቅነው ላይመጡ ይችላሉ፤ እነሱ የሚመጡት ምናልባት እንዳሰብነው ሳይሆን በጣም በምንፈልጋቸው ጊዜ ነው።”—Ibid., vol. 3, p. 209. አሜን!

የአጠቃላይ ኮንፈረንስ ሰንበት ትምህርት መምሪያ

**መስከረም 25፣ 2017**

# የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ በረድንግ፣ ፔንስልቬንያ፣ ዩኤስኤ ውስጥ ለሚገኝ የጸሎት ቤት መሥሪያ ይዉላል

*የምስራቅ ዩናይትድ ስቴትስ ፊልድ* (EUSF) *ከፔንስልቬንያ፣ ኒው ዮርክ፣ ኮነክቲከት፣ ሮድ አይላንድ፣ ማሳቹሴትስ፣ ሜይን፣ ቨርሞንት፣ ኒው ሃምፕሻየር ግዛቶችን ያቀፈ በስምንት መልክዓ ምድራዊ አካባቢዎች የተከፋፈለ ነው። በፔንስልቬንያ ያለው ሥራ በአሁኑ ጊዜ ፈጣን እድገት እያሳየ ነው።*

*በዚህ ግዛት ውስጥ ከ* 53% *በላይ የሚሆኑ ሰዎች ሃይማኖተኛ እንደሆኑ ይገመታል - ሜቶዲስቶች ፣ ሉተራኖች ፣ ባፕቲስቶች፣ ጴንጤቆስጤዎች እና ሌሎችም ያቀፈ ሲሆን* 28.3% *ካቶሊኮች። በቅኝ ግዛት ዘመን መጀመሪያ ፔንስልቬንያ በአውሮፓ ከሚደርስባቸው ስደት ለማምለጥ የሃይማኖት ነፃነት ለሚፈልጉ ምዕመናን መሸሸጊያ ቦታ ነበረች። ይህ ታሪክ አሁንም በላንካስተር አውራጃ ውስጥ በሚገኙ ትላልቅ የአርሶ አደር ማህበረሰቦች ውስጥ ጨዋ የሆነ አለባበስ ለብሰው፣ በፈረስና በቡጊ ጋሪ እየተጓዙ በሚኖሩ በርካታ ባህላዊ የአሚሽ አማኞች ምስክር ናቸዉ።*

*ባለፉት አመታት፣ ጥቂት* SDARM *አባላት በፔንስልቬንያ ኖረዋል እናም እዚህም የሚስዮናዊ ስልጠና ተሰጥቷል። ነገር ግን የወቅቱ እውነት ፍላጎት መነቃቃት የጀመረው በ*2016 *በረድንግ ከተማ ሁለት አባላት ከኒውዮርክ ሄደዉ መስራት ከጀመሩ በኋላ ነው። ቁጥራቸዉ እየጨመረ በመሄድበ በጋ ወቅት በየሰንበት ቀን ከሰአት በኋላ በአንድ መናፈሻ ውስጥ በመሰብሰብና በክረምት በአንድት እህት ቤት ውስጥ መሰብሰብ ተጀመረ። ከብዙ ወራት ጥናት በኋላ ብዙዎች በተሃድሶ እምነት ተጠመቁ።*

*ረድንግ* ከ95,000 *በላይ ህዝብ ያለው አከባቢ ሲሆን የኤሌክትሮኒክስ መለዋወጫዎች፣ የህክምና መሳሪያዎች፣ የሃይል ማከማቻ ቴክኖሎጂዎችና ሌሎችም ቁሶች የማምረቻ ማዕከል ነው። እዚህ ያለው ቤተክርስቲያናችን አሁን በምስራቅ ዩኤስ መስክ ውስጥ ትልቁ ነዉ። ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ለመቀላቀል ተጨማሪ አዳዲስ ነፍሳት እየተዘጋጁ ነው። በአሁኑ ጊዜ፣ በተከራየነው ተቋም ውስጥ እናመልካለን እናም መገኘታችንን ማረጋገጥና ለበለጠ አገልግሎት ማስፋት እንፈልጋለን። "የምእመናን ማኅበር ባለበት ቦታ ሁሉ የአምልኮ ቤት መገንባት አለበት። . . . መልእክቱ በተሰበከባቸውና ነፍሳት መልዕክቱን በተቀበሉባቸው ብዙ ቦታዎች፣ በማይመች ሁኔታዎች ውስጥ ናቸው፣ በዚህም ለሥራዉ የሚሆኑ ጥቅሞችን ለማግኘት ምንም ማድረግ አይችሉም። ብዙውን ጊዜ ይህ ሥራውን ወደፊት ለማስኬድ አስቸጋሪ ያደርገዋል።"*—Evangelism, p. 376.

*በአካባቢዉ የአምልኮ ቤት እንድንሰራ፣ ብዙ ነፍሳት ወደ መንጋው እንዲገቡ እንዲረዱን እንጠይቃለን። ስለቸር ልግስናዎ በጣም እናመሰግናለን፣ ጌታ በበረከቱ ይባርካችሁ።*

*ወንድሞቻችሁ ከምስራቃዊ ዩናይትድ ስቴትስ ፊልድ*

## የእግዚአብሔር መልእክት በያዕቆብ በኩል

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “የእግዚአብሔርና የጌታ የየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ ለተበተኑ ለአሥራ ሁለቱ ወገኖች፤ ሰላም ለእናንተ ይሁን።” ያዕቆብ 1፡1**

*በእያንዳንዱ ልማድና አስተሳሰብ ፍጹም የሆነ ሰው ወይም ሕዝብ የለም። አንዱ ስለሌላው መማር አለበት። ስለዚህ እግዚአብሔር የተለያዩ ብሔረሰቦች እንዲቀላቀሉ፣ በፍርድ አንድ እንዲሆኑ፣ በዓላማም አንድ እንዲሆኑ ይፈልጋል። በዚያም በክርስቶስ ውስጥ ያለው አንድነት በምሳሌነት ይገለጻል።”*—Testimonies for the Church, vol. 9, pp. 180, 181.

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ**፡ Testimonies for the Church, **vol. 9, pp. 190–203.**

እሁድ **መስከረም 19**

### 1. የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት

**ሀ. ከክርስቶስ ጋር የተቆራኙት “ያዕቆብ” የተባሉት ሦስቱ ሰዎች እነማን ነበሩ? ብዙውን ጊዜ የምናስተውለው የትኛውን ነው? ማቴዎስ 10:2፣ 3፤ 13፡55።**

**ለ. የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ ከየሱስ ጋር ያሳለፉትን አንዳንድ ልዩ ጊዜዎች ጥቀስ። ሉቃስ 8:51-55፤ ማቴዎስ 17:1፣ 2፤ ማርቆስ 14:32-34**

*“የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ ክርስቶስን ከተከተሉት የመጀመሪያ ሁለት ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር። እርሱና ወንድሙ ያዕቆብ ሁሉን ነገር ትተው ክርስቶስን ለማገልገል ከተከተሉት ከመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሐዋርያት መካከል ነበሩ። እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች ከየሱስ ጋር ለመሆን ሲሉ ያለ አንዳች ቅሬታ ቤታቸውንና ወዳጆቻቸውን ሁሉ ትተዋል፣ ከእርሱ ጋር ተጉዘዋል፣ ተጫውተዋልም፣ እንደዚሁም በግል ቤትና በአደባባይ ከእርሱ ጋር ተገኝተዋል። የሱስም ልባቸው ከእርሱ ልብ ጋር እስኪጣመር ድረስ ፍርሃታቸውን አስወገደላቸው፣ ከአደጋ አዳናቸው፣ ሥቃያቸውን አስወገደላቸው፣ ባዘኑ ጊዜ አጽናናቸው፣ በትእግሥትና በርህራሄም አስተማራቸው። እነርሱም ለእርሱ በነበራቸው የጋለ ፍቅር በመንግሥቱ ወደ እርሱ ተጠግተው የመቀመጥ ፍላጐት አደረባቸው።”*—The Desire of Ages, p. 548.

*“ከአትክልቱ ቦታ መግቢያ ሲደርሱ የሱስ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ሶስቱን አስከትሎ ሲገባ የቀሩትን ለእርሱና ለራሳቸው እንዲጸልዩ አዘዛቸው። የሱስ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ይዞ በአትክልቱ ውስጥ ወደሚገኝ ልዩ ቦታ ገባ። እነዚህ ሶስቱ ደቀ መዛሙርት የየሱስ የቅርብ ጓደኞች ነበሩ። እነዚህ ሶስቱ የሱስ በተለወጠበት ተራራ ላይ ክብሩን አይተዋል፣ ሙሴና ኤልያስ የሱስን ሲያነጋግሩት ተመልክተዋል፣ ከሰማይ የወረደውን ድምጽም ሰምተዋል፣ አሁን ደግሞ በዚህ ታላቅ የትግል ወቅት የሱስ በአጠገቡ እንዲሆኑለት ፈለገ።”*—Ibid., p. 686.

## 2. ዋንጫውን (ጽዋዉን) መጠጣት

### ሀ. የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ የነበራቸውን ዋና ዓላማቸዉን ግለጽ። ማርቆስ 10፡35-38

*"አጋጣሚዉን ባገኘ ቁጥር ሁሉ ከአዳኙ ቀጥሎ ባለ ቦታ ላይ ይቀመጥ ነበር፣ እንዲሁም ያዕቆብም ከእርሱ ጋር ባለው የቅርብ ግንኙነት መከበርን ይፈልግ ነበር።*

*"እናታቸው የክርስቶስ ተከታይ ነበረች፣ እንዲሁም በነጻ ታገለግለው ነበር። እናት ለልጆቿ ባላት ፍቅር እና ምኞት በአዲሱ መንግሥት ውስጥ እጅግ የተከበረ ቦታን ትመኛላቸው ነበር። ለዚህም እንዲጠይቁ አበረታታቻቸው።*

*"እናትና ልጆቿ በአንድነት ወደ የሱስ መጡ፣ በልባቸው ያደረጉን መሻት እንዲሰጣቸው ጠየቁት።*

*ምን ላደርግላችሁ ትወዳላችሁ? ሲል ጠየቀ የሱስ።*

*"እናቲቱም መለሰች፡- እነዚህ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ ሌላውም በግራ በመንግሥትህ እንዲቀመጡ ስጣቸው።*

*"በልባቸው ውስጥ የነበረውን ስሜት ስላነበበ ስለ እርሱ የነበራቸውን የፍቅር ጥልቀት አወቀ። ምንም እንኳን ሰብአዊ ፍጡራን በመሆናቸው ምክንያት በዓለማዊነት ቢጉድፍም ለእርሱ የነበራቸው ፍቅር ከራሱ ከየሱስ ከአዳኝነት ፍቅሩ የፈለቀ እንጂ ተራ ሰብአዊ ፍቅር አልነበረም። ስለዚህ የሱስ ይህን ዓይነት ፍቅር ጥልቀት ያለውና የጠራ እንዲሆን ያደርገዋል እንጂ በመገሰጽ አያቀዘቅዘውም። «እኔ የምጠጣውን (የመከራ) ጽዋ መጠጣት ትችላላችሁን? እኔስ የምጠመቀውን ጥምቀት መጠመቅ ትችላላችሁን? » ሲል የሱስ ጠየቃቸው። ስለ ፈተናና ስቃይ የተናገራቸው ምስጢራዊ ቃላት ትዝ ቢላቸውም በልበ ሙሉነት «አዎ፣ እንችላለን» አሉ። በጌታቸው ላይ የሚደርስበትን ሁሉ በመካፈል ታማኝነታቸውን መግለጽ እንደ ከፍተኛ ክብር የሚቆጥሩት ነገር ነበር።*

*በፊቱ በዙፋን ፈንታ መስቀልና ሁለት ወንጀለኞች አንዱ በቀኙ፣ ሌላው በግራው ሲሰቀሉ እየታየው «በእርግጥ እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ? እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ትጠመቃላችሁ?» አላቸው።"*—The Desire of Ages, pp. 548, 549.

### ለ. ልክ ክርስቶስ አስቀድሞ እንደተናገረው፣ ከጌታ ዕርገት በኋላ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ ምን ሆነው ነበር? ሥራ 12:1፣ 2፤ ራእይ 1፡9።

*"ዮሐንስና ያዕቆብ ከመምህራቸው ጋር መከራን መቀበል ነበረባቸው። አንዱ ከወንድሞች መካከል አስቀድሞ በሰይፍ ሲጠፋ ሌላው፣ ድካምን፣ ነቀፋንና ስደትን በጽናት በመቀበል ከሁሉ የበለጠ ረጅም ዕድሜ ኖረ።"*—Ibid., 549.

**3. ደብዳቤውን የጻፈው ማን ነው?**

### ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነውን የእልፍዮስን ልጅ ያዕቆብን (የዮሐንስን ወንድም ዘብዴዎስ ልጅ ያልሆነዉን) እንዴት ይገልጸዋል? ማርቆስ 15:40

*"እንደሌዋዊው ማቴዎስ የመሰሉ ቀራጮች የሆኑም ነበሩበት። ከተራ ሥራ የተጠሩ የሮማ አገልጋይ የነበሩ ናቸው። ቀናተኛው ሲሞን ጠላቶቹ ከነበሩት ንጉሣዊያን ባለሥልጣኖች ጋር ድርድር የማይወደውና ለራሱ የሚበቃውን ብቻ የሚያስበው የጋለ ልብ የነበረው ጴጥሮስ ከወንድሙ ከእንደርያስ ጋር፤ ሽሙንሙን፣ ትልቅ ችሎታ ያለው ግን ደካማ መንፈስ የነበረው ይሁዳዊዉ ይሁዳ፤ ፊሊጶስና ቶማስ ደግሞ ታማኝና ቀና ሲሆኑ ነገር ግን ለማመን ዳተኛ ልብ ያላቸው ነበሩ። ያዕቆብና ይሁዳ ወንድሞች መካከል ታናሾቹ ነበሩ፤ ነገር ግን የኃይልና የቀልጣፋ አስተሳሰብ ባለቤቶች ነበሩ። በእምነት ገና ልጅ የሆነዉ የዚያ ጥል የሚወደው የዘብዴዎስ ልጅ ናትናኤል ነበሩ።"*—Education, pp. 85, 86.

### ለ. ለምን ምናልባት የያዕቆብ መልእክት ጸሐፊ (ሐዋርያ ተብሎ የሚጠራው ጌታን በአካል ስለሚያውቅ ነው) የክርስቶስ ግማሽ ወንድም ሊሆን ይችላል - እና ስለ ራሱ በሰጠው መግለጫ ባህሪው በባህሪው በጌታ ተጽእኖ እንደተለወጠ የሚያሳየው እንዴት ነው? ያዕቆብ 1፡1 (የመጀመሪያ አጋማሽ)።

*"የክርስቶስ ወንድሞች እርሱን በስህተት ተረድተዉታል፤ እርሱ እንደ እነርሱ አልነበረምና። ስቃይ ላይ ያሉትን ባየ ቁጥር ሁሉ ስቃያቸዉን ለማስታገስ ሠርቷል፣ በዚህም ሁልጊዜም ስኬታማ ነበር። ለመስጠት ትንሽ ገንዘብ ነበረው ነገር ግን ከራሱ የበለጠ ችግረኛ ለሚመስሉት በትህትና የራሱን ምግብ ይሰጥ ነበር። ወንድሞቹ የእሱን ተጽእኖ ለመቋቋም ከሚቻለዉ በላይ በጣም አልፎ እንደሄደ ይሰማቸዉ ነበር፤ ምክንያቱም እነሱ ከድሆች ጋር በተገናኙት ቁጥር ለነዚያ ምስክን ነፍሳት ሸካራ ቃላትን ሲናገሩ፣ ክርስቶስ ግን እነዚህን ፈልጎ የሚያበረታታ ቃል ይነግሯቸዉ ነበር። በቤተሰብ ክበብ ውስጥ እያለ ከዚያ በላይ ማድረግ ባይችል እንኳን በተቻለ መጠን በጸጥታና በድብቅ እርዳታው ለሚያስፈልጋቸው ምስኪኖች ቀዝቃዛ ውሃ ይሰጣቸውና ከዚያም የራሱን ምግብ በእጃቸው ያስቀምጣላቸዉ ነበር።* —This Day With God, p. 59.

### ሐ. ጳውሎስ ለየሱስ ወንድም ለያዕቆብ ያለውን አክብሮት ያሳየው እንዴት ነው? ገላትያ 1:17–19፤ የሐዋርያት ሥራ 21:18

## 4. አንዳንድ ጉዳዮችን ማብራራት

### ሀ. የክርስቶስ ወንድም የሆነው ያዕቆብ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ትልቅ ጉባኤ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ሰው እንደነበር የሚያሳየው ምንድን ነው? የሐዋርያት ሥራ 15:5፣ 6፣ 13፣ 19፣ 20

"በዚህ አጋጣሚ ያዕቀብ በምክር ቤቱ የደረሰውን ውሳኔ የሚያበስር ሆኖ የተመረጠ ይመስላል። ሜዳዊዉ ሕግ፣ በተለይም የግርዛት ሥርዓት፣ በአሕዛብ ላይ እንዳይበረታ፣ ወይም ለእነርሱ እንደ ግዴታ ባይመከር መልካም ነው የሚለዉ የእርሱ ዉሳኔ ነበር። ያዕቀብ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ አሕዛብ በሕይወታቸው ውስጥ ትልቅ ለውጥ እንዳደረጉና ግራ የሚያጋቡና ጥቃቅን በሆኑ ጥቃቅን ጥያቄዎች በማስቸገር ክርስቶስን በመከተል ተስፋ እንዲቆርጡ እንዳያደርጓቸው ብዙ መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ በማሳሰብ የወንድሞቹን አእምሮ ለመማረክ ፈለገ።"—The Acts of the Apostles, p. 195.

### ለ. በዚህ ጠቃሚ የምክር ቤት ዉሎ ውስጥ ያዕቆብ ትልቅ ሚና በመጫወቱ ምክንያት ውድቅ የሆነው የተሳሳተ የይገባኛል ጥያቄ ምንድነዉ? ማቴዎስ 16፡18

"ያዕቀብ ጉባኤውን ይመራ ነበር፣ እና የመጨረሻ ውሳኔው፣ 'ስለዚህ ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን እንዳናስቸግራቸው ፍርዴ ይህ ነው።'

"ይህ የውይይቱ ማጠቃለያ ነበር። በዚህ ምሳሌ በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነበር የሚለውን አስተምህሮ ውድቅ እናደርጋለን። እንደ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ተተኪዎች ነን የሚሉ ሰዎች ለማጣቀስ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም። በጴጥሮስ ሕይወት ውስጥ እርሱ የልዑል ምክትል ሊቀ መንበር ሆኖ ከወንድሞቹ በላይ ከፍ ከፍ አለ ለሚለው አባባል ምንም ማረጋገጫ መስጠት አይችሉም። የጴጥሮስ ተተኪዎች እንደሆኑ የተገለጹት ሰዎች የእሱን ምሳሌ ቢከተሉ ኖሮ ምንጊዜም ቢሆን ከወንድሞቻቸው ጋር በእኩልነት ለመኖር ረክተው ይኖሩ ነበር።"—Ibid., pp. 194, 195.

"አዳኛችን የወንጌልን ሥራ ለጴጥሮስ ለብቻው አልሰጠውም። ለጴጥሮስ የተናገራቸውን ቃላት ቀይቶ በሌላ ጊዜ በቀጥታ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ተናግሮአቸዋል። ይህንኑ ሐሳብ የያዘ ንግግር ምዕመናንን እንደሚወክሉ አድርጐ ለአሥራ ሁለቱም መዛሙርቱ ለአንዱ የተለየ ሥልጣን ሰጥቶ ከመካከላቸው ትልቁ ማን እንደሆነ ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር። የሱስ ከደቀ ቢሆን ኖሮ ደቀ መዛሙርቱ ሲከራከሩ ባልታዩም ነበር። በዚህ ፈንታ የጌታቸውን ፍላጐት በመቀበል እርሱ የመረጠውን ሰው ያከብሩት ነበር።"—The Desire of Ages, p. 414.

ሐሙስ **መስከረም 23**

## 5. የእግዚአብሔር እስራኤል

### ሀ. ይህ መልእክት የተጻፈው ለማን ነው—የሱስን እንደ ጌታ የሚቀበሉትን ሁሉ የሚያጠቃልለውስ እንዴት ነው? ያዕቆብ 1:1 (ሁለተኛ አጋማሽ)፤ ገላትያ 3፡27-29

"*ከእግዚአብሔር እስራኤል መካከል በሥጋ የአብርሃም ዘሮች ያልሆኑ ብዙዎች ይቈጠራሉ።*"—Prophets and Kings, p. 367. "*የክርስቶስ ሕይወት፣ የዘር መድሎ የሌለበትን ሃይማኖት፣ አይሁዳዊና አሕዛብ፣ ጌታና አሽከር፣ በአንድ ወንድማማችነት የሚተሳሰሩበትና በእግዚአብሔር ፊት እኩል የሆኑበትን ሃይማኖት አቋቋመ።*"—Testimonies for the Church, vol. 9, p. 191.

"*ክርስትና በጌታና በአገልጋይ፣ በንጉሥና በተገዢው፣ በወንጌል አገልጋይ እና በክርስቶስ ከኃጢአት መንጻትን ባገኘው የበዋረደዉ ኃጢአተኛ መካከል ጠንካራ አንድነት ይፈጥራል።*"—The Acts of the Apostles, p. 460.

### ለ. በትንቢቱ ላይ የመጨረሻዎቹ መንፈሳዊ እስራኤላውያን ምን ስም ተሰጥቷቸዋል? ከክርስቶስ መምጣት በፊት የሚያጋጠማቸው ነገርስ እንዴት ተገልጿል? ራእይ 7፡4።

"*ብዙም ሳይቆይ የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደ ብዙ ውሃ ሰማን፣ በዚህም የየሱስን መምጫ ቀንና ሰዓቱ ተነገረን። ሕያዋን ቅዱሳን ቁጥራቸው* 144,000 *ያህሉ ድምፁን አውቀው ተረድተውታል፤ ክፉዎች ግን ነጎድጓድና የመሬት መንቀጥቀጥ መሰሏቸው ነበር።* . . .

"144,000*ዎቹ ሁሉም የታተሙና ፍጹም አንድንድነት አላቸዉ። በግንባራቸው ላይ አምላክ፣ አዲሲቱ የሩሳሌም፣ የሚሉት ቃላትና የየሱስን አዲስ ስም የያዘ የከበረ ኮከብ ነበሩ። ደስተኛ፣ ቅዱስ በሆነው ሁኔታችን ክፉዎች ተናደዱ፣ ወደ እስር ቤትም ሊያስገቡን በኃይል ይጣደፉ ነበር፣ ነገር ግን በጌታ ስም እጃችንን ስንዘረጋ አቅመ ደካሞች ሆነዉ በምድር ላይ ይወድቃሉ። ከዚያም የሰይጣን ማኅበር አምላክ እንደወደደን፣ እንዲሁም እርስ በርሳችን እግራችንን መታጠብና ወንድሞችን በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ መስጠት የምችል መሆናችንን ሲያዉቁ በእግራችን ሥር ወድቀዉ ሰገዱ።*"— Testimonies for the Church, vol. 1, p. 59.

አርብ **መስከረም 24**

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. *የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብ ክርስቶስን ወደ መምሰል ያደገው እንዴት ነው?*
2. *የየሱስ ወንድም የሆነው ያዕቆብ ክርስቶስን ወደ መምሰል ያደገው እንዴት ነው?*
3. *ጴጥሮስ የሐዋርያት ራስ እንዳልሆነ የሚያሳዩት የትኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ናቸው?*
4. *ጳውሎስ የሁሉም ክርስቲያኖች አንድነትና እኩል ጥቅም የገለጸው እንዴት ነው?*
5. *የአምላክ መንፈሳዊ እስራኤል የመጨረሻውን ድል የሚያሳየው ምንድን ነው?*

# የመቋቋም ጥበብ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል።" (ያዕቆብ 1፡5)።**

"እግዚአብሔር ቅርብ ነውና ጥበብን ፍለጋ ወደ ምድር ዳርቻዎች መሄድ አያስፈልግም። ስኬትን የሚሰጣችሁ አሁን ያላችሁ ወይም የሚኖራችሁ ችሎታዎች አይደሉም። ጌታ ለእናንተ ሊያደርግ የሚፈልገው ይህ ነው። . . . በጊዜአዊ (በሥጋዊ) እና በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ማስተዋልን ሊሰጣችሁ ይናፍቃል። እሱ የማሰብ ችሎታችሁን ማጎልበት ይችላል። ብርታትና ብልሃትን መስጠት ይችላል። መክሊትህን በሥራ ላይ አውል፣ ጥበብ እንዲሰጥህ አምላክን ጠይቅ፣ እሱም ይሰጣሃል።"—Christ's Object Lessons, p. 146.

**ለንባብ የተመረጡት መጽሐፍት፡** Testimonies for the Church, **vol. 1, pp. 120, 121; vol. 2, pp. 232–235.**

እሁድ **መስከረም 26**

## 1. ጥበብን ለማግኘት መጸለይ

### ሀ. በሕይወታችን ውስጥ ከሰበአዊ ጥበብ በላይ የምንፈልገው ለምንድን ነው? እንዴትስ ማግኘት ይቻላል? ያእቆብ 1:5

"ሰው ማድረግ በሚችለው ነገር ላይ መተማመን በመተዉ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ነፍስ ሊያደርግ በሚችለው ነገር ላይ የበለጠ መተማመን አለብን። እርሱ ከኋላዉ በእምነት እንድትከተል ይፈልጋልና። ከእርሱ ታላቅ ነገርን ለማግኘት እንድትጠብቅ ይናፍቃል።"—Christ's Object Lessons, p. 146

"በየሰንበት ቀኑ ስብከቶችን መስማት ብቻ፣ መጽሐፍ ቅዱስን እየገለጥን ማንበብ፣ ወይም በቁጥር በቁጥር ማብራሪያ መስጠታችን ብቻ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ወደ ግል ልምዳችን ካላመጣን በስተቀር ለእኛም ሆነ ለሚሰሙን አይጠቅምም። ማስተዋላችን፣ ፈቃዳችን፣ ፍቅራችን፣ ለእግዚአብሔር ቃል ቁጥጥር መስጠት አለበት። ያኔ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የቃሉ ሕግጋቶች የሕይወት መርሆዎችን ይሆናሉ።

"ጌታ እንዲረዳህ ስትለምን በረከቱን እንደምትቀበል በማመን አዳኝህን አክብር። ኃይል ሁሉ ጥበብ ሁሉ በእኛ ቁጥጥር ሥር ነው። ማድረግ ያለብን መጠየቅ ብቻ ነው።"—The Ministry of Healing, p. 514.

## 2. በመተማመን የተጠናከረ

### ሀ. የአምላክን ጥበብ ከራሳችን አልፎ ተርፎም በሕይወታችን ውስጥ ካሉት የተለመዱ ነገሮች የላቀ እንደሆነ አድርገን የምንመለከተው ከሆነ ምን ጥቅም እናገኛለን? ምሳሌ 3፡3-8

“ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው ፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን ይሰጠዋልም። እንዲህ ዓይነቱ የተስፋ ቃል ከወርቅ ወይም ከብር የበለጠ ዋጋ አለው። በትሑት ልብ በእያንዳንዱ ችግር እና ግራ መጋባት ውስጥ መለኮታዊ መመሪያን ከፈለግክ፣ የጸጋ መልስ እንደሚሰጥህ በቃሉ ቃል ገብቷል። ቃሉም ፈጽሞ ሊወድቅ አይችልም። ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሉ ግን አያልፍም። በጌታ ታመኑ፣ ከቶ አታፍሩም። “በሰው ከመታመን በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል። በአለቆች ከመታመን በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል።”

“በሕይወት ውስጥ ምንም ዓይነት የሥልጣን ቦታ ብንይዝ፣ ሥራችን ምንም ይሁን ምን እርዳታ እንደሚያስፈልገን እንዲሰማን ትሑት መሆን አለብን። በእግዚአብሔር ቃል በመደገፍ፣ ሁሉንም ነገር እርሱ እንደሰጠን እውቅና በመስጠትና ነፍሳችንን በጸሎት በፊቱ በማፍሰስ ታማኝ መሆን አለብን። በራሳችን ማስተዋል ከተደገፍን፣ ውድ ወንድሞቼ፣ በአለም ውስጥ ስንጓዝ፣ ሀዘንና ብስጭት እናጭዳለንና። በፍጹም ልብህ በጌታ ታመን፣ እርሱ እርምጃህንም በጥበብ ይመራል፣ የሚያስፈልጉህ ነገሮች ሁሉ በዚህም ሆነ ለቀጣዩ ሕይወት የተሟሉ ይሆናሉ። ብርሃንና እውቀት ያስፈልግሃል። ከእግዚአብሔር ካልሆነ ደግሞ ከራስህ ልብ ትመካከራለህ፤ ከልብህ ጋር ከሆነ የተመካከርከዉ በራስህ ጭስ ውስጥ ትባዝናለህ፣ ከአምላክ ጋር ከሆነ ደግሞ መለኮታዊ ብርሃንን ከጽድቅ ፀሐይ ወደ ራስህ ትሰበስባለህ።”—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 427.

### ለ. መመሪያ ለማግኘት በሌሎች ሰዎች ላይ ከመደገፍ ራሳችንን ማላቀቅ ለምን ያስፈልገናል? ኤርምያስ 17:5-8

“ግራ መጋባት ሲፈጠርና ችግሮች ሲያጋጥሙህ ከሰው ልጅ ዘንድ እርዳታ አትፈልግ። ሁሉንም ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ። ችግሮቻችንን ለሌሎች የመንገር ልምዳችን ደካሞች ያደርገናል እንጂ ጥንካሬን አያመጣልንም። የመንፈሳዊ ድክመቶቻችንን ሸክም በእነርሱ ላይ ይጭንባቸዋል፣ እነሱም ሊያስወግዱት አይችሉም። የማይሳሳት፣ ወሰን የሌለው አምላክ ብርታት ማግኘት እየቻልን ለምን ተሳሳችና ሟች የሆነዉን የሰዉን ልጅ እርዳታ ለምን እንሻለን።”—Christ’s Object Lessons, p. 146

## 3. የላቀ መረጋጋትን ማዳበር

**ሀ. ጌታ ልመናችንን ከመመለሱ በፊት ምን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አለብን? ያዕቆብ 1:6 (የመጀመሪያ ክፍል)፤ ማርቆስ 11፡24። በዚህ ረገድ ጥንካሬን ለማዳበር እንዴት መወሰን እንደምንችል የሚያሳይ አንድ ምሳሌ ግለጽ። 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡3–5**

"በዚህ ጉዳይ ላይ ሸክሙን በሚሸከሙት ጥቂት አገልጋዮች ላይ ያለውን ሃላፊነት የሚገነዘቡት ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው። ወንድሞች እነዚህን ሰዎች፣ በራሳቸዉ ሊፈቷቸዉ በምችሏቸዉ በጥቃቅን ጉዳዮቻቸውን እነሱ እንዲፈቷቸዉ ወይም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያንን ፈተናዎች ለመፍታት ከሥራቸው ላይ ደጋግመው ይጠሯቸዋል። "ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፣ እርሱም ይሰጠዋል።" ነገር ግን በጸሎት ትጉና ታታሪ መሆን አለበት። ቀራጥ ካልሆነ፣ ጌታ የገባውን ቃል እንደሚፈጽም ያለማቋረጥ የሚጠራጠር ከሆነ ምንም አያገኝም።

"ብዙዎች ለራሳቸው ወደ እግዚአብሔር ከመሄድ ይልቅ ይህን ርካሽ መንገድ በማሰብ አገልጋዮቻቸውን ከእግዚአብሔር ብርሃን እንዲያመጡላቸው ይፈልጋሉ። እንደዚህ ሲያደርጉ ብዙ ነገርን ያጣሉ። ክርስቶስን በየቀኑ ከተከተሉና እርሱን መሪና አማካሪ ካደረጉት፣ ስለ ፈቃዱ ግልጽ እውቀት ሊያገኙና በዚህም ጠቃሚ ልምድ እያገኙ ይሄዳሉ። እውነትን የሚያምኑ አንዳንድ ወንድሞች ይህን ልምድ በማጣታቸዉ በሌሎች ሰዎች ብርሃን ይመላለሳሉ። ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ምንም አይተዋወቁም እንዲሁም ስለ ፈቃዱ ምንም እውቀት የላቸውም፣ ስለዚህም በቀላሉ እምነታቸው ይሸረሸራል። እነሱ ያልተረጋጉ ናቸው፣ ምክንያቱም ለራሳቸዉ ልምድ ለማግኘት በሌሎች ላይ የመመርኮዝ እምነት ነበራቸውና።"—Testimonies for the Church, vol. 2, pp. 643, 644.

**ለ. ክርስቲያን ነኝ የሚል ግን እምነቱ የሚዋልል ከሆነ ከምን ጋር ይነጻጸራል? ያዕቆብ 1:6 (የመጨረሻው ክፍል)፤ ዘፍጥረት 49:4 (የመጀመሪያ ክፍል) ይህን እንዴት ማስወገድ እንችላለን?**

"የአብዛኞቹ ክርስቲያኖች ለጉባኤና ለጸሎት አንድ ላይ መሰብሰባቸውን በማቋረጥ ለጥቃት ቸል ቢሉ እምነታቸው ይናወጣል።"—Ibid., vol. 4, p. 106

"የክርስቶስን ቃል እንደ ማረጋገጫ ያዙ። ወደርሱ እንድትመጡ አልጠራችሁምን? ተስፋ በሌለውና ተስፋ በሚያስቀርጥ ሁኔታ መንገድ በፍጹም እንዳትናገር። ይህን ካደረግክ ብዙ ታጣለህ። ይህም ከላይ ላዩን በመመልከት ብቻ ችግሮችና ጫናዎች ሲደርሱ ማጉረምረምህ፣ መናኛና ደካማ እምነት እንዳለህ ያሳያል። ስትናገርም ሆነ ስትሠራ፣ እምነትህ የማይበገር ይመስል።"—Christ's Object Lessons, pp. 146, 147

## 4. የተከፋፈለ ልብን ማስወገድ

### ሀ. ጥበብ ለማግኘት የምናቀርበው ጸሎት ምላሽ እንደሚያገኝ እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን? ሉቃስ 18:1፤ ያእቆብ 1:6፣ 7

“[ጥበብን ለማግኘት የሚደረግ] ልመና ከአእምሮ የወጣ፣ ትርጉም የለሽ ጸሎት መሆን አይደለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመወሰን ከጥበብ ጉድለት የሚመነጨው ጠንካራ የልብ ፍላጎትን የሚገልጽ ጸሎት ነው።

“ከጸሎቱ በኋላ፣ መልሱ ወዲያውኑ ካልመጣ ለመጠበቅ አይታክቱና የተረጋጋችሁ ሁኑ፤ አትጠራጠሩም። የጠራችሁ የታመነ ነው እርሱም ደግሞ ያደርጋል የሚለውን የተስፋ ቃል ያዙ። እንደ መበለትዋ ሴት፣ ለዓላማችሁ ጽኑ። ነገሩ ለእርስዎ ጠቃሚና ትልቅ ውጤት ያለዉ ነውን? በእርግጥ አዎ፡ ፡ እምነታችሁ ሊፈተን ይችላልና አትጠራጠሩ። የምትመኙት ነገር ዋጋ ያለው ከሆነ ለጠንካራ፣ ልባዊ ጥረት ይገባዋልና። የተስፋው ቃል አለላችሁ፤ ትጉና ጸልዩ። ጽኑ ሁኑ፣ ጸሎቱ ምላሽ ያገኛል፤ ተስፋ የሰጠውስ አምላክ አይደለምን? እሱን ለማግኘት አንድ መስዋዕትነት የሚያስከፍልዎት ከሆነ ሲያገኙት የበለጠ ያመሰግናሉና። የምትጠራጠሩ ከሆነ ከጌታ አንዳች ነገር እንደምትቀበሉ እንዳታስቡ በግልፅ ተነግሯችኋል። እንዳትዝሉ፣ ነገር ግን በተስፋው ላይ ጸንተን እንድትኖሩ ማስጠንቀቂያ እዚህ ተሰጥቷል። ጤቁም አብዝቶም ይሰጣችኋል።

ብዙዎች የሚሳሳቱበት ቦታ እዚህጋ ነዉ። ከዓላማቸው ይርቃሉ፣ እምነታቸውም ይወድቃል። የብርታታችን ምንጭ ከሆነው ከጌታ ምንም የማያገኙት በዚህ ምክንያት ነው። እንደ ዕውርም እየተሰናከሉ በጨለማ መሄድ አያስፈልግም። ጌታ ብርሃንን ሰጥቷቸዋልና እነርሱም እሱ ባዘዘው መንገድ ቢሄዱና የራሳቸውን መንገድ ባይመረጡ ሁሉም ይከናዉንላቸዉ ነበር። የዕለት ተዕለት ሥራዎችን በትጋት መፈጸምን ይጠይቃቸዋል።”—Testimonies for the Church, vol. 2, pp. 130, 131.

### ለ. ለምንድነው ከተከፋፈለ ሀሳብ መራቅ ያለብን? ያዕቆብ 1:8፤ መዝሙረ ዳዊት 86:11

“ክርስቲያን ነን እያሉ ብዙዎች የዓለምን ቀርጽ አላቸው፣ እናም ፍቅራቸው በአምላክ ላይ የተመሠረተ አይደለም። በአንድ ጊዜ እግዚአብሔርንና ጣኦትን ለማገልገል እየሞከሩ ያሉ ባለ ሁለት አስተሳሰብ ናቸው። . . . ሁለት ጌቶችን ለማገልገል በመሞከር፣ በመንገዳቸው ሁሉ ያልተረጋጉ ስለሆኑ በየትኛዉም ሊመኩ አይችሉም። . . .

“የሰይጣን ሥራ አጸያፊ እነደሆነ የሚያሳዩ ቃላቶችን መናገር፣ ነገር ግን በተግባር ወደ እርሱ አሳብ ሁሉ ሰተት ብሎ መግባት፣ ምን ይጠቅማል? ይህ ባለሁለት ዓይነት አስተሳሰብ ባለቤት መሆን ነው።”—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 938.

ሐሙስ **መስከረም 30**

## 5. ያዕቆብን ማስታወስ

## ሀ. የሱስ የአምላክን ፈቃድ ለመፈጸም የሚያስችል ጥንካሬ ለማግኘት ልመናችንን ማቅረብ ያለብን እንዴት ባለ ብርታት እንደሆነ የገለጸው እንዴት ነው? ማቴዎስ 11፡12

*"የሰማዩ መንግሥት ግፍ ተፈጸመባት ፥ ግፈኞችም ያዙአት። ይህ ጥቃት በሙሉ ልብ ውስጥ ይይዛል። ሁለት አስተሳሰብ መያዝ ማለት አለመረጋጋት ማለት ነው። ለዝግጅት ስራ ቆራጥነት፣ ራስን መካድና የተቀደሰ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ማስተዋልና ኀሊና አንድ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ፈቃዱ ለሥራ ካልበረ ውድቀት ይከተለናል። ሁሉም ሀሳቦችና ስሜቶች በሥራዉ ላይ መሳተፍ አለባቸው። ቅንዓትና ልባዊ ጸሎት የግድየለሽነትንና የቸልተኝነትን ቦታ መውሰድ አለባቸው። በትጋት፣ በቁርጠኝነት እና በክርስቶስ ትሩፋቶች ላይ በማመን ብቻ ማሸነፍና ሰማን ማግኘት እንችላለን። የስራ ጊዜያችን አጭር ነው። ክርስቶስ በቅርቡ ዳግም ይመጣል።"*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 1, p. 1096.

*"የመቀበል እድል ባገኘነዉ በታላቅ እውነት እና በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ስር ህያው የብርሃን መስመሮች መሆን እንችላለን። ከዚያም ወደ ምሕረት መክደኛው መቅረብ እንችላለን፤ የተስፋውንም ጨረር በማየት በተሰበረ ልብ በመንበርከክ ሽልማትን በሚያስገኝ መንፈሳዊ ወጊያ መንግሥተ ሰማያትን እንፈልግ። ያዕቆብም እንዳደረገዉ ታግለን በጉልበት እናገኘዋለንና። ያኔ መልእክታችን የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል ያለዉ ይሆናል። ልመናችን በትጋትና በታላቅ ፍላጎት ስሜት የተሞላ ይሆናል። እኛም የጠየቅነዉን ነገር አንከለከልም። የያዝነዉም እውነት የሚገለጸው በህይወታችንና በባህርያችን፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ ባለው ሕያው ፍም በተነካው ከንፈራችን ነው።*

*"ይህ ልምዳችን የኛ ሲሆን፣ በጣም ከልብ ከምንከባከበው ከምስክኑና ርካሹ ማንነታችን እንወጣለን። ከሚያበሰበሰዉ ከራስ ወዳድነት ኃይል ልባችንን ባዶ እናደርጋለን፣ ለእግዚአብሔርም በምስጋናና በዉዳሴ እንሞላለን። ክርስቶስን ያከበረ የጸጋ ሁሉ አምላክ የሆነውን ጌታን እናከብራለን። ኃይሉንም በእኛ ይገልጣል፥ በመከሩም እርሻ እንደስለታም ማጭድ ያደርገናል። አምላክ ሕዝቡን የጠራዉ እርሱን ለሌሎች እንዲገለጡ ነዉ።"*—Reflecting Christ, p. 217.

አርብ ጥቅምት 01

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. *ከሰማይ የላቀ ጥበብ ለማግኘት አንዳንድ አስፈላጊ ቁልፎችን ግለጽ።*
2. *በሰዎች እውቀት ላይ በመታመን ስንረካ ምን ይሆናል?*
3. *አገልጋዮችን ነጻ በማውጣት በአዲስ ነፍሳት ላይ እንዲያተኩሩ የበኩሌን ማድረግ የምችለው እንዴት ነው?*
4. *ከማስበው በላይ በየትኞቹ የሕይወት ዘርፎች የበለጠ ባለሁለት አሳብ ልሆን የምችለዉ?*
5. *በመጨረሻው ቀን የያዕቆብን ተጋድሎ ኃይልና አስፈላጊነት ግለጽ።*

3ኛ ትምህርት                    ሰንበት፣ ጥቅምት 09፣ 2017

## ፈተናን መጋፈጥ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፦"በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።" (ያዕቆብ 1፡12)።**

"ከጸሎታችሁ ጋር በሚስማማ መንገድ ተናገሩ። ፈተና እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑን ካረጋገጠ ወይም ጸሎታችሁ መልክ (ቅርጽ) ብቻ እንደሆነ የሚያሳዩ ከሆነ በእናንተ ላይ የሰማይና የምድርን ያህል ርቀት ያለዉ ለውጥ ያመጣባችኋል።"—Christ's Object Lessons, p. 146.

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, **vol. 3, pp. 477–492.**

እሁድ                                                    **ጥቅምት 03**

### 1. የመንፈሳዊ እድገት ምክንያቶች

### ሀ. ያዕቆብ 1:2 በሕይወታችን እንዴት እንደሚፈጸም ምሥጢሩን ግለጽ። ነህምያ 8:10

"እንደ አስተማሪ የምንቀበላቸዉ ፈተናዎች ሁሉ ደስታን ይፈጥራሉ። መላው ሃይማኖታዊ ሕይወት የሚያንጽ፣ ከፍ የሚያደርግ፣ የሚያስደስት፣ በመልካም ቃላትና ሥራዎች መዓዛ ያላቸው ይሆናሉ። ጠላት በተስፋ መቁረጥ፣ በጭንቀት፣ በሐዘን እና በመቃተት ላይ ያሉ ነፍሳትን በማግኘቱ ይደሰታል። የእምነታችንን ውጤት በተመለከተ እንዲህ ዓይነት አመለካከት እንዲኖረን ይፈልጋል። ነገር ግን አስተሳሰባችን አሽቀልቁሎ አእምሯችን ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳይደርስ እግዚአብሔር ይሻል። እያንዳንዱ ነፍስ በቤዛው ኃይል አሸናፊ እንዲሆን ይፈልጋል።"— Testimonies for the Church, vol. 6, pp. 365, 366

### ለ. አምላክ ፈተናዎች እንዲደርሱብን የሚፈቅደው ለምንድን ነው? ያዕቆብ 1:3፤ ሮሜ 5፡3

"የሚገጥሙንን ውጣ ውረዶች ተቋቁመን በሰይጣን ፈተና ላይ ድል የምንጎናጸፍ ከሆነ በእምነታችን ዙሪያ የሚመጡትንም ፈተናዎች እንዲሁ በማለፍ ከወርቅ ይልቅ የከበርን—ቀጣዩን ፈተና ለመቋቋም ጠንካራና የተሻለ ዝግጅት ያለን እንሆናለን። ነገር ግን ቁልቁል የምንሰጥምና ለሰይጣን ፈተናዎች መንገድ የምንከፍት ከሆነ እየተዳከምን በመሄድ በፈተናው ድል አንቀዳጅም። … ለቀጣዩም ፈተና በቂ ዝግጅት አይኖረንም። በዚህ መልኩ የሰይጣን ፈቃድ ምርኮኛ እስክንሆን እየቀጨጭን እንሄዳለን። መላውን የእግዚአብሔር የጦር ትጥቅ ዕቃ ለብሰን በማንኛውም ወቅት ከጨለማው ኃይል ሊነሳ ለሚችል ተጋድሎ ዝግጁ ልንሆን የግድ ነው።"—Early Writings, p. 46.

## 2. ካሰብነው የተሻለ ውጤት

### ሀ. ትዕግስትን በመለማመድ ያለውን ጥቅም ግለጽ። ያእቆብ 1:4፤ ሉቃስ 21፡19

"እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ጸሎታችንን በምንፈልገው መንገድና ሰዓት ሊመልስልን ይችላል፣ ነገር ግን እርሱ ከዚያ በላይ ጥበበኛና መልካም ነው። ምኞታችንን ሁሉ ከማሳካት የበለጠና የተሻለ ነገር ያደርግልናል። በጥበቡና በፍቅሩ ስለምንታመን፣ በፈቃዳችን እንዲሸነፍ ልንጠይቀው አይገባም፣ ነገር ግን በእርሱ አላማ ዉስጥ ለመግባትና አላማውን ለመፈጸም መፈለግ አለብን። ምኞታችንና ፍላጎታችን በእርሱ ፈቃድ ዉስጥ መስጠም አለበት። እምነትን የሚፈትኑ እነዚህ ተሞክሮዎች ለእኛ ጥቅም ናቸው። በእነሱ አማካኝነት እምነታችን እውነት እና ቅን፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ብቻ የተመሠረተ፣ ወይም እንደሁኔታው የማይቀያየርና የማይለዋወጥ እንደሆነ ይገለጣል። እምነት የሚጠናከረው በተግባር ነው። በቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ ጌታን ለታጋሾች የተገቡላቸዉ ውድ ተስፋዎች እንዳሉ በማስታወስ ትዕግሥት ፍጹም ሥራውን በሕይወታችን እንድሠራ ልንፈቅድለት ይገባል።"—The Ministry of Healing, p. 231.

### ለ. ያዕቆብ እንዴት እና ለምን በዚህ ብልሹ ዓለም ውስጥ ስላለው የሥልጣንና የብልጽግና ጊዜያዊ አመለካከት የበለጠ ትልቅ ሥዕል ያሳየናል? ያዕቆብ 1፡9-11

"በዚህ ጊዜ፣ ከታላቁ የመጨረሻ ተጋድሎ በፊት፣ ልክ ከዓለም የመጀመሪያው ጥፋት በፊት እንደሆነዉ፣ ሰዎች በተድላና በገዛ ፍላጎቶች ይጠመዳሉ። በሚታዩትና አላፊ ነገሮች የተጠመዱ ሁሉ፣ የማይታየውንና ዘላለማዊውን እይታ ያጣሉ። አሁን ተጠቅመዉ ለሚጨርሱት ነገሮች የማይጠፋዉን ሀብት እየሠዉ ነው። አእምሯቸው ከፍ ሊል፣ የሕይወት አመለካከታቸው ሊሰፋ ይገባል። ከዓለማዊ ህልም ግድየለሽነት መንቃት ያስፈልጋቸዋል።

"በቅዱስ ጽሑፍ ገጾች ላይ በግልጽ እንደተገለጸው የመንግሥታት መነሳትና መውደቅ፣ ውጫዊና ዓለማዊ ክብር ምን ያህል ዋጋ እንደሌለው መማር ያስፈልጋቸዋል። ባቢሎን፣ በሙሉ ኃይሏና በታላቅነቷ፣ ዓለማችን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አይታ የማታውቀው፣ በዚያን ጊዜ ለነበሩት ሰዎች በጣም የተረጋጋና ዘላቂ የሚመስለው ኃይልና ግርማ የነበራት፣ እንዴት ባለ መንገድ ሙሉ በሙሉ አለፈች! እንደ 'የሣር አበባ' ጠፋች። ስለዚህ መሠረቱ እግዚአብሔር ያልሆነበት ሁሉ ይጠፋል። ከዓላማው ጋር የተሳሰረና ባህሪውን የሚገልጽ ብቻ ነው የሚጸናው። ዓለማችን የምታውቃቸው ብቸኛ ነገሮች የእርሱ መሠረታዊ ሥርዓቶች ናቸው።"—Education, p. 183.

"ዓለማዊ ውድ ሀብት ሁሉ ጊዜያዊ ነው። ዘላለማዊ ሀብት ማግኘት የምንችለው በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው።"—The Review and Herald, December 10, 1901.

## 3. በጦርነቱ ሙቀት ውስጥ

### ሀ. ፈተና ሲደርስብን በጸሎት ምን ማድረግ አለብን? ለምንስ? ያእቆብ 1:12

“ማስመሰልንና ስሜትን ሁሉ አስወግድ። ቀላልና ተፈጥሯዊ እራስህን ሁን። በማንኛውም ሐሳብ፣ በቃልም ሆነ በሥራ እውነተኛ ሁን፤ እንዲሁም ‘እያንዳንዱ ለሌላው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር።’ መቼም ቢሆን ሥነ ምግባራዊ ተፈጥሮ በቋሚ ንቃትና ጸሎት መደገፍ እንዳለበት አስታውስ። ወደ ክርስቶስ እስከተመለከትክ ድረስ ደህና ነህ፤ ነገር ግን መሥዋዕትነቶችህንና ችግሮችህን ባሰብክበት ጊዜ፣ እንዲሁም ለራስህን ማዘን በጀመርክ ጊዜ፣ በአምላክ ላይ ያለህን እምነት ታጣለህ እናም ትልቅ አደጋ ላይ ትወድቃለህ።”—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 522.

“ከመልካም ሥራ ልባችን ሳናዞር ወይም ተስፋ ሳንቆርጥ፣ በመንገዳችን ላይ የሚያጋጥሙን ፈተናዎች ምክንያት ምንም ዓይነት የሞራል ጨለማ ሊሸፍነን ቢሞክር እንኳ፣ በጸጥታ ወደ ፊት መሄድ አለብን። ትዕግስት፣ እምነትና ሥራችን መውደድ ልንማርባቸው የሚገቡ ትምህርቶች ናቸው። ራስን መግዛትና የሱስን መመልከት የዕለት ተዕለት ሥራ ነው። ጌታ በእርሱ የታመነችውንና የእርሱን እርዳታ የምትፈልግ ነፍስን ፈጽሞ አይተወውም። የሕይወት አክሊል የሚቀመጠው በአሸናፊው ራስ ላይ ብቻ ነው።”—Ibid., vol. 5, pp. 70, 71

### ለ. እግዚአብሔር መከራዎችንና ፈተናዎችን ይልካል ማለት ስህተት የሆነዉ ለምንድነው? ያእቆብ 1:13

“ለኃጢአት ሰበብ በማቅረብ በደላችንን ለመቀነስ መሞከር የለብንም። እግዚአብሔር ለኃጢአት ያወጣዉን ዋጋ ተመን (ግምት) መቀበል አለብን፣ ያ ደግሞ በእውነተም ከባድ ነው። የኃጢያትን አስከፊነት መግለጥ የምችለዉ ቀራንዮ ብቻ ነዉ። . . .

“ፈተና ኃጢአትን እንድናደርግ የሚገፋፋ ማታለያ ነው፣ ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር አይደለም፣ ከሰይጣንና ከልባችን ክፋት እንጂ። “እግዚአብሔር በክፉ አይፈትነንም፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም።” ያዕቆብ 1:13

“ሰይጣን እኛን ወደ ፈተና ሊያገባን ይፈልጋል፣ የባህሪያችን ክፋት በሰውና በመላእክት ፊት ይገለጥ ዘንድ፣ እኛን የራሱ አድርጎ ለመያዝ ሲል ይህንን ያደርጋል። . . . ጠላት ወደ ኃጢአት ይመራናል፤ ከዚያም ለአምላክ ፍቅር የማይገባን አድርጎ በመለኮታዊ ዓለማት ፊት ከሰሰ።”—Thoughts From the Mount of Blessing, pp. 116, 117.

### ሐ. ከሳሹ የቆሸሸዉን ባህሪያችንን እያሳዬ ሲከስ፣ ጌታ እንዴት ይቆምልናል? ዘካርያስ 3:1-4፤ 1ኛ ዮሐንስ 1:9–2:1

## 4. በድካማችን ላይ የእግዚአብሔር ጥንካሬ

### ሀ. በጌታ ጸሎት ውስጥ “ወደ ፈተና አታግባን” የሚለውን ሐረግ አብራራ ። ማቴዎስ 6:13 (የመጀመሪያ ክፍል)፤ ት. ኢሳ 30፡21

“[እግዚአብሔር] እንቅፋትን፣ ስደትን፣ እና ችግሮችን እንድንጋፈጥ የፈቀደልን እንደ እርግማን ሳይሆን እንደ የህይወታችን ታላቅ በረከት ነው። በጀግንነት ተቋቁመን የምናሳልፈዉ እያንዳንዱ ፈተና ፣ አዲስ ልምድ ይሰጠናልና በባህሪይ ግንባታ ስራችን ላይ እድገት ያመጣልናል። በመለኮታዊ ኃይል ፈተናን የምትቃወም ነፍስ የክርስቶስን ጸጋ ብቁነት ለዓለምና ለመለኮታዊ ዓለማት ትገልጣለች።

“ነገር ግን ምንም እንኳን መራራ ቢሆንም ፈተናን ባንፈራም፣ እግዚአብሔር በገዛ ክፉ ልባችን ፍላጎት ወደምንወሰድበት ገደል እንድንወስድ እንዳይፈቅድ መጸለይ አለብን። ክርስቶስ የሰጠውን ጸሎት በማቅረብ፣ በመልካም ጎዳና እንዲመራን በመጠየቅ፣ እራሳችንን ለእግዚአብሔር መሪነት እናቀርባለን። ይህንን ጸሎት በቅንነት ማቅረብ ካልቻልን፣ በመረጥነው በማንኛውም መንገድ ለመራመድ እንወስን ይሆናል። እጁ እንዲመራን ብንጠብቅ መልካም ነዉ። . . .

“ለሰይጣን ጥቆማዎች በመገዛት የምናገኘውን ጥቅም በማሰብ ዉሳኔ ለመስጠት መዘግየታችን ትልቅ ችግር አለው። ኃጢአት ማለት ውርደትና ጥፋት ማለት ነዉ፣ ይህም ወደ ኃጢአት ለሚቀርብ ነፍስ ሁሉ ነው። ነገር ግን ኃጢአት በባህሪው የሚያሳውርና አታላይ ነው፣ እንዲሁም በሚያማምሩ አቀራረቦች ቀርቦ ያታልለናል። በሰይጣን ግዛት ላይ ራሳችን ካስቀመጥን ከኃይሉ እንደምንጠበቅ ምንም ማረጋገጫ የለንም። ኃጢአት ሁል ጊዜ በዙሪያችን ስላለ፣ ፈታኙ እኛን ሊያገኝ የሚችልበትን መንገዶች ሁሉ መዝጋት ይኖርብናል።

“‘ወደ ፈተና አታግባን’ የሚለው ጸሎት ራሱ የተስፋ ቃል ነው።”—Thoughts From the Mount of Blessing, pp. 117, 118.

### ለ. ፈተናን በተመለከተ አምላክ ምን ተማጽኖና ማረጋገጫ ሰጥቶናል? ያዕቆብ 1:14–16፤ 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 10:13

“ፈተና ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ልጆች ነን የሚሉ ሁሉ የሚፈተሹበትና የሚፈተኑበት መንገድ ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን እንደፈተነ፣ የእስራኤልን ልጆች እንደፈተነ እናነባለን። ይህ ማለት እምነታቸውን ለመፈተሽና እርዳታ ለማግኘት ወደ እርሱ እንዲመለከቱ ለመምራት ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ፈቀዱል ማለት ነዉ። እግዚአብሔር ዛሬ ረዳታቸው መሆኑን እንዲገነዘቡ ፈተናን ወደ ህዝቡ እንዲመጣ ፈቅዱል። በሚፈተኑበት ጊዜ ወደ እሱ ከቀረቡ፣ ፈተናውን እንዲቋቋሙ ያበረታቸዋል።”—In Heavenly Places, p. 251.

ሐሙስ ጥቅምት 07

## 5. ፈተናዎችን የምንመለከትበት እይታ

### ሀ. በክርስቶስ ለመኖርና ከፈተናዎች ለመዳን ሁል ጊዜ ምን መምረጥ አለብን? ሉቃስ 4:8፤ ፊልጵስዩስ 1፡21

"ፈታኙ ክፉ ነገር እንድናደርግ ሊያስገድደን አይችልም። በራስ ፈቃድ ካልተገዙለት በቀር ሰይጣን አእምሮን መቆጣጠር አይችልም። ሰይጣን በእኛ ላይ ኃይሉን ለማሳየት የሚችለው ፈቃደኞች ስንሆንና የሃይማኖት እጃችን ክርስቶስን ሲለቅ ብቻ ነው። መለኮት ከእኛ የሚፈልገውን ለማሟላት ባፈገፈግን ቁጥር ሰይጣን ሊፈትነንና ሊያጠፋን መግቢያ በር ያገኛል። የእኛ ውድቀት ወይም ሽንፈት ክርስቶስን ለመንቀፍ ለሰይጣን ጥሩ አጋጣሚ ይሆንለታል።"—The Desire of Ages, p. 125.

### ለ. በክርስቶስ ወደ ድል እንድንገሰግስ የሚያነሳሳን ምንድን ነው? ፊልጵስዩስ 4:13፤ ራእይ 2:10 (የመጨረሻው ክፍል)፤ 3፡21።

"የክርስቶስን መንፈስ የተላበሰ ሁሉ በክርስቶስ ይኖራል። በእሱ ላይ ያነጣጠረው የትኛዉም ምት ሁሉ ዙሪያዉን በከበበዉ በአዳኙ ላይ ያርፋል። ወደ እርሱ የሚመጣው ማንኛዉም ነገር ከክርስቶስ ዘንድ ነው። ክፋትን መቃወም አያስፈልገውም፣ ምክንያቱም ክርስቶስ መከላከያው ነውና። በጌታችን ፈቃድ ካልሆነ በቀር ምንም ሊነካው አይችልም፣ እና 'የተፈቀደው ሁሉ' 'እግዚአብሔርን ለሚወዱት ለበጎ ነዉ። ሮሜ 8:28።"—Thoughts From the Mount of Blessing, p. 71.

"የሕይወት ዘውድ የሚደረገዉ በአሸናፊው ራስ ላይ ብቻ ነዉ። በሕይወት ሲንኖር ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ ለእግዚአብሔር የምሠሩት ልባዊ ሥራ አለ።"—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 71.

አርብ ጥቅምት 08

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. በሚቀጥለው ጊዜ አስቸጋሪ ፈተና ሲመጣብኝ ምን ማስታወስ አለብኝ?
2. አምላክ ለጸሎት መልስ ስለሚሰጥበት መንገድ ምን ማወቅ አለብኝ?
3. ፈተናዎችና መከራዎች የሚመጡት ከየት ነው? ለምንስ?
4. ፈተናን በምንቋቋምበት ጊዜ ምን እንሆናለን?
5. በክርስቶስ ሙሉ በሙሉ እንዴት ልኑር?

## 4ኛ ትምህርት ሰንበት፣ ጥቅምት 16፣ 2017

## እምነትን በተግባር ላይ ማዋል

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ።" (ያዕቆብ 1፡22)።**

የሰዉ ልጅ የተሾመዉ ከእግዚአብሔር አፍ ለሚወጣ ቃል ሁሉ እንዲታዘዝና ሰሚ ብቻ ሳይሆን ቃሉን የሚያደርግ እንዲሆን ነው።"—Testimonies to Ministers, p. 454.

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, **vol. 2, pp. 24–26, 50–55, 164, 165**

እሁድ **ጥቅምት 10**

### 1. ፍጹም ሰጪው

**ሀ. የእግዚአብሔርን ታላቅ ቸርነት የሚገልጠው ምንድን ነው? ያእቆብ 1:17**

"ክርስቶስ ለልጆቹ ያለው ፍቅር ጠንካራ እንደሆነ ያህል የሚራራ ነው። ከሞትም ይልቅ ብርቱ ነው፤ እርሱ የእኛን መዳን ሊዋጀን እና ከእርሱ ጋር በታላቅ ምስጢርና በዘላለማዊነት አንድ ሊያደርገን ሞቶአልና። ፍቅሩ በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ኃይሎቹን ሁሉ ይቆጣጠራል፣ እናም መላውን የሰማይን ሀብት ለህዝቡ መልካም ለማድረግ ይጠቀምበታል። ያለ ተለዋዋጭነት ወይም በማይዞር ጥላ - ትላንትና፣ ዛሬና ለዘላለም ያው ነው። ምንም እንኳን ኃጢአት ይህን ፍቅር ለመቃወም እና ወደ ምድር የሚፈሰውን ውሃ ለማደናቀፍ እየሞከረ ለዘመናት የኖረ ቢሆንም፣ አሁንም ክርስቶስ ለሞተላቸው ሰዎች በብዙ ሞገድ ይፈሳል።

"እግዚአብሔር የሚያገለግሉትን እና ለትእዛዙም ሁሉ የሚታዘዙትን ኃጢአት የሌለባቸውን መላእክት ይወዳል። ነገር ግን ጸጋን አይሰጣቸውም፤ ምክንያቱም ከቶ አላስፈለጋቸውም፤ ከቶ ኃጢአትን አላደረጉምና። ጸጋ ለማይገባቸው የሰው ልጆች የተገለጠ ባህሪይ ነው። እኛ አልፈለግነውም፤ እኛን ፍለጋ ነው የተላከው። እግዚአብሔር ለተራቡና ለተጠሙ ሁሉ ጸጋን ሲሰጣቸው ደስ ይለዋል እኛ ለመቀበል የተገባን ሆነን ሳይሆን የማይገባን በመሆናችን ነው። ለመቀበል የምናሳየዉ ፍላጎታችን ብቻ ስጦታውን እንደምንቀበል ማረጋገጫ ይሰጠናል።"—Testimonies to Ministers, p. 519.

**ለ. ከእግዚአብሔር እንዴት እና ለምን ተወለድን? ያዕቆብ 1:18፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1:23፤ 2፡9።**

## 2. ግለቱን ማቀዝቀዝ

### ሀ. በቁጣ ዓለም ውስጥ እንዴት እና ለምን የተለየ መሆን አለብን? ያእቆብ 1:19

*"እርስ በርሳችሁ የስድብ ቃል እንዳትናገሩ ደንብ አድርጉ፣ ነገር ግን በቻላችሁ መጠን እንዳችሁ ሌላችሁን አመስግኑና አወድሱ።*

*"አንዳንዶች ያለገደብ መናገር ጥሩ ነገር እንደሆነ አድርገው ያስባሉ፣ እና በልባቸው ውስጥ ያሉትን የማይስማሙባቸዉን ነገሮችን የመናገር ልምዳቸውን ያወድሳሉ። የንደት መንፈስ በመሆን በነቀፋና በስህተት ፍለጋ እራሳቸዉን እንዲደክም አድርገዋል። ባወሩ ቁጥር፣ የበለጠ ይደሰታሉ፣ እና ሰይጣን ለእርሱ ስለሚስማማው ስራውን ለመርዳት ከጎናቸዉ ይቆማል። ቃሉ የተነገረለትን ሰዉ ያበሳጫል፣ በዚያም ትንሽ ነገር ወደ ታላቅ ነበልባል አድጋ እስክታቃጥል ድረስ እርስ በርስ ቃላቶችን መወራወር ይጀምራሉ። ሁለታችሁም ልትቋቋሙት ከምትችሉት በላይ የሆኑ ፈተናዎች እንዳለባችሁና በህይወቶቻችሁ ደስተኛ እንዳልሆናችሁ ሊሰማችሁ ይጀምራል። ስለዚህ ሀሳቦቻችሁን፣ ቃላቶቻችሁንና ድርጊቶቻችሁን የመቆጣጠር ስራን በቀራጥነት ጀምሩ። ከእናንተ ማናችሁም የቂም በቀል መነሣሣት ሲሰማችሁ እያንዳንዳችሁ ብቻችሁን ሆናችሁ ወደ አምላክ ጸለይ እንዳለባችሁ ለራሳችሁ መመሪያ አድርጉ።"*—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 243.

### ለ. ቁጣ አምላክን የሚያሳዝነዉ ለምንድን ነው? ፈወስ ሊያገኝ የሚችለዉስ እንዴት ነወ? ያዕቆብ 1፡20

*"አንዳንዶች ይጨነቃሉ፣ እናም በቃላቸውም ሆነ በመንፈሳቸዉ በቁጣ ራሳቸውን መግዛት ከተሳናቸዉ ከመጠዋ ስካር በበለጠ ሁኔታ በቁጣ የሰከሩ ይሆናሉ። በዚያን ጊዜ እነሱ ምክንያታዊ አይደሉም፣ እንዲሁም በቀላሉ ለማሳመን ወይም ለመመለስ የሚቻሉ አይደሉም። እንደዚህ በሚሆኑበት ጊዜ እነሱ ጤናማ አይደሉም፤ ሰይጣን ለጊዜው በእነርሱ ላይ ሙሉ ቁጥጥር አለውና። እያንዳንዳቸው እነዚህ የቁጣ ጊዜያቶች የነርቭ ሥርዓትን እና የሞራል ኃይሎችን ያዳክማሉ፣ እንዲሁም በሌላ ጊዜ ተንኳሽ ነገሮች ሲያጋጧቸዉ ቁጣን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ያደርጉባቸዋል።*

*"ለዚህ ሁኔታ አንድ መድኃኒት ብቻ አለዉ - ይህም በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ አዎንታዊ የሆነ ራስን መግዛት ማዳበር ነዉ። ራሳችንን ምቹ በሆነና የሚያናድድ ነገር በሌለበት ቦታ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ለጊዜው ሊሳካ ይችላል፤ ነገር ግን ሰይጣን እነዚህን ምስክን ነፍሳት የት እንደሚያገኛቸው ያውቃልና በደካማ ጎናቸው በኩል ደጋግሞ ያጠቃቸዋል። ስለራሳቸው አብዝተዉ እስካሰቡ ድረስ በዚህ ጉዳይ ያለማቋረጥ ይቸገራሉ። . . . ግን ለእነሱም ተስፋ አላቸዉ። ይህ በግጭቶችና በጭንቀቶች  አውሎ ንፋስ እየተወዛወዘ ያለው ህይወታቸዉ፣ ከክርስቶስ ጋር ወደ አንድነት ይምጣ ፤ ከዚያ በኋላ እራስ ለበላይነት (ክብሩን ለማስጠበቅ) መጮህ አይችልም። . . . በሐቀኝነት 'ስህተት አድርጌያለሁ' በማለት ራሳቸውን ዝቅ ማድረግ አለባቸው። እግዚአብሔር በቁጣችን ላይ ፀሐይ እንዳትገባ ተናግሯልና። ይቅር ትለኛለህ? ይበል። ይህ ብቸኛው አስተማማኝ መንገድ ነው።"*—Sons and Daughters of God, p. 142.

## 3. የሰማይን ብርሃን መዉደድ

## ሀ. ለእያንዳንዳችን የተሰጠዉን የእግዚአብሔርን ጥሪ አብራራ። ያዕቆብ 1፡21

"አሀ፣ የእውነት ብርሃን፣ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ታላቅ ብርሃን የተሰጣቸው፣ እግዚአብሔር በቃሉ እንዳያደርጉ የነገራቸውን ነገሮች በማድረግ በእርሱ ላይ ኃጢአት በመሥራት የእግዚአብሔርን ቁጣና ፍርድ እንዴት ሊቃወሙ ደፈሩ? እንደዚህ እያወቁ ኃጢአትን በመሥራት እግዚአብሔርን በፊቱ እንዲያዋርዱና ነፍሳቸውንም እንዲያረክሱ በሰይጣን እንዴት ይህን ያህል ዓይናቸዉን ሊታወሩ ቻሉ? ሐዋርያው፡- "ለዓለምና ለመላእክት፣ ለሰዎችም የአይን ማረፊያ ሆነናል" ይላል። እነዚህ ኃጢአተኞች— ግብዞች ልበላቸሁን?— በጽዮን ተራራ ላይ ያኔ ሲጠየቅ ፡ እኔ ለዓለም፣ ለመላእክት እና ለሰዎች በምን መልኩ ነበር የአይን ማረፊያቸዉ የነበርኩት? ይህንን ጥያቄ ለራሳችሁ መልስ ስጡ፣ የተሰጠኝን ብርሃን በአግባቡ ባለመጠቀም፣ በተሰጠው መብትና ምሕረት በመመረኮዝ፣ ነፍስን በሚያረክሱና በሚያበላሹ ድርጊቶች ላይ በመዋል ይሆንን?"—Testimonies to Ministers, p. 447.

## ለ. የእግዚአብሔር ቃል በተለይ በመጨረሻው ቀን ከመዳናችን ጋር እንዴት ይዛመዳል? 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:15፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:1፣ 2

"የመንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ሥራ በሰው ልብ ላይ፣ በቃሉ በኩል መከናወንን ለመስጠት ቃል ገብቷል። ክርስቶስ በቃሉ መንፈስና ህይወት እንዳለ ተናግሯል። . . .

"ሰይጣን የመላእክትን ልብስ በማልበስ የሰውን ፈጠራዎች ለማስተዋወቅ በጣም ረቂቅ በሆነ መንገድ ይሰራል። ነገር ግን የቃሉ ብርሃን በምግባር ጨለማ መካከል ይበራል፤ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ በድንቅና ተአምራቶች ፈጽሞ አይተካም። እውነት መጠናት አለበት፣ እንደተደበቀ ሀብትም መፈለግ አለበት። ድንቅ የሆኑ መገለጦች ከቃሉ ዉጪ (በተለየ መንገድ) አይሰጡም፣ ወይም የቃሉን ቦታ አይተኩም። ከቃሉ ጋር ተጣበቁ፣ ያልተበረዘውን ቃል ያዙ፣ ይህም ሰዎችን ለመዳን ጥበበኞች ያደርጋል።"—Selected Messages, bk. 2, p. 100.

"እውነትን የተቀበሉ ሰዎች ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እና ስለ ሕያው አዳኝ የተግባር እውቀት መፈለግ አለባቸው። የማሰብ ችሎታን ማዳበር፣ ማስተዋላችንም ማጠንከር አለብን። ለማወቅ ስንፍናን ማሳየት ኃጢአት ነው፣ መንፈሳዊ ግድየለሽነት ደግሞ ሞት ነው።"—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 399.

"የእርሱ የትምህርት ቃላቶች ወደ እኛ ዉስጥ ሲገቡና ቦታ ሲይዙ፣ ሀሳባችንንና ድርጊቶቻችንን የሚቆጣጠር ዘላቂ የሆነ የየሱስ መገኘት ይኖረናል። ዓለም ካየቻቸዉ ሁሉ የበላይ የሆነ ታላቅ አስተማሪ በሚሰጠው ትምህርት ተሞልተናልና።"—Messages to Young People, p. 160.

## 4. የእግዚአብሔር ሕግ መስተዋት

### ሀ. ልባችንን መመርመራችን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ያዕቆብ 1፡22-24

*“አንዳንድ ሰዎት ለሌላቸው ችሎታ ምሥጋና ይጎርፍላቸዋል። ልብን መርማሪው አምላክ ሥራን ሁሉ መዝኖ ሰዎች ያመሰግኑትን ተግባር መነሻው ራስን መውደድና ግብዝነት መሆኑን ይመዘግባል። በሕይዎታችን የምንሠራው ሥራ ሁሉ ቢመሰገንም ቢነቀፍም እግዚአብሔር ትንቢቱን መርምሮ ያገኘዋል።*

*ብዙዎች የራሳቸውን የጠባይ ጉድለት በመስታወት መመልከት አይወዱም፡፡ ጉድለትና ኃጢዓት ባይታዩም በሌሎች አየተገመገሙ ከእነርሱ ጋር ይኖራሉ፡፡ ለእግዚአብሔር ታጥቀን እንሠራለን የሚሉትን ሳይቀር ራስን መውደድ ያጠቃታቸዋል። ጠባያቸውን በእግዚአብሔር የሕግ ሚዛን ቢመዝኑነና አውነኛውን ነገር ለማወቅ ዛላፈገፈጉ ቀለው መገኘታቸው አይክዱም። አንዳንዶቹ ግን የልባቸውን ርኩሰተ ጠለቅ ብሰው ሰመመራመር አይፈቅዱም፡፡ ብዙ ነገር ሲጎድላቸው ባለማወቅ ሰማ ተከናንበው ለመኖር ይፈልጋል።”*—Gospel Workers, pp. 275, 276.

### ለ. ለክርስቶስ እና ለፈቃዱ በመገዛት በሚመጣው የመፍጠር ሃይል የእውነተኛውን የነጻነት ውበት ያብራሩ። ያዕቆብ 1:25፤ የዮሐንስ ወንጌል 8፡32

*“በማዳን ሥራ ማስገደድ የሚባል ነገር የለም። በውጫዊ ኃይል መጠቀምም የለም። በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት እያንዳንዱ ሰው ማንን ለማገልገል እንደሚፈልግ ራሱ እንዲወሰን ይደረጋል። አንድ ሰው ራሱን ለክርስቶስ በማስረከቡ ምክንያት በሚከሰተው ለውጥ ከፍተኛ የሆነ የነፃነት ስሜት ይፈጠራል። ኃጢአትን የመተው ሥራ የግለሰቡ ጉዳይ ነው። እርግጥ ነው ራሳችንን ከሰይጣን ቁጥጥር ነፃ ለማድረግ አቅም የለንም፣ ነገር ግን ከኃጢአት አርነት ለመውጣት ፍላጎት ሲያድርብንና ከእኛ ውጭና በላይ የሆነ ኃይል ለማግኘት ስንጮህ ነፍሳችን መለኮታዊ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሞላና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም በፍላጐት ይንቀሳቀሳል።*

*ሰው ነጻነቱን ለማግኘት የሚያስችለው ብቸኛው ውል ከክርስቶስ ጋር አንድነት መፍጠር ነው። «እውነትም ነጻ ያወጣችኋል፣» እውነቱም ክርስቶስ ነው። ኃጢአት በሰው ላይ ድል የሚጐናጸፈው አእምሮን በማዳከምና የነፍስን ነጻነት በመደምሰስ ነው። ለእግዚአብሔር መገዛት ማለት ወደ እውነተኛው ሰብአዊ ደረጃ ማለትም ወደ እውነተኛው ማዕረግና ሰብአዊ ክብር ተመልሶ መምጣት ማለት ነው። እንድንተዳደርበት የተደነገገ ልን መለኮታዊ ሕግ የነጻነት ሕግ ነው። ያዕ.*2:12*።”*—The Desire of Ages, p. 466.

ሐሙስ ጥቅምት 14

## 5. እውነተኛ ሃይማኖት

### ሀ. ብዙ ጊዜ የሚጎድለንን የክርስትና አስፈላጊ ገጽታ ጥቀስ። ያዕቆብ 1፡26።

"ክርስቶስ በሚሰጠው እርዳታ፣ አንደበትን መቆጣጠርን መማር እንችላለን። እርሱ በችኮላና በንዴት እንዲናገር ሲፈተን በፈተናዉ ወድቆ አንድም ቀን በከንፈሩ ኃጢአትን ሰርቶ አያውቅም። በትዕግስት በተረጋጋ መንፈሱ የተነሳ በአናጺ መሥሪያ ቦታዉ ላይ አብረው ከሚሰሩት እጅግ ብዙ ፌዝ፣ ስላቅ እና ተረባ ደርሶበታል። በቁጣ ከመመለስ ይልቅ፣ ከዳዊት ውብ መዝሙሮች አንዱን መዘመር ይጀምር ነበር። እናም ባልደረቦቹ የሚያደርጉትን ከማስተዋላቸው በፊት በመዝሙሩ ከእርሱ ጋር ይተባበሩ ነበር። በዛሬው ጊዜ ያሉ ወንዶችና ሴቶች በቃላት አጠቃቀም የክርስቶስን ምሳሌ ቢከተሉ በዚህ ዓለም ውስጥ እንዴት ያለ ለውጥ ይመጣ ነበር።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 936.

### ለ. እውነተኛው ሃይማኖት በጸጥታ፣ ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ መንገድ ከመጋረጃ ጀርባ እንዴት ይሠራል? ያዕ 1፡27።

"አገልጋይ መሆን፣ እራስን መካድ በሚጠይቀው በጎ ስራ በትዕግስት መቀጠል፣ ሰማይ ደስ የሚሰኝበት ክቡር ሥራ ነው። ለእግዚአብሔር እጅግ እንቀናለን ከምንለዉና እጅግ ቅዱስ አምልኮ ነዉ ብለን ከምናስበዉ አምልኮ ይልቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ታማኝ ሥራ ነዉ። እውነተኛ አምልኮ ከክርስቶስ ጋር አብሮ መሥራት ነው። ጸሎቶች፣ ምክሮችና ንግግሮች ብዙ ጊዜ የምናሳያቸዉ ርካሽ (ተራ) ፍሬዎች ናቸው፤ ነገር ግን በበጎ ሥራ የሚገለጥ፣ ችግረኞችን፣ ድሀ አደጎችንና መበለቶችን በመንከባከብ የሚገለጡት ፍሬዎች እውነተኛ ፍሬ ናቸው፤ በተፈጥሯቸው የሚበቅሉትም በመልካም ዛፍ ላይ ነዉ።"—Testimonies for the Church, vol. 2, p. 24.

አርብ ጥቅምት 15

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. ለምንድነው በዘላለማዊው በሰማይ አምላክ የምንታመነዉ?
2. ቁጣቸውን መቆጣጠር ለሚከብዳቸዉ ሁሉ ግዴታቸው ምንድን ነው?
3. የእግዚአብሔርን ቃል ለራሴ ማጥናት ለምን አስፈለገኝ?
4. እውነተኛ ነፃነት ምን እንደሆነ አስረዳ።
5. እውነተኛውን ሃይማኖት ከልቤ ማዳበር የምችለው እንዴት ነው?

## ሰንበት፣ ጥቅምት 23፣ 2017

# የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ ለጄነራል ኮንፈራንስ ሥነ ጽሑፍ ክፍል

"አንድ የቀለም ጠብታ አንድ ሚሊዮን ሰው እንዲያስብ ሊያደርግ ይችላል" የሚል ታዋቂ አባባል አለ። የታተሙ ጽሑፎች ከንግግር ቃላቶች የበለጠ ክብደትን የመሸከም አዝማሚያ አላቸው በተለይም በቋሚነታቸዉ። በጽሑፍ ሲሆን፣ በራሳችን ፍጥነት ለማንበብ ጊዜ ወስደን፣ እንዲሁም ወደ ኋላ በመመለስ ለመማር የምንፈልገውን መረጃ በጥልቀት ማጤን እንችላለን። ጥልቅ መንፈሳዊ ርእሶችን ለመቅሰም ስንሞክር ይረዳናል።

ይህ በታሪክ ውስጥ እውነት ነው፡- "የሉተር ብዕር ሃይል ነበር፣ እንዲሁም ጽሑፎቹ፣ ተበታተነዉ በመሰራጨታቸዉ፣ ዓለምን ቀስቅሰዋል። አሁን ደግሞ ተመሳሳይ ተቋሞች በመቶ እጥፍ ከዘመኑ መገልገያዎች ጋር በእኛ ትዕዛዝ ውስጥ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱሶች፣ በብዙ ቋንቋዎች የተጻፉ የወቅቱን እውነት የሚገልጹ ጽሑፎች በእጃችን ናቸው፣ እንዲሁም በፍጥነት ወደ ዓለም ሁሉ ሊዳረሱም ይችላሉ።"—Testimonies for the Church, vol. 6, p. 403.

"ከሰማይ በታላቅ ኃይል የወረደው፣ በክብሩም ምድርን የሚያበራ የሌላ መልአክ ሥራ በማተሚያ ቤቶቻችን በከፍተኛ ደረጃ ይፈጸማል።"—Ibid., vol. 7, p. 140.

በ1849፣ ወንድም ጄምስ ኋይት የወቅቱ እውነት የተባለች ትንሽ ሕትመት አዘጋጀ። "ትንሽ የወረቀት ክምር መሬት ላይ ተዘርግታለች። ከዚያም ወንድሞች እና እህቶች በዙሪያው ተሰበሰቡና ዓይኖቻቸው እንባ እያቀረሩ ትንሿን የወረቀት ክምር ወደ ውጭ ሀገራት ለመላክ እግዚአብሔር እንዲባርክላቸዉ ለመኑ። ከዚያም ወረቀቶቹ ታጥፈው፣ ተጠቀልለውና የሚላኩበት አድራሻ ተደረገላቸዉ፣ እና ጄምስ ኋይት ወደ 13 ኪሎ ሜትር ገደማ መንገድ ወደ ሚድልታውን ፖስታ ቤት ተሸክሞ ሄደ።"—Early Writings, (xxv)

ይህ ድርጊት ፡ "'ትንሽ ወረቀት አትመህ ለሰዎች ላክ። መጀመሪያ ላይ ትንሽ ይሁን፤ ነገር ግን ሰዎቹ ሲያነቡ፣ ተጨማሪ የምታትምበትን ገንዘብ ይልኩልሃል፣ እናም ሥራዉ ከመጀመሪያውም የተሳካ ይሆናል" ለምለዉ መልእክት ምላሽ ነበር። Ibid., (xxiv)

የማጓጓዣ ወጪዎች ሲጨምሩና የድንበር ገደብ ቀረጦች የበለጠ ውድ የሆኑ የስርጭት ዓይነቶችን እንድንጠቀም ሲያስገድዱን ምን እናደርጋለን? እኛ የምናስከፍለዉ ሕሳብ ዋጋ እነዚህን አዲስ ወጪዎች አይጨምርም። እንግዲያው ለመጀመሪዉ አታሚዉ "ሰዎቹ ሲያነቡ ገንዘብ ይልኩልሃል" ተብሎ የተነገረለት ትንቢት ለመፈጸም የእምነት ባልንጀሮቻችን ደግነት ላይ ልንደገፍ ግድ ብሎናል።

የወቅቱን እውነት ማንበብ ለሚፈልጉ በዓለም ዙሪያ ላሉ ነፍሳት ተጨማሪ ለመስጠት ለጂሲ የስነ-ጽሁፍ ክፍል ይህ የመጀመሪያ ሰንበት ስጦታ በለጋስነት እንድትሰጡ ልባችሁ እንዲነካ እንጸልያለን። እናመሰግናለን!

ወንድሞቻችሁ ከጄነራል ኮንፌረንስ ሥነ ጽሑፍ ክፍል

**5ኛ ትምህርት　　　　　　ሰንበት፣ ጥቅምት 23፣ 2017**

# አድልዎን ማሸነፍ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና።" (ሮሜ 2፡11)።**

"እግዚአብሔር የማዕረግ ልዩነትን አያውቅም። ከእርሱ ዘንድ ምንም የዘር ልዩነት የለም። በእሱ እይታ ሰዎች በቀላሉ ጥሩም ይሁኑ መጥፎ ሰዎች ናቸው። በመጨረሻው የፍርድ ቀን፣ ሹመት፣ ማዕረግ፣ ወይም ሀብት የማንንም ጉዳይ የፀጉር ቅንጣት ያህል ለውጥ አያመጣም። ሁሉን በሚያየው አምላክ ፊት፣ ሰዎች በቅድስናቸዉ፣ በባሕርያቸዉና፣ በክርስቶስ ባላቸው ፍቅር ይፈረዳሉ።"—Counsels on Stewardship, p. 162.

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, **vol. 3, pp. 304–309, 320–329.**

እሁድ　　　　　　　　　　　　　　ጥቅምት 17

## 1. የአመለካከት ችግር

### ሀ. ምናልባትም ሳናውቅ ጥፋተኛ ልንሆን የምንችልበትን የተለመደ ምድራዊ ዝንባሌን ግለጽ። ያዕቆብ 2፡1-4

"ድሆች እንደ ሀብታሞች ብዙ ፍላጎት እና ትኩረት ሊደረግላቸው ይገባል። ሀብታሞችን ማክበር ደግሞ ድሆችን ማቃለል እና ችላ ማለት በእግዚአብሔር ፊት ወንጀል ነው። በሁሉም የሕይወት ምቾቶች የተከበቡ ወይም በዓለማችን ሀብታም በመሆናቸው የተማረኩ እና የሚንከባከቧቸው፣ ሕይወታቸው ከድህነት ጋር ለረጅም ጊዜ ሲታገሉ ለኖሩት ሰዎች ርኅራኄ እና ፍቅር እንደሚያስፈልጋቸው አይሰማቸውም። —Testimonies for the Church, vol. 4, p. 551.

"ክርስቶስ በሰማያዊ አደባባዮች ሀብታም ቢሆንም እኛ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች እንድንሆን ድሃ ሆነ። የሱስ የእነርሱን ዉርደታቸዉን በመካፈል ድሆችን አክብሯል። ከህይወቱ ታሪክ ድሆችን እንዴት መያዝ እንዳለብን መማር አለብን።"—Ibid., p. 550.

### ለ. በዚህ ዓለም ዝባዝንኬ ድሆች ስለሆኑ ነገር ግን በእምነት የበለጸጉ ሰዎችን በተመለከተ ምን ማስተዋል አለብን? ያእቆብ 2፡5

## 2. ማስተዋል እና ፍትሃዊነት

### ሀ. የሱስ ድሆችን በመርዳት ረገድ ያስተማረውን ሚዛናዊ አቀራረብ ግለጽ። ማርቆስ 14:3-9

*"አንዳንዶች የበጎ አድራጎት ግዴታን እስከ ጽንፍ በመሸከም ችግረኞችን ከልክ በላይ በመርዳት እንርሱን ይጎዳሉ። ድሆች ሁል ጊዜ እንደ ሚገባቸው አይተጉም። ችላ ተብለው እንዲሰቃዩ እና እንዲሰቃዩ ባይደረግም፣ እራሳቸውን እንዲረዱ መሥራትን መማር አለባቸው።*

*"ድሆች የመጀመሪያ ትኩረታችንን እንዲያገኙ ሲባል የእግዚአብሔር ጉዳይ ቸል ሊባል አይገባም። ክርስቶስ በአንድ ወቅት በዚህ ነጥብ ላይ ለደቀ መዛሙርቱ በጣም ጠቃሚ ትምህርት ሰጥቷቸዋል። ማርያም ሽቱ በየሱስ ራስ ላይ ባፈሰሰች ጊዜ፣ ስግብግብ የሆነው ይሁዳ፣ ገንዘብ ማባከን ነው ብሎ በሚቆጥረው ነገር እያጉረመረመ በድሆች ስም ተማጸነ። የሱስ ግን "ለምን ታስጨንቋታላችሁ? በእኔ ላይ መልካም ነገር ነዉ ያደረገችዉ። ይህ ወንጌል በአለም ሁሉ በሚሰበክበት በማናቸውም ስፍራ እርስዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ይነገራል። በዚህ የተማርነው ክርስቶስ ከሀብታችን ምርጡን በመቀደስ እንዲከበር እንደሚያስፈልግ ነው። ትኩረታችን የድሆችን ችግር ለመቅረፍ ከሆነ የእግዚአብሔር ጉዳይ ችላ ይባል ይሆናል። መጋቢዎቹ ኃላፊነታቸውን ከተወጡ በሁለቱም በኩል ችግር አይኖርም፤ ነገር ግን የክርስቶስ ጉዳይ መቅደም አለበት።"*—Testimonies for the Church, vol. 4, pp. 550, 551.

### ለ. በጥንቷ እስራኤል ፍትሕን ከሚሰጡ ሰዎች ምን ዓይነት ዝንባሌ ይጠበቅባቸው ነበር? ዘሌዋውያን 19:15፤ ዘዳግም 1:17፤ 10፡17።

### ሐ. ዛሬ፣ በየትኛውም የቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ ያሉ ሁሉ ይህንኑ መርህ ተግባራዊ ለማድረግ እንዴት መማር አለባቸው? 1ኛ ጴጥሮስ 1:17፤ ቆላስይስ 3፡25

*"ፍቅራቸውን እና ፍላጎታቸውን ከአንድ ወይም ከሁለት ጋር የሚያቀራኙ እና እነርሱን ለመርዳት ሲሉ ሌሎችን ለጉዳት የሚያደርጉ ሰዎች በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ለአንድም ቀን እንኪዋን መቆየት የለባቸውም። ይህ ያልተቀደሰ አድሎአዊ ፍላጎቱን ለሚያስደስቱ ልዩ ሰዎችን ለማስደሰት ሲሉ፣ ሌሎችን ህሊና እና ፈሪሃ አምላክ ያላቸውን ችላ ማለታቸው በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው። እግዚአብሄር ዋጋ የሚሰጠውን እኛም ዋጋ ልንሰጠው ይገባል። እግዚአብሔር የዋህነትንና ጸጥ ያለ መንፈስን ጌጥ፤ ከውጫዊ ውበት፣ ከውጫዊ ጌጥ፣ ከሀብት ወይም ከዓለማዊ ክብር ከፍ ያለ ዋጋ እንዳለዉ አድርጎ ይመለከታል።"*—Ibid., vol. 3, p. 24.

## 3. የተሻሉ ልማዶችን መፍጠር

### ሀ. ያዕቆብ አማኝ ነን የሚሉ ሰዎች በቁሳዊ ነገሮች ላይ ስለሚያሳዩት ዝንባሌ ምን ተግሣጽ ሰጥቷል— ይህስ አሳሳቢ ጉዳይ የሆነውስ ለምንድን ነው? ያእቆብ 2:6፣ 7

*"እግዚአብሔር በሰውና በመላእክት ፊት እንደ ልጁ አድርጎ አውቆሃል። የተጠራችሁበትን መልካም ስም እንዳታዋርዱ ጸልዩ። ያእቆብ 2:7 እግዚአብሔር ወኪሉ አድርጎ ወደ አለም ይልክሃል። በማንኛውም የሕይወት እንቅስቃሴ የእግዚአብሔርን ስም መወከል አለብህ። ይህ ተማጽኖ የእርሱን ባህሪ እንድትይዙ ይጠይቃችኋል። በህይወት እና በባህሪው የእግዚአብሔርን ህይወት እና ባህሪ እስካልወክሉ ድረስ ስሙን ልታስቀድሱት አትችሉም፣ እርሱን ለዓለም ልትወክሉት አትችሉም። ይህን ማድረግ የምትችለው የክርስቶስን ጸጋና ጽድቅ በመቀበል ብቻ ነው።"*—Thoughts From the Mount of Blessing, p. 107.

### ለ. ክርስቶስን በትክክል በመወከል አሸናፊ መሆን የምንችለው እንዴት ነው? ሮሜ 2:11፤ ምሳሌ 23:7

*"የመለኮትንና የሰውን ባሕርይ በጥንቃቄ አጥኑ፣ እና ዘወትር፣ 'የሱስ በእኔ ምትክ ቢሆን ምን ያደርግ ነበር?' በሉ። ይህ የእኛ ግዴታ የኛ መለኪያ መሆን አለበት። እራሳችሁን በኪነ ጥበባቸው ትክክል ለማድረግ አላማችሁን በሚያዳክሙ ወይም በህሊናችሁ ላይ እድፍ በሚያመጡ ሰዎች ማህበር ውስጥ አላስፈላጊ በሆነ መልኩ ራሳችሁን አታስቀምጡ። ከማያውቋቸው ሰዎች መካከል፣ በመንገድ፣ በመኪኖች፣ በቤት ውስጥ በትንሹም ቢሆን የክፋት መልክ ያለዉን ምንም ነገር አታድርጉ። ክርስቶስ በገዛ ደሙ የዋጃትን ሕይወት ለማሻሻል፣ ለማስዋብ እና ለማሳደግ በየቀኑ አንድ ነገር ያድርጉ።*

*"ሁልጊዜ በመርህ እንጂ በሥሜት ፈጽሞ ምንም ነገር አትሥራ። ተፈጥሮአዊ ችኩልነትህን፣ የዋህነትንና ርህራሄን በመለማመድ ግራዉ። በማይረባ ወይም ተራ ነገሮች ዉስጥ አትግባ። ተራ ንግግሮች ከከንፈሮችህ እንዳያመልጡ ተጠንቀቅ። በሀሳብህ እንኳን ጸብ ቀስቃሽ ነገር እንዲመጣብህ አትፍቀድለት። ሀሳብህ ለክርስቶስ በመታዘዝ ምርኮ ስር መሆን አለበት። በተቀደሱ ነገሮች ላይ አሰላስል። ያኔ ሀሳቦችህ፣ በክርስቶስ ጸጋ፣ ንፁህና እውነተኛ ይሆናሉ።*

*"የንጹህ አስተሳሰቦች የሚያበረታ ኃይል የማያቋርጥ ግንዛቤ ያስፈልገናል። ለማንኛውም ነፍስ፣ ደህንነት የሚገኝበት ብቸኛው መንገድ ትክክለኛ አስተሳሰብ ነው። . . .*

*"ስለሌሎች መልካም የመናገርን ልማድ አዳብር። በምትወዳቸው ሰዎች መልካም ባሕርያት ላይ አትኩር፤ በተቻለ መጠን ስህተታቸውንና ጉድለታቸዉን ላለመመለከት ሞክር።"*—The Ministry of Healing, pp. 491, 492.

## 4. ንጉሳዊ ባህሪይ ባለቤት መሆን

### ሀ. ቅዱሳት መጻሕፍት ለክርስቲያናዊ እምነታችን በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ የሚያጎሉት ምንድር ነው—ለምንስ? ያእቆብ 2፡8።

*"ብዙ ኃይማኖታዊ አስተማሪዎች ክርስቶስ በሞቱ ሕጉን እንደሻረውና በዚህም ምክንያት ሰዎች ከመጠይቁ ነፃ እንደሆኑ አስረግጠው ይናገራሉ። አንዳንዶች ከባድ ቀንበር እንደሆነ በማመልከት፣ ከሕጉ ባርነት በተቃራኒ በወንጌሉ ስር ሊጣጣም የሚገባውን ነፃነት ያስተምራሉ።*

*ነብያትና ሐዋርያት ግን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ በእንዲህ ሁኔታ አላዩትም ነበር። ዳዊት እንዲህ አለ፦ "ትእዛዛትህን ፈልጌያለሁና አስፍቼ [በነፃነት] እሄዳለሁ*/And I will walk at liberty for I seek thy precepts" [*መዝ* 119÷45]*። ከክርስቶስ ሞት በኋላ የፃፈው ሐዋርያው ያዕቆብ ስለ አሥርቱ ትዕዛዛት ሲናገር፦ "የንጉሥ ሕግ እንዲሁም ነፃ የሚያወጣውን ፍፁሙን ሕግ" በማለት ይገልፀዋል* [*ያዕ* 2÷8፤1÷25]*። ከስቅለት ግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላ፣ ምስጢር ገላጩ [ክርስቶስ] "ትዕዛዛቱን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው ስልጣናቸው በሕይወት ዛፍ ላይ ይሆን ዘንድ በደጅም ወደ ከተማ ይገባሉ"* [*ራዕ* 22÷14] *በማለት በረከትን ያውጅላቸዋል።"*—The Great Controversy, p. 466.

*"አንድ ሰው ለክርስቶስ ሲሰጥ አእምሮ በህግ ቁጥጥር ስር ይሆናል፤ ነገር ግን ሕጉለታሰሩት ሁሉ ነጻነትን የሚያውጅ የንጉሣዊ ሕግ ነው። ሰው ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን ነፃ ወጥቷል። ለክርስቶስ ፈቃድ መገዛት ፍጹም ወደሆነዉ ሰውነት መመለስ ማለት ነው።*

*"እግዚአብሔርን መታዘዝ ከኃጢአት ቀዉስ፣ ከሰበአዊ መነሳሳት እና ስሜት ነጻ መውጣት ነው። ሰው ራሱን የሚያሸንፍ፣ የራሱን ዝንባሌ የሚያሸንፍ፣ አለቅነትንና ሥልጣኖችን እንዲሁም 'የዚህን የጨለማ ዓለም ገዥዎች' እንዲሁም 'በከፍታ ቦታዎች ያሉ መንፈሳዊ ክፋቶችን' ድል አድርጎ ሊቀም ይችላል። ኤፌሶን* 6:12*።"*—The Ministry of Healing, p. 131.

### ለ. አድሎአዊነት፣ ማዳላት፣ እና/ወይም ጭፍን ጥላቻ ስለክርስቶስ ያለንን ምስክርነት በከባድ ሁኔታ የሚያበላሸው እንዴት ነው? ያእቆብ 2፡9

*"የክርስቶስ ተከታዮች ነን ልንል እንችላለን፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለውን እውነት ሁሉ እናምናለን እንል ይሆናል። ነገር ግን እምነታችን በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ እስካልገባ ድረስ ይህ ለባለእንጀሮቻችን ምንም አይጠቅምም። የእኛ አገልግሎት የሰማይ ያህል ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ክርስቲያን ካልሆንን በቀር ራሳችንንም ሆነ ወንድሞቻችንን አያድንም። ትክክለኛ የሕይወት ምሳሌነት ከአገልግሎታችን ሁሉ የበለጠ ዓለምን ይጠቅማል።"*—Christ's Object Lessons, p. 383.

## 5. በርኅራኄ ውስጥ የሚገኝ የጥበብ ትምህርት

### ሀ. እኛ ራሳችን የአምላክን የሥነ ምግባር ሕግ ስንጠብቅና ይህን እውነት ለቀጣዩ ትውልድ ስናካፍል ምን ማስታወስ አለብን? መክብብ 11:9፤ 12:13፣ 14፤ ያዕቆብ 2፡10-13

*"ወጣቶች አብሯቸው የሚወለድ ነፃ የመሆን ፍቅር በውስጣቸው አለ። ነፃነትን ይፈልጋሉ። እናም ከነዚህ ለግምት በሚያስቸግሩ በረከቶች ለመደሰት የሚቻለው የእግዚአብሔርን ሕግ ስንታዘዝ ብቻ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋቸዋል። ይህ ሕግ የእውነተኛ አርነትና ነፃነት ዐቃቢ ነው። የሚያዋርደውንና ባሪያ የሚያደርገውን ነገር ያመለክታል። ከእሱም ይከላከላል። እናም ታዛዥ ለሆነው ሰው ከክፉው ኃይል ይጠብቀዋል ይከላከልለታል። ባለመዝሙሩ እንዲህ ይላል፡ ፡ ‹‹ትዕዛዝህን ፈልጌአለሁና አስፍቼ እሄዳለሁ።›› ‹‹ምስክርህም ተድላየ ነው ሥርዓትህም መካሪየ ነው።›› መዝ* 119፡ 24፣45

*ክፋውን ለማስተካከል በምናደርገው ጥረት ስህተት ወይም ግድፈት ፈላጊ የመሆንን አዝማሚያ መከላከል አለብን። ዘወትር ጥፋትን ብቻ መከታተል የበለጠ ያሳስታል እንጅ አያቀናም። ብዙ ጊዜ እጅግ ድንቅ ሐሳብ ያላቸው በቀላሉ ስሜታዊ የሚሆኑ ሰዎች ጥረታቸው ሁሉ ርህራሄ በሌለው ትችት ላይ የመውደቅ ዕድል ያጋጥመዋል። አበቦች ለኃይለኛ አውሎ ነፋስ መጋለጥ አይችሉምና።* . . .

*እውነተኛ የተግሳጽ ዓላማ የሚገኘው ስህተት ፈፃሚው ራሱ ጥፋቱን እንዲያይ ሲደረግና ፍላጎቱም ለእርምት ዝግጁ ሲሆን ብቻ ነው። ይኸንን ሲፈጽም የይቅርታና የኃይል ምንጭ ወደሆነው አመልክቱት። እርሱም የሚሰጠውን ራስ ማክበርን እንዲጠብቅና በድፍረት በተስፋ ይሞላ ዘንድ እሹ።*

*ይህ ሥራ ለሰው ከተሰጠው ግዳጅ ከሁሉም የበለጠ የሚያምር እጅግ ከባድም ነው። እጅግ ድንቅ የሆነ የዋህነት ስለሰው ተፈጥሮ ባለው እውቀት ከሰማይ የመጣውን እውቀትና ትዕግሥት፤ ለማስተዋልና ለመጠበቅ እጅግ ውስብስብ የሆነ ዘዴ ይጠይቃል። ወደር የማይገኝለት አስፈላጊ ነገር ነው። — ትምህርት ገጽ* 291, 292



## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. ብዙ ባይኖረኝም ትንሽ እንኳ ስለሌላቸው ስለሌሎች ምን ማስተዋል አለብኝ?

2. በአንዳንድ ሰዎች ላይ ጭፍን አድልዎ ወይም ፍትሃዊ ያልሆነ ጭፍን ጥላቻ ማድረግ ምን ያህል ቀላል ነው?

3. አስተሳሰባችን እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች በምንይዝበት መንገድ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?

4. የእግዚአብሔር ሕግ የነጻነት ሕግ ተብሎ የሚጠራው ለምንድን ነው?

5. የተሳሳተ አስተሳሰብ ያላቸውን ሰዎች በማስተማር ረገድ ያለውን አመለካከት ግለጽ።

**6ኛ ትምህርት** **ሰንበት፣ ጥቅምት 30፣ 2017**

## እምነት በተግባር

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? (ያእቆብ 2፡20)**

*"መልካም ሥራ አንዲትን ነፍስ እንኳ ባያድንም፣ ያለ መልካም ሥራ አንዲት ነፍስ ግን ማዳን አይቻልም።"*—Faith and Works, p. 111.

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Early Writings, **pp. 226–228, 269–273.**

እሁድ **ጥቅምት 24**

### 1. እምነት እና ምሳሌ

**ሀ. ከምንናገረው እምነት ጋር ሙሉ በሙሉ ተስማምቶ መኖር በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? 1ኛ ቆሮንቶስ 4:9፤ 1ኛ ዮሐንስ 5:3፤ ያእቆብ 2፡14**

*ሆን ብለው የአምላክን መሥፈርቶች እየጣሱ ቅዱሳን ሊሆኑ እንደሚችሉ በማመን ራሳቸውን አያታልሉ። እያወቁ ኃጢአት መሥራት የመንፈስን ምሥክርነት ድምፅ ጸጥ ያደርገዋል እንዲሁም ነፍስን ከእግዚአብሔር ይለያል።"*—The Great Controversy, p. 472.

*"የአንድ ሰው የሕይወት ምስክርነት ለሚመሰክረው እምነት ታማኝ መሆን አለመሆኑን ለዓለም ይናገራል። ምግባራችሁ በዓለማዊ ጓደኞችህ ግምት የእግዚአብሔርን ህግ ዋጋ ይቀንሳል። ለእነሱ እንዲህ የሚል መልዕክት ያስተላልፍላቸዋል:- 'ትእዛዛትን መታዘዝም ወይም አለመታዘዝም ይቻላል። የእግዚአብሔር ህግ በሰዎች ላይ አስገዳጅ የሚሆንበት ሁኔታ እንዳለ አምናለሁ፤ ነገር ግን፣ ከሁሉም በላይ፣ ጌታ ትእዛዛቱን በጥብቅ እንድንታዘዝ ቀራጥ ግዴታ አላስቀመጠም፣ ስለዚህ አልፎ አልፎ የሚፈጸም መተላለፍን እርሱ አክብዶ አይመለከተዉም።'*

*"ብዙዎች የአንተን ምሳሌ በመጥቀስ ሰንበትን ስለጣሱ ለራሳቸው ሰበብ ያቀርባሉ። ሰባተኛው ቀን ሰንበት ነው ብሎ የሚያምን መልካም ሰው ሁኔታዎቹ አስቸጋሪ በሚመስልበት ቀን ዓለማዊ ሥራ መሥራት ከቻለ፣ ሌሎቹም ያለምንም ኩነኔ ያንኑ ማድረግ እንደሚችሉ ይከራከራሉ። ብዙ ነፍሳት ለእግዚአብሔር ህግ አለመታዘዛቸው ምክንያት የአንተ ተጽእኖ ሰበብ እንደሆነ በመግለጽ ከአንተ ጋር በፍርድ ቀን ፊት ለፊት ይጋፈጣሉ። ምንም እንኳን ይህ ለኃጢአታቸው ይቅርታ ባያሰጥም በአንተ ላይ ግን በሚያስፈራ ሁኔታ ይነገራል።"*—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 250.

## 2. ሰማይና ምድር እየተመለከቱ ነው

### ሀ. ያዕቆብ ከድርጊት የለሌዉ ባዶ ንግግር ግብዝነት ለማሳየት ምን ምሳሌ ሰጥቷል? ያዕቆብ 2፡15-17

"*በአሥርቱ ትእዛዛት ሕግ ላይ ሊሰበክ የሚችለው እጅግ አስደናቂ ስብከት እነርሱን በሕይወታችን በመታዘዝ ተግባራዊ ማድረግ ነዉ። ይህም የግል ግዴታ መሆን አለበት። የዚህ ግዴታ ቸልተኝነት ግልጽ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ለራሳችን መንግሥተ ሰማያትን እንድናገኝ ብቻ ሳይሆን መንገዱን ለሌሎች ማሳየት እና በእኛ እንክብካቤ እና ራስ ወዳድነት በሌለዉ ፍቅራችን፣ በተጽእኖአችን ክልል ውስጥ የሚመጡትን ወደ ክርስቶስ መምራት አስገዳጅ ግዴታ እንደሆነ እንዲሰማን እግዚአብሄር በነዚህ ግዴታዎች ውስጥ ያስቀምጠናል። የብዙ ክርስቲያን ነን ባዮችን ሕይወት የሚያመለክት መርህ አለመኖሩ አሳሳቢ ነው። የአምላክን ሕግ ችላ ማለታቸው የተቀደሰ የይገባኛል ጥያቄዎቹን የሚገነዘቡትን ሰዎች ያሳዝናል፤ እንዲሁም ይህን ሕግ አዲስ የሚቀበሉትን ከእውነት እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል።*"—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 58. [Author's emphasis.]

### ለ. በክርስቶስ ላይ ያለ እውነተኛ እምነት ማለት ምን ማለት ነው? ያዕቆብ 2:18፤ ማቴዎስ 6፡24

"*እግዚአብሔር ተናግሯል፣ እናም ይህ ማለት ደግሞ ሰው መታዘዝ አለበት ማለት ነው። ይህን ለማድረግ የሚመች እንደሆነ አይጠይቅም። የሕይወትና የክብር ጌታ ሰውን ካለመታዘዝ መዘዝ ለማዳን ውርደትንና ሞትን ተቀብሎ የሐዘን ሰው ሆኖ ከኃዘን ጋር የተዋወቀው የሥልጣን ቦታውን ለቆ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ምቾቱንና ተድላውን አልጠየቀምና። የሱስ የሞተው ሰውን በኃጢአቱ ለማዳን ሳይሆን ከኃጢአቱ ለማዳን ነው። ሰው የስህተት መንገዱን ትቶ የክርስቶስን አርአያ በመከተል መስቀሉን ተሸክሞ እርሱን በመከተል ራሱን በመካድ በምንም ዋጋ እግዚአብሔርን መታዘዝ አለበት።* . . .

"*እውነተኛ የአምላክ አገልጋዮች ከሆንን ትእዛዛቱን እንደምንታዘዝ ወይም የራሳችንን ጊዜያዊ ጥቅም እንደምናስከብር በአእምሮአችን ውስጥ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሊኖር አይገባም። በዚህ በአንጻራዊነት ሰላማዊ በሆኑ ጊዜያት ውስጥ በእውነት ውስጥ ያሉ አማኞች በእምነታቸው ካልጸኑ፣ ታላቁ ፈተና ሲመጣና የአውሬውን ምስል በማይሰግዱና ምልክቱን ግንባራቸዉ ወይም በእጃቸው በማይቀበሉ ሁሉ ላይ አዋጁ ሲወጣ ምን ይሆናሉ? ይህ ታላቅ ጊዜ ሩቅ አይደለም። የአምላክ ሕዝቦች ደካማና ተስፋ ቢስ ከመሆን ይልቅ በችግር ጊዜ ብርታትንና ድፍረትን ማሰባሰብ ይኖርባቸዋል።*"—Ibid., pp. 250, 251. [Author's emphasis.]

## 3. ከአብርሃም መማር

### ሀ. በጥብቅ ማስጠንቀቂያ የተሰጠን ስለ የትኛው መንፈሳዊ ሁኔታ ነው? ያእቆብ 2፡19

*የአለም አዳኝ እንደሆነ አምነዋል ፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ራሳቸውን ከእርሱ ያርቃሉ፣ እናም ከኃጢአታቸው ንስሐ ስለማይገቡ፣ የሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው መቀበል ተስኗቸዋል። የእነሱ እምነት በቀላሉ የአዕምሮ ስምምነት እና ለእውነት መፍረድ ነው፤ እውነት ግን ነፍስን እንዲቀድስና ባሕርይን እንዲለውጥ ወደ ልብ ውስጥ አይገባም።*”—Selected Messages, bk. 1, pp. 389, 390.

“*እውነትን ሁሉ ታምኑ ይሆናል፤ ሆኖም የእሱ መርሆዎች በህይወታችሁ ውስጥ ተግባራዊ ካላደረጋችሁ እምነታችሁ አያድናችሁም። ሰይጣን አምኖ ይንቀጠቀጣል። ሥራዉንም ይሰራል። ዘመኑ አጭር እንደሆነ ያውቃል እናም እንደ እምነቱ ክፉ ስራውን ለመስራት በታላቅ ሀይል ወርዷል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ነን የሚሉ ሰዎች ግን እምነታቸውን በሥራ አይደግፉም። ጊዜዉ አጭር እንደሆነ ያምናሉ፣ ነገር ግን ዓለም አሁን ባለበት ሁኔታ ለሺህ ዓመትታ የሚቀይ ያህል የዚህን ዓለም መዝገብ ለማከማቸት በጉጉት ይሯሯጣሉ።*”—Testimonies for the Church, vol. 2, p. 161.

### ለ. በአብርሃም ምሳሌ መነሳሳት የምንችለው እንዴት ነው? ሮሜ 4:1-3፤ ያዕቆብ 2፡20-22

“*አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ። ማመኑን እንዴት እናውቃለን*? *ሥራውም የእምነቱን ባሕርይ ይመሰክራል፣ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት።*”

“*በዘመናችንየእግዚአብሔርን ፍቅር ጣፋጭ ብርሃን ለመሸፈን እና መንፈሳዊ እድገትን ድንክዬ ለማድረግ በዙሪያችን የሚሰበሰበውን ጨለማ ለማብራት የአብርሃም እምነት ያስፈልገናል። . . . እያንዳንዱ የተከናወነው ተግባር፣ በየሱስ ስም የሚከፈል መስዋዕትነት ሁሉ እጅግ የላቀ ሽልማት ያስገኛል። ሰዉ ግዴታውን በሚወጣበት ጊዜ አምላክ ይናገራል እንዲሁም ይባርካል።*”—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 936.

“*ሰዎች በእምነት ይጸድቃሉ፣ ነገር ግን የሚፈረድባቸውና የሚሸለሙት እንደ ሥራቸው ነው።*”—The Signs of the Times, November 20, 1884.

“*የክርስቶስ ጽድቅ በትክክለኛ ሥራ እና ከንጹሕ እንዲሁም ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ ውስጣዊ ግፊት የሚገኝ መልካም ሥራዎችን ያካትታል።*”—Testimonies for the Church, vol. 3, p. 528.

“*የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ማክበር ከእኛ የሚፈልገው መልካም ስራን፣ ራስን መካድ፣ ራስን መስዋዕትነትን እና ለሌሎች መልካም ለማድረግ መስዋዕት መሆንን የሚጠይቅ ነው፤ መልካም ስራችን ብቻ ሊያድነን አይችልም ነገር ግን ያለ መልካም ስራ በእርግጠኝነት መዳን እንደማንችል ግልጽ ነው። ማድረግ የምንችለውን ሁሉ ካደረግን በኋላ ማለት ያለብን፡- “ግዴታችን ብቻ ነዉ የተወጣነዉ ፣ ከእግዚአብሄር ዘንድ ትንሽ ዉለታ እንኳን የማይገባን የማንጠቅም አገልጋዮች ነን” ነዉ። ክርስቶስ ጽድቃችንና የደስታችን አክሊል ሊሆን ይገባዋል።*”—Ibid., p. 526.

## 4. የማበረታቻ ቃላት

### ሀ. የአብርሃም ሕይወት ምሳሌ በእኛ በክርስቶስ አማኞች በራሳችን ሕይወት ውስጥ እንዴት መንጸባረቅ እንዳለበት አስረዳ። ዘፍጥረት 26:5፤ ያእቆብ 2:23፣ 24

"*መልካም ሥራዎች የእምነት ፍሬዎች ናቸው። እግዚአብሔር በልቡ ሲሠራ፣ ሰውም ፈቃዱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሲሰጥ፣ እና ከእግዚአብሔር ጋር ሲተባበር፣ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ የሚሠራውን በሕይወቱ ይሠራል፣ በልቡ ዓላማና በሕይወቱ ሥራ ልምምድ መካከልም ስምምነት ይኖራል። እያንዳንዱን ኃጢአት የሕይወትና የክብር ጌታን እንደ ሰቀለው ክፉ ነገር አድርገዉ መጸየፍ አለበት፣ እናም አማኙ የክርስቶስን ሥራዎች ያለማቋረጥ በመሥራት ተራማጅ ልምድ ሊኖረው ይገባል። ቀጣይነት ባለው የፈቃድ እጅ በመስጠት፣ በማያቋርጥ መታዘዝና፣ የፅድቅ በረከት የሚቀየው።*

"*በእምነት የሚጸድቁ የጌታን መንገድ የሚጠብቅ ልብ ሊኖራቸው ይገባል። ሰው ሥራው ከእምነቱ ጋር በማይጣጣምበት ጊዜ በእምነቱ እንደማይጸድቅ ማስረጃ ነው። ያዕቀብ 'እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፥ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን*? (*ያእቀብ* 2፡22)

"*መልካም ሥራ የማያደርግ እምነት ነፍስን አያጸድቅም።*"—Selected Messages, bk. 1, p. 397.

### ለ. በዛሬው ጊዜ ለአረማውያን የሚመሰክሩ ሁሉ አምላክ ያጸደቃት ጋለሞታይቱ ረዓብ መጠቀሷ ሊያበረታታ የሚችለው እንዴት ነው? ያዕቆብ 2:25፤ ዕብራውያን 11፡31

"*በክፉዋ ኢያሪኮ የአሕዛብ ሴት ምስክርነት፡- አምላክህ እግዚአብሔር እርሱ በላይ በሰማይ በታችም በምድር አምላክ ነው። ኢያሱ* 2፡11 *በዚህ መንገድ የመጣላት የአምላክ እውቀት መዳንዋን አረጋግጧል። . . . እሷም መመለሷ አምላክ መለኮታዊ ሥልጣኑን ለተቀበሉ ጣዖት አምላኪዎች የነበሩ ቢሆኑም እንኳን ያለውን ምሕረት የሚያሳይ ነበር።*"—Prophets and Kings, p. 369.

*ሞዓባዊቷ እንደ ሩት ከጣዖት አምልኮ ወደ እውነተኛው አምላክ አምልኮ የተመለሱ ሁሉ ከተመረጠው ሕዝብ ጋር ራሳቸውን አንድ ማድረግ ነበረባቸው።*"—Christ's Object Lessons, p. 290.

"*ታላቅ ሥራ በከተሞቻችን ይሠራል፤ እርሻውም ሁሉ መከሩ ደርቋል። በክርስቲያንም ሆነ በአረማውያን አገሮች ያሉ ንስሐ የገቡ ነፍሳት ለእርዳታ ድምጻቸውን ያሰሙ ዘንድ ትኩረታችን በሁሉም አቅጣጫ ይጠራሉ። ራስን ከፍ ከፍ የምናደርግበት አንድት ቅንጣት ነገር እንኳ መኖር የለበትም፤ ደህንነታችን በአምላክ በመታመን ብቻ ነውና።*"—The General Conference Bulletin, April 1, 1895.

ሐሙስ ጥቅምት 28

## 5. የድል ቁልፎች

## ሀ. በክርስቶስ ድል እንዴት እንደምንሆን አስረዳ። ያዕቆብ 2:26፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1:3፣ 4

“በየሱስ ማመን እና በእርሱ መዳናችሁን ማመን አስፈላጊ ነው። ዳሩ ግን ብዙዎች ‘ድኛለሁ’ ብለው የሚወስዱትን አቋም መያዝ አደጋ አለው። ብዙዎች:- “መልካም ሥራን አድርግ በሕይወትም ትኖራለህ” ይላሉ፤ ነገር ግን ከክርስቶስ በቀር ማንም መልካምን ማድረግ አይችልም። በአሁኑ ጊዜ ብዙዎች ‘እመኑ፣ ብቻ እመኑና ኑሩ’ ይላሉ። እምነት እና ስራ አብረው ይሄዳሉ፣ ማመን እና መስራት የተዋሃዱ ናቸው። ጌታ አሁን አዳም ከመውደቁ በፊት በገነት ውስጥ ከጠየቀው ያነሰ ነገር ከእኛ ነፍስ አይፈልግም - እሱም ፍጹም ታዛዥነትንና እንከን የለሽ ጽድቅ ነዉ። በጸጋው ቃል ኪዳን ስር ያለው የእግዚአብሔር መስፈርት ልክ በገነት ውስጥ እንዳደረገው መስፈርት ሰፊ ነው—ቅዱስ፣ ጻድቅ እና መልካም ከሆነው ከህጉ ጋር የሚስማማ። . . . ማንም ሰው፣ ምንም እምነት ቢኖረውም፣ ሕይወት የቱንም ያህል ፍጹም ባይሆንም እግዚአብሔር ቅንነትን ይቀበላል በሚል የተፈጥሮ ልብን ደስ በሚያሰኝ ማታለል አይወሰድ። እግዚአብሔር ከልጆቹ ፍጹም ታዛዥነትን ይፈልጋል።

“የሕግ መስፈርቶችን ለማሟላት በእምነት የክርስቶስን ጽድቅ እንደ ጽድቃችን መቀበል አለብን። ከክርስቶስ ጋር በመተባበር፣ በእምነት ጽድቁን በመቀበል፣ የእግዚአብሔርን ስራ ለመስራት፣ ከክርስቶስ ጋር ተባባሪዎች ለመሆን ብቁ እንሆናለን። ከክፋው ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ለመንገድ ፍቃደኛ ከሆናችሁ እና ዘላለማዊ ጽድቅ እንዲመጣ ዘንድ ከሰማያዊ ወኪሎች ጋር በቤተሰብዎ እና በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ያለውን በደል ለመከልከል ካልተባበራችሁ፣ እምነት የላችሁም ማለት ነዉ። እምነት የሚሠራው በፍቅር ነው ነፍስንም ያነጻል። በእምነት መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ቅድስና ለመፍጠር በልብ ይሠራል፤ ነገር ግን ይህ የሰው ወኪል ከክርስቶስ ጋር ካልሰራ በስተቀር ማድረግ አይቻልም። . . . የክርስቶስ ጽድቅ እንዲኖረን በየዕለቱ በመንፈስ ተጽዕኖ መለወጥና የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንድንሆን ያስፈልገናል።”—Selected Messages, bk. 1, pp. 373, 374.

አርብ ጥቅምት 29

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. የአምላክን ሕግ እንደምጠብቅ ሰዉ ስለ ተጽዕኖዬ ምን መገንዘብ አለብኝ?
2. ሰማይ ከክርስቲያን አማኞች ምን ይፈልጋል?
3. አብርሃም ብዙ ጊዜ የአማኞች አባት ተብሎ የሚጠራው ለምንድን ነው?
4. ከማውቃቸው ሰዎች መካከል፣ የተለወጠችው ረዓብ ማን ሊሆን ይችላል?
5. የድል አድራጊ ክርስቲያናዊ ልምድን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

## 7ኛ ትምህርት ሰንበት፣ ህዳር 07፣ 2017

## *አፋችንን ከመክፈት በፊት መጸለይ*

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "አስተምሩኝ፥ እኔም ዝም እላለሁ፤ የተሳሳትሁትንም ንገሩኝ።" (ኢዮብ 6፡24)።**

*"በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር እርሱ ፍጹም ሰው ነው ሥጋንም ሁሉ ደግሞ ሊገታ ይችላል። በመንገዳችን ላይ የሚያበራው ብርሃን፣ ለህሊናችን የምናገረዉ እውነት ራሱ ነፍሳችንን ያወግዛትና ያጠፋታል፣ ወይም ይቀድሳትና ይለውጣታል። የምንኖረው በአማክሮ ጊዜ መገባደጃ ላይ ሲሆን በአጉል የታይታ ሥራ ለመርካት ተገቢ አይደለም።"*—Testimonies for the Church, vol. 1, p. 308.

**ለንባብ የተመረጡት መጽሐፍት**፡ Testimonies for the Church, **vol. 2, pp. 50–55, 314–318; vol. 5**, **pp. 55–59, 175–177.**

እሁድ ህዳር 01

### 1. የእኛን የበላይ የመሆንን ጉጉት ማረጋጋት

### ሀ. ሁልጊዜ ሌሎችን ለመቆጣጠር የሚጣደፉ ሰዎች ምን ማስታወስ አለባቸው? ያዕቆብ 3:1፤ ማርቆስ 9፡35።

*"አምላክ በነፍሳችን ላይ ለምኖረው ተጽዕኖ፣ በራሳችንም ሆነ በሌሎች ሰዎች ጉዳዮች ላይ ለሚደርሰው ተጽዕኖ እያንዳንዱን ሰው ተጠያቂ ያደርጋል።"*—Counsels to Parents, Teachers, and Students, p. 102.

*"በተፈጥሮ የሰው ልጅ በራሱ ላይ ያተኮረ አመለካከት ያለው ነው። ክርስቶስ ሊያስተምራቸው የሚፈልገውን ትምህርት ከሚማሩ ሰዎች ሕይወት ግን ራስ ወዳድነት ይጠፋል። የመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች ይሆናሉ፣ ክርስቶስም በእነርሱ ይኖራል። ሁሉንም ሰዎች ተመሳሳይ ምኞት፣ ችሎታዎች፣ ፈተናዎችና ችግሮች፣ ርህራሄንና እርዳታ የሚያስፈልጋቸዉ እንደ ወንድማማቾች አድርገዉ ይመለከቷቸዋል።*

*"ባልንጀራን በፍፁምአናዋርድ። ስሕተቶችን ስናይ የራሳችንን ልምድ በመንገር የተሳሳቱትን ለመርዳት የተቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን - ከባድ ስህተቶችን በሠራን ጊዜ በሥራ ባልደረቦቻችን የተደረገልንን፣ ትዕግስትና ህብረት፣ ደግነትና እርዳታ፣ እንዴት ድፍረትና ተስፋ እንደሰጡን ልናካፍላቸዉ ይገባል።"*—The Signs of the Times, May 11, 1904.

## 2. የተሻለ አመለካከትን ማዳበር

### ሀ. የራሳቸውን ስህተት ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የተነሳ በሌሎች ላይ ጨካኝ ለሆኑ ሰዎች ምን ዓይነት ስለታም ተግሣጽ ተሰጥቷቸዋል? መክብብ 7:20፤ ያዕቆብ 3፡2 (የመጀመሪያው ክፍል)።

*"የራሳችሁን ጉድለት ለይታችሁ የጽድቅን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ አይገባችሁምን? እግዚአብሄር እንዳይዋረድ እና እውነት በስህተት እንዳይገለጽ እናንተ በሌሎች መንፈስ ላይ እንደምትሆኑ በራሳችሁ መንፈስ፣ ስሜትና ቃላቶች ላይ ንቁ ተቺ አትሁኑምን? ይህን ብታደርጉ ማስተዋላችሁ በእጅጉ ይሻሻላል። እውነት፣ ሕያው ቃል፣ ግልጽ በሆነ፣ በማያሻማ ልዩነት፣ በአጥንታችሁ ውስጥ እንደተዳፈነ እሳት ረመጥ እያቃጠለ ክርስቶስን ለዓለም በመወከል ይታያል። . . .*

*"ራሳቸውን መርማሪ ካደረጉት መካከል አንዳቸውም የቁጥጥር ሥልጣንን የወሰዱበትን ቦታ ዝንባሌ ማየት አልቻሉም? የጠራ መንፈሳዊ እይታቸው የት ነበር? በገዛ ዓይናቸው ውስጥ ምሰሶ ሳለ በወንድም ዓይን ያለውን ጉድፍ ለምን ማስተዋል ቻሉ?"*— Testimonies to Ministers, pp. 295, 296.

### ለ. አንድ ሰው የሞራል ፍጽምና ደረጃ ላይ እንደደረሰ የሚያሳየው ምንድን ነው - እና ይህ እንዴት ብቻ ሊሆን ይችላል? ያእቆብ 3:2፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡5 (ሁለተኛ አጋማሽ)።

*"የማይታዘዝ ምላስ ርኩስ ሥራውን ለመሥራት ሥፍራ በሚያገኝበት ቦታ የጌታ ደስታ ጸንቶ ሊቆይ አይችልም።*

*"በወንድሞቻቸው ላይ ክፉ የሚያስቡና የሚናገሩ ተጠራጣሪዎች የዲያብሎስን በትር ይዘዉ እየሰሩ መሆናቸውን ያስታውሱ። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል በትጋትና በጸሎት እርዳታ የዚያ የታመመውን አባል፣ አንደበትን ለመፈወስ ይሥራ። እያንዳንዱ ሰው ጥቃቅን ልዩነቶችንና ስህተቶችን ያለ ተቋዋሞ ማሳለፍ የእርሱ ግዴታና ልዩ መብት እንደሆነ ይሰማው። አንድ ሰው የሠራውን ጥቃቅን ስሕተቶችን አታጉላ ፣ ነገር ግን በእርሱ ያለውን መልካም ነገር አስብ። እነዚህ ስህተቶች በሚታሰቡበትና በተነገሩ ቁጥር እየጨመሩ ይሄዳሉ። ተራራ የሚሆነው ከትንሽ ኮረብታ ነው። መጥፎ ስሜትና አለመተማመን ውጤቱ ነው።"*—Australasian Union Conference Record, April 15, 1903.

*"ቃልህን እንድትጠብቅ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ግባ። "በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር እርሱ ፍጹም ሰው ነው ሥጋንም ሁሉ ደግሞ ሊገታ ይችላል።" ያእቆብ 3፡2 ያስታውሱ የበቀል ንግግር አንድ ሰው ድል እንዳገኘ እንዲሰማው በጭራሽ አያደርገውም። ክርስቶስ የእናንተ ፋንታ ይናገር። ክፋትን ባለማሰብ የሚገኘውን በረከት እንዳታጣ።"*—Testimonies for the Church, vol. 7, p. 243.

## 3. የሚጀምረው ከሥሩ ነው።

### ሀ. ቂም ስንይዝ የሚከተለውን የተሳሳተ አቅጣጫ ይከታተሉ እና ይህንን ለማስወገድ ብቸኛውን መንገድ ያብራሩ። ዕብራውያን 12:15፤ ያእቆብ 3:3-5

*"በባልሽና በበደሉሽ ሰዎች ላይ ቂምሽን ተንከባክበሽ፣ ነገር ግን የተሳሳትሽበትን ነገር ሳታስተውይ በራስሽ የተሳሳተ አካሄድ ጉዳዩን አባብሰሻል። ግፍ በፈጸሙብህ ሰዎች ላይ መንፈስህ መራራ ሆኖ፤ ስሜትህም ስድብና ዘለፋን እንድታወጣ አድርጎሃል። ይህ ሽክሙ ለከበደዉ ልብህ ጊዜያዊ እፎይታ ይሰጣል፣ ነገር ግን በነፍስህ ላይ ዘላቂ ጠባሳ ትቶልህ ያልፋል። ምላስ ትንሽ ብልት ነው፣ ነገር ግን አንተ የሚያቃጥል እሳት እስኪሆን ድረስ አላግባብ መጠቀምን አዳብረሃል።*

*"እነዚህ ሁሉ ነገሮች መንፈሳዊ እድገትህን የሚፈትሹ ሆነዋል። እግዚአብሔር ግን ታጋሽና ይቅር ባይ መሆን ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ያያልና እንዴት እንደሚራራና እንደሚረዳ ያውቃል። ህይወትህን እንድታስተካክል፣ ጉድለቶችህን እንድታስተካክል ይፈልግብሃል። ጽኑና የማይታክት መንፈስህ በጸጋው እንዲገዛ ይፈልጋል። ከሁከትና ከክርክር ይልቅ ሰላምና ጸጥታ ያስፈልጋሃልና የእግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ አለብህ። የክርስቶስ ሃይማኖት ከስሜታዊነት መንቀሳቀስን እንድትቀንስና የበለጠ በተቀደሰ ምክንያታዊነትና ከተረጋጋ ፍርድ እንድትንቀሳቀስ ያዛል።"*—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 139.

### ለ. ስለምንናገረው ቃል ምን ማስተዋል አለብን? ያእቆብ 3፡6

"*ቃሎችህ ይናገራሉ፣ ሥራህም መዝገብህ ያለበትን ያሳያል።*"—Ibid., vol. 1, pp. 698, 699

*"እህት ኤፍ በስሜታዊነት ተነስታ ትንቀሳቀሳለች፣ እናም ስህተት ታገኛለች፣ በዚህም በወንድሞቿና እህቶቿ ላይ ብዙ ነገር ትናገራለች። ይህ ደግሞ በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግራ መጋባትን ይፈጥራል።"*—Ibid., vol. 2, p. 51.

*በክርስቶስ አገልጋዮች ላይ የስድብና የሐሰት ቃላትን መፈለግ የሚወዱ እግዚአብሔር የሥራቸው ምስክር መሆኑን ያስታውሱ። የእነርሱ የስም ማጥፋት ንክኪ ነፍስ የሌላቸውን ግዑዝ ዕቃዎችን የሚያረክስ ሳይሆን ክርስቶስ በደሙ የገዛቸውን ሰዎች ባሕርይ የሚያረክስ ነውና። በብልጣሶር ቤተ መንግሥት ውስጥ በግድግዳዉ ላይ ቃላቶቹን የጻፈዉ እጅ በአምላክ ሕዝቦች ላይ የተፈጸመውን ማንኛውንም ኢፍትሐዊ ድርጊት ወይም ጭቆና በታማኝነት መዝግቧል።"*—Ibid., vol. 5, pp. 244, 245

## 4. እውነት ቢሆንም እንኳን . . .

## ሀ. በዘመናችን በአደገኛ ሁኔታ የተለመደ ዝንባሌን በተመለከተ ምን ጠንካራ ተማጽኖ ቀርቧል? መዝሙረ ዳዊት 15:1-3፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡6

"በክፋት ደስ የሚሰኝ አንደበት፣ ሪፖርት አድርጉ፣ እኔም እከሰዋለሁ የሚለው ምላስ፣ በሐዋርያው ያዕቆብ መልዕክት በገሃነም እሳት እንደሚቃጠል ተነግሯል። በእያንዳንዱ በኩል እሳትን ይተፋልና። የንጹሃንን ስም የሚያጠፋው ወሬ ሻጭ ምን ግድ አለው? በሸክማቸው ስር እየሰመጡ ያሉትን ተስፋና ድፍረት ቢያጠፋም ከክፉ ስራው አይታቀብም። እሱ የሚታትረዉ ቅሌት-አፍቃሪ ወይም ሀሜት ወዳድ ዝንባሌውን ለማስደሰት ብቻ ነው። ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎችም ቢሆኑ ንጹሕ፣ ሐቀኛ፣ ክቡር እና ተወዳጅ የሆኑትን ሁሉ ዓይኖቻቸውን ጨፍነው የሚቃወሙትንና የማይስማሙበትን ነገሮች ብቻ ቀጥበው ለዓለም አሳትመውታል።

"ሰይጣን እንዲገባ እናንተ ራሳችሁ በሮችን ከፍታችኋል። በምርመራችሁ ወይም በስብሰባችሁ ላይ የተከበረ ቦታ ሰጥታችሁታል። ነገር ግን በታማኝነት ለዓመታት ለገነባዉ ለባህርይዉ ልቀት ክብር አላሳያችሁም። ቀናተኛ፣ የበቀል ምላሶች ከራሳቸው ሃሳብ ጋር የሚስማማ ቀለም ያላቸው ድርጊቶችና ምክንያቶች አኗችሁና። ጥቁር ነጭ፣ ነጭ ጥቁር ሆኖ እንዲታይ አድርጋችዋል። አንዳንዶች በንግግራችሁ እንደገና ሲቃወሟችሁ የምንናገረዉ 'እውነት ነው' ትላላችሁ። የተናገራችሁ ነገር እውነት መሆኑን አምናችሁ መቀበላችሁ ብቻ አካሄዳችሁን ትክክል የሚያደርግ ይመስላችኋልን? አይ፣ አይሆንም። እግዚአብሔር በእውነት በአንተ ላይ ሊነሱ የሚችሉትን ውንጀላዎች ሁሉ ወስዶ አንተን ለቅጣት ጅራፍ አሳልፎ ቢሰጥህ ቁስልህ በወንድም ----- ላይ ካደረስከው የበለጠና ጥልቅ ይሆን ነበር። ምንም እንኳን እውነታዎች ቢሆኑም የተሳሳተ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ጥቅም ላይ ሊዉሉ ይችላሉ። በእሱ ላይ ማንኛውንም ዘገባ ለመሰብሰብና ስሙን ለማበላሸትና ተጽዕኖዉን ለማጥፋት ልትጠቀምበት መብት የለህም። ለወንድምህ ያሳየሄዉን መንፈስ ጌታ ለአንተ ቢያሳይ ያለ ርኅራኄ ትጠፋለህ። ሕሊና የለህምን? እንደዚያ ሳይሆን አይቀርምና ፈራሁ። ይህ ሰይጣናዊ ድግምት ኃይሉን የሚያጣበት ጊዜ ገና አልደረሰም። ወንድም ---- እንደዚያ እንዳልሆነ አዉቃለሁ፣ ግን አንተ እንዳልከዉ ሁሉ ቢሆንም እንኳ አካሄድህ አሁንም ፍትሃዊ አይሆንም ነበር።

"በወንድማችን ላይ የሚሰነዘረውን ነቀፋ ስንሰማ ያንን ነቀፋ እንቀበላለን። . . . (መዝሙር 15:1–3]"— Testimonies for the Church, vol. 5, pp. 57, 58.

## ለ. በጌታ ዘንድ አስጸያፊ ተብለው ከተጠቀሱት ሰባት ኃጢአቶች፣ ከአንደበታችን ጋር የተያያዙ ስንቶቹ ናቸው? ምሳሌ 6፡16-19

## 5. የሚያቆስል መሳሪያ

### ሀ. በጣም የተለመደውን የሃሜት ልማድ እንዴትና ለምን ማስወገድ አለብን? ኢዮብ 6:24፤ ምሳሌ 11:13፤ 26፡20–22።

"እያንዳንዱ ሰው የሌሎችን ስህተት የሚነግሩት ሰዎች ጥፋቱን ምቹ አጋጣሚ ሲያገኙ በተመሣሣይ ሁኔታ ለሌላ ሰዉ እንደምናገሩ ቢያስታውስ ሃሜት ምንኛ ይንኮታኮት ነበር። ስለእነርሱ በሌላ መልክ ከማሰባችን በፊት ስለሁሉም ሰው በተለይም ስለወንድሞቻችንን በደንብ ለማሰብ መጣር አለብን። ክፉ ዘገባዎችን በችኮላ መከበል የለብንም። እነዚህ ብዙውን ጊዜ የምቀኝነት ወይም አለመግባባት ውጤቶች ናቸው፣ ወይም እነሱ ከማጋነን ወይም ከፊል እውነታዎችን በመግለጽ ሊሆኑ ይችላሉ። ምቀኝነት እና ጥርጣሬ አንድ ቦታ ከተፈቀደላቸው በኋላ እራሳቸውን እንደ እሾህ ያሰራጫሉ። አንድ ወንድም ቢሳሳት ለእሱ ያለህን መልካም ፍላጎትህ የምታሳይበት ጊዜ ነው። በደግነት ወደ እርሱ ሂዱ ፣ ክርስቶስ ለቤዛነቱ የከፈለውን ወሰን የለሽ ዋጋ በማስታወስ ከእርሱ ጋር ጸልዩ። በዚህ መንገድ ነፍስን ከሞት ማዳንና የኃጢያትን ከማባዛት ማቆም ትችላላችሁ።

"ጥቅሻ፣ ቃል፣ የድምፅ ቃና፣ ለመዋሸት በጣም አስፈላጊ ሊሆኑ ይችላል፣ ልክ እንደ ጠንካራ ቀስት ወደ አንድ ልብ ውስጥ እየሰመጠ፣ የማይድን ቁስል ያመጣል። ስለዚህ እግዚአብሔር መልካም ሥራን በሚፈጽምበት ሰው ላይ ጥርጣሬ፣ ነቀፋ ሊወርድ ይችላል፣ እነዲሁም ተጽዕኖው ይጎዳል፣ ጥቅሙም ይጠፋል። ከአንዳንድ የእንስሳት ዝርያዎች ዉስጥ ከመካከላቸው አንዱ ቆስሎ ቢወድቅ ወዲያውኑ በባልንጀሮቹ ተዘልዝሎ ይዘነጠልና ይበላል። የክርስቲያን ስም በተሸከሙት ወንዶችና ሴቶችም ተመሳሳይ ጭካኔ የተሞላበት መንፈስ እየታየ ነው። ከራሳቸው ያነሰ ጥፋተኛ የሆኑትን ሌሎችን በድንጋይ ለመውገር የፈሪሳዊያንን ቅንዓት ያሳያሉ። የሌሎችን ስህተት የሚጠቁሙና ትኩረታቸውን ከራሳቸው ለማራቅ ወይም ለአምላክና ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ቅንዓት እንዳላቸው ለማስመሰል ይህን የሚያደርጉ አሉ።"—Testimonies for the Church, vol. 5, pp. 58, 59.

"ከስራ ፈት፣ ከንቱና ተንኮለኛ ወሬዎችን ለማዳመጥ የሚዉለዉ ጊዜ በከንቱ ከባከነዉ ይልቅ በጣም የከፋ ነዉና፤ ከፍ ያሉና ላቅ ላሉት ነገሮች ለማሰላሰል መሰጠት አለበት።"—Ibid., p. 176.



### የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. ስለ ሁሉም ነገር አስተያየት የመስጠት ዝንባሌን መቀነስ ማድረግ ያለብኝ ለምንድነዉ?

2. ብዙውን ጊዜ ችላ የሚባለዉን የክርስቶስን መሳይ ባሕርይ አንድ አስፈላጊ ገጽታ ጥቀስ።

3.የእምነት ባልንጀሮቻችንን በሌሎች ፊት ስናጎድፍ አምላክ እንዴት ይመለከተዋል?

4. ከመዝሙር ዳዊት ምዕራፍ 15 ምን መማር አለብኝ—ይህስ አስፈላጊ የሆነውስ ለምንድን ነው?

5. በወንድማማቾች መካከል ጠብ በመዝራት ጥፋተኛ መሆን የምችለው እንዴት ነዉ እንዲሁመ፣ ማቆም ያለብኝ ለምንድነዉ?

**8ኛ ትምህርት** **ሰንበት፣ ህዳር 14፣ 2017**

## *ስለ ምን ማሰብ እንዳለበን መምረጥ*

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና።” (ማቴዎስ 12:34፣ ሁለተኛ አጋማሽ)።**

*“ከመናገርህ በፊት ጸልይ፣ እና የሰማይ መላእክት ወደ አንተ ሊረዱህ ይመጣሉ፤ ያኔ እግዚአብሔርን የሚያዋርዱ፣ ዓላማውን የሚነቅፉና ነፍሳችሁን የሚያደክሙ ክፉ መላእክት ይሸሻሉ።”*—Testimonies for the Church, vol. 2, p. 82.

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ**፡ Thoughts From the Mount of Blessing, **pp. 125–129.**

እሁድ **ህዳር 08**

### 1. የመርዙ መከላከያ

### ሀ. ክፉ አስተሳሰብ ባላቸው ሰዎች የንግግር ልማዶች ስንዋጥ፣ በዚህ ሁሉ ውስጥ እንኳን የእግዚአብሔር መልእክት ምንድር ነው? ያእቆብ 3:7፣ 8፤ ዕብራውያን 10፡38

*“[ወንድም ጄ] በጨለማ የተከበበ ነውና በሰማያዊ መላእክት አዘኑ። ጆሮዎቹ ያለማመንና የጨለማ ቃላትን ያለማቋረጥ ይሰማሉ። ጥርጣሬዎች እና ጥያቄዎች በፊቱ ይመላለሳሉ። አንደበት የዓመፅ ዓለም ነው። “ምላስን ሊገራ ማንም አይችልም፤ የሚገድል መርዝ የሞላበት የማይታዘዝ ክፋት ነውና።” ወንድም ጄ ከአምላክ ጋር ይበልጥ አጥብቆ ከተጣበቀ እና በአምላክ ፊት ንጹሕ አቋሙን የተፈጥሮ ሕይወቱን መሥዋዕት በማድረግም ቢሆን መጠበቅ እንዳለበት የሚሰማው ከሆነ ከላይ ኃይልን ያገኛል። በዙሪያው ባለው ጨለማና አለማመን፣ በጥርጣሬዎችና በጥያቄዎች እንዲሁም በብዙ ወሬዎች እምነቱ እንዲነካ ከፈቀደ ብዙም ሳይቆይ ጨለማ፣ ጥርጣሬና አለማመን ይሆናል፣ እንዲሁም በእውነት ብርሃን የመጽናት ጥንካሬ አይኖረውም።*

*“በእምነታችን ላይ ከተበሳጩት ጓደኞቹ ጋር ለመስማማት በመፈለጉ ለእርሱ ቀላል ነገር እንደሆነ አድርጎ ማሰብ የለበትም። በማንኛውም ዋጋ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ አንድ ቀራጥ አላማ ይዞ ከቆመ እርዳታና ጥንካሬን ያገኛል። እግዚአብሔር ወንድም ጄን ይወደዋል፣ ይራራለታልም። ሁሉንም ግራ መጋባት፣ ተስፋ መቁረጥን፣ መራራ ንግግርን ያውቃል። ሁሉንም ያውቀዋል። አለማመኑን ትቶ ሳይነቃነቅ በአምላክ የሚቆም ከሆነ፣ እምነቱ በተግባር ይበረታል።”*—Testimonies for the Church, vol. 4, pp. 236, 237.

## 2. ከባድ ጉዳይ

### ሀ. ስለ አታላይና ቀስቃሽ ንግግሮች የተጻፈው ምንድን ነው—በዚህ የሕይወት ዘርፍ ለማሸነፍ መጸለይ ያለብን ለምንድን ነው? መዝሙረ ዳዊት 5:8-10

*"ንግግር እግዚአብሔር ለሰው ከሰጣቸው ታላላቅ ስጦታዎች አንዱ ነው። አንደበት ትንሽ ብልት ነው፣ ነገር ግን የሚቀርፃቸው፣ በድምፅ የተፈጠሩ ቃላቶች ትልቅ ኃይል አላቸው። እግዚአብሔር ምላስን ሊገራ ማንም አይችልም ይላል። ሕዝብን በሕዝብ ላይ ያስነሳል፣ ጦርነትና ደም መፋሰስንም ያስከትላል። ቃላቶች ለማርገብ የሚከብድ እሳት ይቀሰቅሳሉ። ለብዙ ነፍሳት ደግሞ ደስታንና እፎይታን አምጥተዋል። እንዲሁም እግዚአብሔር ' ቃሌን ንገራቸው' ስለሚል የእርሱ ቃላቶች ሲነገሩ ብዙ ጊዜ ሰዎችን ወደ ንስሃ ያመጣሉ።*

*"የንግግር መክሊት ትልቅ ኃላፊነት ሸክም ያለበት ነዉ። በጥንቃቄ መጠበቅ ያስፈልገዋል፤ ለክፉም ለበጎም ታላቅ ኃይል የያዘ ነውና።"*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 3, p. 1142.

*"የማይታዘዝ ብልትን ለመግራት ስትፈተን፣ ኦ እጅግ ከባድ ነዉ! መዝጋቢው መልአክ እያንዳንዱን ቃል እየተመለከተ መሆኑን አስታውስ። ሁሉም ነገር በመጽሐፍ ተጽፈዋል፣ እናም በክርስቶስ ደም ካልታጠበ በቀር፣ እነሱን እንደገና በፍርድ ቀን ታገኛቸዋለህ። አሁን በሰማይ ውስጥ እየታየ ያለ መዝገብ አለ። በእግዚአብሔር ፊት ልባዊ ንስሐ አሁንም ተቀባይነት አለዉ። በስሜታዊነት ለመናገር ሲገፋፋ፣ ላለመናገር አፍህን ዝጋዉ። አንድም ቃል አትናገር።"*—Testimonies for the Church, vol. 2, p. 82.

### ለ. ቃላቶቻችን በቀላሉ እኛ የምናስበውንና ማን እንደሆንን ማንነታችን እንዴት እንደሚያሳዩ ግለጽ። ኤርምያስ 17:9፤ ማቴዎስ 12:33–37፤ 14፡6–8።

*"የንግግርህ ጭብጥ የልብን ሀብት ወይም ሀሳብህን ያሳያል። ርካሽ፣ ተራ ወሬ፣ የማታለል ቃላት፣ የቂልነት ጥበብ፣ ሳቅ ለመፍጠር የሚነገሩ ተራ ንግግሮች፣ የሰይጣን ሸቀጣ ሸቀጥ ናቸው፣ በዚህ ንግግር የሚዋዋጥ ሁሉ በሸቀጦቹ እየነገደ ነው። ሄሮድስ የሄሮድያዳ ልጅ በፊቱ ስትጨፍር ከነበረው ጋር የሚመሳሰል ተራ ስሜት ነዉ እነዚህን ነገሮች ለሚሰሙ ሰዎች የሚሰማቸዉ። እነዚህ ሁሉ ግብይቶች በሰማዩ መዝገብ ውስጥ ተመዝግበዋል ፤ እናም በመጨረሻው ታላቅ ቀን በጥፋተኞች ፊት በእውነተኛ ብርሃን ግልጽ ሆነዉ ይታያሉ። በዚያን ጊዜ ሁሉ የዲያብሎስን አሳሳችና ክፉ ሥራ እነርሱን ወደ ሰፊው መንገድ ለጥፋትም ወደተከፈተው ሰፊው ደጅ ይመራቸዉ እንደነበረ ለይተው ያውቃሉ።"*—Testimonies to Ministers, pp. 84, 85.

## 3. በሙሉ ልብ ያስፈልጋል

### ሀ. በወቅቱ እውነት ውስጥ አማኞች የማይለዋወጥ ንግግር (የማያወላዉል አንደበት) እንድኖራቸዉ ለምን መጠበቅ አለብን? ያዕቆብ 3:9፣ 10 በዚህ ነጥብ ላይ ከወደቅን ምን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል?

*"እግዚአብሔር የምታደርጉትንና የምትናገሩትን ሁሉ እንደሚያይና እንደሚሰማ እንዲሁም ቃላቶቻችሁንና ተግባራችሁን ሁሉ በታማኝነት መዝግቦ እንደሚይዝ፣ በመጨረሻም ለፍርድ እንደሚያመጣዉ ካመናችሁና ሁሉንም መስፈርቶቹን ማሟላት እንዳለባችሁ የሚሰማችሁ ከሆነ፣ በምትሰሩትና በምትናገሩት ነገር ሁሉ በንቁና በበራ ሕሊና የአምላክን መመሪያዎችን ተከተሉ። በዚያን ጊዜ አንደበትህ ለእግዚአብሔር ክብር ጥቅም ላይ ይውላል፤ እንዲሁም ለራስህና ለሌሎች የበረከት ምንጭ ይሆናል። ነገር ግን እንዳደረጋችሁት ከእግዚአብሔር ከተለያችሁ፥ አንደበታችሁ የዓመጻ እንዳያደርግና የሚያስፈራ ፍርድ እንዳያመጣብህ ተጠንቀቅ። በአንተ ምክንያት ነፍሳት ይጠፋሉና።"*—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 244.

### ለ. ሁልጊዜ አስበን እንድንናገር የሚረዳን የትኛው ጸሎት ነው? መዝሙረ ዳዊት 86:11

*"የመጽሐፍ ቅዱስን እውቀት የሚቀበለው ሰው ከእውነት ብርሃን ጋር የሚመጣጠን በልማዱ ወይም በድርጊቶቹ ላይ ምንም ለውጥ ካላመጣ፣ ምን ዋጋ አለዉ? መንፈስ ከሥጋ ጋር ሥጋም ከመንፈስ ጋር ይዋጋል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ማሸነፍ አለበት። በእውነት ነፍስህ ከተቀደሰ ኃጢአትን ትጠላለህ፣ ምክንያቱም ክርስቶስ በልብህ እንደተከበረ እንግዳ ተቀባይነት አግኝቷልና። ክርስቶስ ግን የተከፋፈለን ልብ ከሌላ ጋር ሊጋራ አይችልም፤ ኃጢአትና የሱስ ፈጽሞ አጋር አይሆኑምና።"*—Testimonies to Ministers, p. 160.

*"ትጋ እና ሁል ጊዜ ጸልይ። ያለ እረፍት ራስህን ለጌታ ስጥ፣ ከዚያ በኋላ እሱን ማገልገል አስቸጋሪ አይሆንም። የተከፋፈለ ልብ አለህ። በብርሃን ፈንታ ጨለማ የሚከብብህም ለዚህ ነው። የመጨረሻው የምሕረት መልእክት አሁን እየታወጀ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ትዕግስትና ርህራሄ ምልክት ነው። ና ግብዣው አሁን ተሰጥቷል። ና ፣ ሁሉም ነገር አሁን ዝግጁ ነውና። ይህ የምሕረት የመጨረሻ ጥሪ ነው። ከዚህ ቀጥሎ በቅርቡ በአንተ ባሕርይ የተከፋዉ አምላክ በበቀል ይመጣልና።"*—Testimonies for the Church, vol. 2, p. 225.

*"አሁን ጸንተዉ የሚቆሙት በሙሉ ልብ፣ በሚገባ የወሰኑ ወንዶች እና ሴቶች ብቻ ናቸው። ክርስቶስ ተከታዮቹን ደጋግሞ ያነጥራል፣ በአንድ ወቅት የክርስቲያን ቤተክርስቲያንን መሰረት ለመጣል አስራ አንዶቹ እና ጥቂት ታማኝ ሴቶች ብቻ ቀርተዉ ነበር። ሸክም ሲመጣ ወደ ኋላ የሚቀሩ (ከኋላ የሚቆሙ) አሉ፤ ነገር ግን ቤተክርስቲያኑ በጋለ ጊዜ፣ ግለቱ ይይዛቸዋል፣ ይዘምራሉ፣ ይጮኻሉ፣ ይወራጫሉ፤ ነገር ግን ተመልከቷቸው። ስሜቱ ሲጠፋ ወይም ሲቀዘቅዝ ጥቂት ታማኝ ካሌቦች ብቻ ወደ ግንባር መጥተው የማይናወጥ አቋም ያሳያሉ። እነዚህ ጣዕሙን የያዙ ጨው ናቸው።"*—Ibid., vol. 5, p. 130.

## 4. ውሃ ከንጹህ ምንጭ

**ሀ. በእግዚአብሄር ፀጋ የታደሰ ልብ ብቻ ወጥ የሆነ ተግባር ማምጣት እንደሚችል የሚያሳየው የትኛው መርህ ነው? ያዕቆብ 3:11፣ 12 አንዳንድ ተግባራዊ ምሳሌዎችን ስጥ።**

*"ንጹህና ሥርዓት ያለዉ አለባበስ፣ እንዲሁም ንጽህና በሁሉም መኖሪያ ቤቶች፣ ሁልጊዜ በዚህ ምድር ላይ እንደ እንግዳ በሚታዩ እና ስህተታቸውን ለማየት በሚጠበቁ በሰንበት ጠባቂዎች በጥብቅ ሊጠበቁ ይገባል። የእነሱ ተጽዕኖ ቅዱስ መሆን አለበት። የምንላቸው ቅዱሳን እውነቶች ተቀባዮችን ፈጽሞ የሚያዋርዱ፣ እንዲሁም ሸካራ፣ ለግል ጉዳያቸው ቸልተኞችና በቤታቸው ውስጥ ያልተስተካከሉ አያደርጋቸዉም። ተቀባዩ ደካማ ልማዶች ካለው፣ እውነት ከፍ ታደርጋለች፣ በጥልቅ ተሐድሶ ይሠራል። እውነት ይህን ውጤት ካላመጣበት፣ ለግለሰቡ የማዳን ኃይሉ አልተሰማውም ማለት ነዉ። ጥንቃቄ የጎደለውና የተዘበራረቀ ልብስ የትህትና ምልክት አይደለም። በዚህም አንዳንዶች እራሳቸውን አታልለዋል። ህይወቱ፣ ድርጊቶቹ፣ ቃላቶቹ፣ ግለሰቡ እውነተኛ ትህትና እንዳለው ይነግራሉ፣ እና አለባበሱን ከተገለጹት ፍሬዎች ጋር ያዛምዳሉ። ንጹሕ ምንጭ በተመሣሣይ ጣፋጭና መራራን ውሃ አያወጣም። ምንጩን አጽዱና ፈሳሾቹ ንጹህ ይሆናሉ። የእግዚአብሔር ቤት ብዙ ጊዜ በሰንበት ጠባቂዎች ልጆች ይረከሳል። ወላጆቻቸው አምላክን ለማገልገል በተሰበሰቡባቸው ስብሰባዎች ላይ በቤቱ ዉስጥ እንዲሯሯጡ፣ እንዲጫወቱ፣ እንዲነጋገሩ፣ የሰዎችን ትኩረት እንዲስቡና አምላክን ለማምለክ በተሰበሰቡበት ሥፍራ ክፉ ተጽዕኖቻቸውን እንዲያሳርፉ ይፈቅዳሉ። በቅዱሳን ማኅበር ጸጥታ መንገሥ እነደሚገባዉ አይቻለሁ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሰዎች የሚሰበሰቡበት ቤት ብዙውን ጊዜ ፍጹም ባቢሎን ፣ የግራ መጋባትና የሥርዓት አልበኝነት ቦታ ይሆናል። ይህ እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል። ወላጆች በልጆቻቸዉ ላይ ሥልጣን ከሌላቸው፣ እና ልጆቻቸውን በስብሰባ ላይ መቆጣጠር ካልቻሉ፣ ከማይታዘዙ ልጆቻቸው ጋር በቤታቸው ቢቆዩ እግዚአብሔር ደስ ይለዋል። ብዙ ሰዎችን ከማናደድና ስብሰባዎቻቸውን ከማበላሸት ይልቅ ከስብሰባዉና ከበረከቱ ብቀሩ ይሻላቸዋል። ወላጆች ልጆቻቸውን ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑ አድርገዉ አሳድገዉ፣ ቤት ውስጥ ሳይቆጣጠሯቸዉ ከቀሩ፣ በስብሰባ ቦታ ላይ እንደፈለጉ ሊያዟቸዉ አይችሉም። በዚህ ጉዳይ የሚጎዱት ማን መሆን አለባቸው? በእርግጠኝነት፣ ወላጆች። አምላክን ለማምለክ በሚሰበሰቡበት ጊዜ ሌሎች ሰላማቸው እንዲረበሽ የማይፈልጉ ከሆነ ወላጆች ይሄ ሸክም ሊሰማቸው ይገባል።*

*"ወላጆች፣ በዚህ ጉዳይ የተነሳ እናንተ ልትሰቃዩ (ሊሰማችሁ) ይገባል፣ ምክንያቱም የተዘነጋችሁትን ግዴታ እንድትመለከቱና እንድትወጡ ያደርጋችኋልና። ልጆቻችሁን ተሸክማችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ከወሰዳችሁ፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝባቸው ቦታዎች መሆናቸውን እንዲረዱ ማድረግ አለባችሁ። በዚህ ረገድ በሰማዊ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንዳለ በሰንበት ጠባቂዎች ዘንድ እንዲህ ዓይነት ሥርዓት አልተፈጠረም። ወላጆች ሆይ፣ የምትሠሩት ሥራ አለላችሁ። ልጆቻችሁን በቤታችሁ አስገዙ፤ ከዚያም በአምላክ ቤት ውስጥ ልታስተዳድሩአቸው ትችላላችሁና።"*—Spiritual Gifts, vol. 2, pp. 288, 289.

ሐሙስ ህዳር 12

## 5. ጥበብና እውቀትን መላበስ

## ሀ. እያንዳንዳችን የራሳችንን አመለካከት ከውስጥ ወደ ውጭ ማለትም በልባችን፣ በቃላችንና በድርጊት መመርመር ያለብን ለምንድን ነው? 2ኛ ቆሮንቶስ 13፡5

"በእምነት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ። ራሳችሁን ፈትኑ" (2ኛ ቆሮንቶስ 13፡5)። ቁጣችሁን፣ አቋማችሁን፣ ሃሳባችሁን፣ ቃላታችሁን፣ ዝንባሌዎቻችሁን፣ ዓላማዎቻችሁን እና ድርጊቶቻችሁን በቅርበት ተቹ። የመንፈሳዊ ጤንነታችንን በቅዱሳን ጽሑፎች እስካልተረጋገጠ ድረስ የሚያስፈልገንን ነገር በጥበብ መጠየቅ የምንችለው እንዴት ነው?"—Selected Messages, bk. 1, p. 89

"ወንድሞቼና እህቶቼ፣ የንግግር መክሊትን እንዴት ነው የምትጠቀሙት? አንደበት ለበራ ህሊናና ለቅዱስ የፍቅር መመሪያዎች እንዲታዘዝ መቆጣጠርን አስተምረሃልን? ንግግርህ ከዝሙት፣ ከኩራትና ከክፋት፣ ከተንኮልና ከርኩሰት የጸዳ ነውን? በእግዚአብሔር ፊት ተንኰል የሌለብህ ነህን? ቃላቶች የመናገር ኃይል አላቸው። ሰይጣን ከተቻለ አንደበት ለራሱ ለአገልግሎቱ ንቁ እንዲሆን ያደርጋል። በራሳችን የማይታዘዝ ብልትን መቆጣጠር አንችልም። መለኮታዊ ጸጋ ብቸኛው ተስፋችን ነው።"—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 175.

"ራሱን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ያደረገ ሰዉ፣ አእምሮው እየሰፋና እየዳበረ ይሄዳል። እግዚአብሔርን የሚያገለግል ሰዉ የምማረዉ ትምህርት አንድ ወገን የሆነና ሚዛናዊነት የጎደለው፣ የአንድ ወገን ባሕርይን ብቻ የሚያዳብር ሳይሆን ነገር ግን የተመጣጠነና የተሟላ የሚያድርግ ትምህርት ያገኛል። በልፍስፍስ ፈቃድና አቅም በሌለው ባህሪይ ውስጥ የተገለጡ ድክመቶች ይሸነፋሉ፣ ምክንያቱም ቀጣይነት ያለው አምልኮ እና እግዚአብሔርን መምሰል ሰውን ከክርስቶስ ጋር ያለውን ቅርርብ በመያዝ የክርስቶስ አስተሳሰብ እንዲኖረው ያደርጋልና። ነገረ ሥራዉና የመርህ ጥንካሬዉ ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናል። የእሱ ግንዛቤ ግልጽ ነው፣ እናም ከአምላክ የሚገኘውን ጥበብ ይገልጣል።"—Selected Messages, bk. 1, p. 338.

አርብ ህዳር 13

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. መርዛማ የሆነ ንግግር ሲያጋጥመኝ ምላሽ መስጠት ያለብኝ እንዴት ነዉ?

2. ሰዎች ነገሮችን በሚናገሩበት ጊዜ፣ የሚናገሩት ነገር ስለእነሱ ምን ያመለክታል?

3. በሰው አእምሮ ውስጥ ያለውን ጦርነት እና እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻል አብራራ።

4. በውስጣችን ያለውን የተበከለዉን ውሃ የሚያንፀባርቁ ልማዶቼ/ዝንባሌዎቼ የትኞቹ ናቸው?

5. የአነጋገር ልማዴን መቀየር ያለብኝ እንዴትና ለምንድነዉ?

**9ኛ ትምህርት ሰንበት፣ ህዳር 21፣ 2017**

## የጥበብ የዋህነት

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አንዋዋሩ ስራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ።" ያዕቆብ 3፡13**

"*አዳኛችን ሰዎችን በንፁህነቱ እና ከፍ ባለ ስነ ምግባሩ ያስደንቃቸው፣ ደግሞ በፍቅሩና ደግነቱ እንደሱ ለመሆን እንድጓጉ አነሳስቷቸዋል። እጅግ ድሆችና የተዋረዱ እንኳን ወደ እርሱ ለመቅረብ አልፈሩም።*"—Gospel Workers (1892), p. 261.

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, **vol. 5, pp. 167–177.**

እሁድ ህዳር 15

### 1. ጠማማ "ማስተዋል"

### ሀ. ከየትኛው ከባድ ክፋት መጠንቀቅ አለብን— ለምንስ? ያእቆብ 3:14፣ 15

"*የጠላትን ሃሳብ ለመቀበል ልቡን የሚከፍት፣ ክፉ አስተሳሰብን የሚቀበልና ቅናትን የሚወድ፣ ይህን ክፉ አስተሳሰቡን አዘውትሮ በተሳሳተ መንገድ ይገነዘባል፣ ይህም ልዩ አርቆ አሳቢነት፣ አድልዎ፣ ወይም ጥፋተኛነትን ለመለየትና የሌሎችን መጥፎ ዓላማ ለመረዳት የሚያስችል ልዩ ማስተዋል ነዉ ይለዋል። አንድ ውድ ስጦታ ለእሱ እንደተሰጠውም አድርጎ ይቆጥረዋል፤ ተስማምቶ መኖር ከሚገባቸዉ ወንድሞቹም ይለያል፤ በፍርድ ወንበርም ላይ ወጥቶ እርሱ ራሱ ከፈተና ሁሉ የበላይ እንደሆነ አድርጎ ስሕተት የሥራ በመሰለዉ ሰው ላይ ልቡን ይዘጋል። ከእንደዚህ ዓይነት ሰዉ የሱስ ይለያል (ከእርሱ ጋር አይሆንም)፣ እናም በራሱ በገዛ ብርሃኑ ድንግዝግዝታ ውስጥ እንዲሄድ ይተወዋል።*

"*ይህ መንፈስ ኃጢአተኞችን በታማኝነት ለመገሰጽና ለእውነት ለመቆም የሚያስፈልግ ነገር እንደሆነ በመናገር ከእናንተ መካከል ማንም ቢሆን ይህን በማድረጉ ለእዉነት እንደቆመ በማሰብ ኩቶ አይመካ። እንዲህ ዓይነቱ ጥበብ ብዙ አድናቂዎች አሉት፣ ነገር ግን በጣም አታላይና ጎጂ ነው። ይህም ከላይ የመጣ ሳይሆን የያልታደሰ ልብ ፍሬ ነው። የዚህ ነገር መሠረቱ ራሱ ሰይጣን ነው። ማንም ከሳሽ ራሱን አስተዋይ አድርጎ አይቁጠር፤ እንደዚያ ካደረገ ይህንን የሰይጣንን ባሕርይ የማይገባዉን የጽድቅን ልብስ ያለብሰዋልና። ወንድሞቼ ሆይ፣ ከእነዚህ ከሚያረክሱት ነገሮች ሁሉ የነፍሳችሁን ቤተ መቅደስ ታነጹ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤ መራራ ሥር ናቸውና።*"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, pp. 936, 937.

## 2. መርዛማ ባህሪይ

### ሀ. የማይቀረውን የቅናት እና የጠብ ውጤት ይግለጹ። ያእቆብ 3፡ 16

*“በተቋም ውስጥ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በወንድሞች ላይ ክፉ ቃላትን በመናገር ደግነት የጎደላቸው ሐሳቦችን የሚረጭ ሰው፣ የሰበአዊን ልብ መጥፎ ስሜት ቀስቅሶ ከእርሱ ጋር በሚገናኙ ሁሉ ላይ የሚሰራን የክፋት እርሾ ሊዘራ ይችላል። በዚህ መንገድ የጽድቅ ሁሉ ጠላት ድልን ይቀዳጃል፣ የሥራው ውጤትም እርሱ ከአብ ጋር አንድ እንደሆነ ደቀ መዛሙርቱ አንድ እንዲሆኑ የተማፀነዉን የአዳኙን ጸሎት ከንቱ ማድረግ ነው።”*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 937.

### ለ. በነፍሳችን ጠላት ከተቀሰቀሰው የሰው ልጅ ዝንባሌ በተቃራኒ ከሌሎች ጋር እንዴት ልንገናኝ ይገባል? ዮሐንስ 13፡34

*“አቋማቸውን ወይም ስራቸውን ሳትረዳ ግን በመንገዶቻቸውና በአመለካከታቸው ላይ ትችት ትሰጣለህ፣ እንዲሁም በግለሰቦቹ ላይ ፍርድህን ትሰጣለህ። ነገሮችን በራስህ አመለካከት (ላንተ በሚታይህ በኩል ብቻ) ትመለከታለህ ከዚያም በሁሉም አቅጣጫ ጉዳዮችን በቅንነት ሳትመለከት እነርሱ የሚሄዱበትን አካሄድ ለመጠየቅ ወይም ለማውገዝ ዝግጁ ትሆናለህ። ስለሌሎች ወንድሞች ግዴታቸዉ (ስለስራቸዉ) ምንም የምታወቀዉ ነገር የለህም እንዲሁም ለድርጊታቸው ሀላፊነት ሊሰማህ አይገባም፣ ነገር ግን አንተ ግዴታህን ተወጣ፣ የቀረዉን ለጌታ አሳልፈህ ስጥ። መንፈስህን በትዕግስት ያዝ፣ ሰላምንና የአእምሮ መረጋጋትህን ጠብቅ፣ እንዲሁም አመስጋኝ ሁን።* . . .

*“በጣም ስሜታዊ ነህ፣ እንዲሁም አንተ ከምታስበዉ በተቃራኒ መንገድ ያለዉን ሀሳብ የሚደግፍ ቃል ከተነገረህ ትጎዳለህ። በዚህም እንደተከሰስክ ወይም እንደተወገዝህ ይሰማሃል፣ ስለዚህ ራስህን መከላከልና ህይወትህን ማዳን እንዳለብህ ይሰማሃል፤ በዚህም ራስህን ለማዳን በምታደርገዉ ጥረት በራስህ በርግጥም ነፍስህን ታጣለህ። ለራስህ ለመሞትና የመታገሥና የትዕግሥት መንፈስ ለማዳበር ሊትሰራዉ የሚገባ ሥራ ከፊትህ አለህ።”*—Testimonies for the Church, vol. 2, p. 424.

*“አንዳቸዉ አንዳቸዉን የሚተቹና የሚኮንኑ እነዚያ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እየጣሱ ነው፣ እርሱንም እያስቀጡ ናቸው። እግዚአብሔርንም ሆነ ባልንጀሮቻቸውን አይወዱም። ወንድሞችና እህቶች፣ ትችት፣ ጥርጣሬንና ቅሬታን እናስወግድ እንዲሁም ስሜቶቻችንን እንቆጣጠር። አንዳንዶቹ በጣም ስሜታዊ ከመሆናቸው የተነሳ ምክንያታዊ ሊሆኑ አይችሉም። የእግዚአብሄርን ህግ መጠበቅ ምን ማለት እንደሆነና ህግን እየጠበቅክ ወይም እየጣስክ ስለመሆንህ እርግጠኛ ለመሆን በጣም ንቁ ሁን። አምላክ እንድንጠነቀቅ የሚፈልገው ስለዚህ ጉዳይ ነው።”*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 937.

## 3. ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎችን ማስተናገድ

### ሀ. የአምላክን ሕግ ስለሚወዱ ሰዎች ምን ተጽፏል? መዝሙረ ዳዊት 119:165

*“የተያዝኩበት ሁኔታ ትክክል አይደለም (የሚገባኝን ክብር አላገኘሁም)፣ ተበድያለሁ፣ አንድ ሰው ሊያስጨንቀኝ ወይም ሊጎዳኝ ይፈልጋል ከሚለው ሃሳብ ውጣ። በስህተት ዓይን እያየህ ነህና። እነዚህን የተዛቡ ነገሮችን እንድትመለከት የሚመራህ ሰይጣን ነዉ።”*—Testimonies for the Church, vol. 2, p. 424.

*“ዓለም ኃጢአትን ይወዳል፣ እናም ጽድቅን ይጠላል፣ እናም ይህ በየሱስ ላይ ያሳዩት ጥላቻ ምክንያት ነበር። ወደር የሌለውን ፍቅሩን እምቢ ያሉ ሁሉ ክርስትናን የሚረብሻቸዉ ሆኖ ያገኙታል። የክርስቶስ ብርሃን ኃጢአታቸውን የሚሸፍነውን ጨለማ ጠራርጎ ያጠፋዋል፣ እንዲሁም መታደስ እንደሚያስፈልጋቸዉ ይገለጣል። የመንፈስ ቅዱስን ተጽዕኖ የሚቀበሉ ከራሳቸው ጋር ጦርነት ሲጀምሩ፣ ኃጢአትን የሙጥኝ ያሉ ግን ከእውነትና ከተወካዮቹ ጋር ይዋጋሉ።*

*“በዚህም ጠብ ይፈጠራል፣ እንዲሁም የክርስቶስ ተከታዮች ሕዝቡን የሚያስጨንቁ ተደርገው ይከሰሳሉ። ነገር ግን የአለምን ጠላትነት የሚያመጣባቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ህብረት ነው። የክርስቶስን ነቀፋ ተሸክመዋል። እነርሱ የምድር መኳንንት የናቁትን መንገድ እየሄዱ ነው። በሐዘን ሳይሆን በደስታ፣ ስደትን ይጋፈጣሉ። እያንዳንዱ እሳታማ ፈተና የሚያጠራ የእግዚአብሔር ወኪል ነው። እያንዳንዱ ፈተና ከእርሱ ጋር ተባባሪዎች ሆነዉ ለሚሠሩት ሥራ ገጣሚ ያደርጋቸዋል። እያንዳንዱ ግጭት ለጽድቅ በሚደረገው ታላቅ ጦርነት ውስጥ የራሱ ቦታ አለው፣ እንዲሁም ምንቀበላቸዉ እያንዳንዱ ፈተና የመጨረሻውን የድል ደስታን እጥፍ ድርብ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህን ግምት ውስጥ ስለሚያዉቁ እምነታቸውንና ትዕግሥታቸውን የሚፈትን ፈተና ከመፍራትና ከመራቅ ይልቅ በደስታ ይቀበላሉ።”*—The Desire of Ages, p. 306.

### ለ. ኢፍትሐዊ በሆነ መንገድ አንድ ነገር ሲፈጸምብንም ስለ ምን ነገር እናስታውሳለን? ማቴዎስ 5:11፣ 12፣ 41፤ 1ኛ ጴጥሮስ 4:12-15

*“መለኮታዊ የሆነዉ የቤተ ክርስቲያን ራስ፣ የድል አድራጊዎች ሁሉ ኃያላን የሆነው እርሱ ተከታዮቹን ወደ ህይወቱ፣ ድካሙ፣ ራስን መካድ፣ ተጋድሎውና መከራው፣ በንቀት፣ ተቀባይነት በማጣት፣ በመሳለቅ፣ በስድብ፣ በፌዝ፣ በውሸት፣ መካከል አልፎ በቀራንዮ መንገድ ወደ ስቅለቱ ቦታ እንደወጣና እንዳሸነፈ፣ እነርሱም በዚህ መንገድ እንድጓዙና ለአሸናፊው ወደሚሰጠዉ ሽልማትና ክብር ለመድረስ ይበረታቱ ዘንድ ወደ ሕይወቱ ያመላክታቸዋል። ድል የሚረጋገጠው ደግሞ በእምነትና በመታዘዝ ነው። የክርስቶስን ቃላት በግል ጉዳያችን ላይ እንተገብረው።”*—The Review and Herald, July 24, 1888.

## 4. ጥበብ ከላይ

### ሀ. የሰማዩ ጥበብ የመጀመሪያው ባሕርይ ምንድን ነው—ይህስ ለእኛ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ያዕቆብ 3:17 (የመጀመሪያ ክፍል)፤ ማቴዎስ 5፡8

*"ወደ እግዚአብሔር ከተማ የሚያረክስ ምንም ነገር አይገባም። እዚያ የሚኖሩ ሁሉ ልባቸው ንጹሕ ይሆናሉ። ስለ የሱስ በሚማር ሰው ውስጥ፣ ለግዴለሽነት ጠባይ፣ ጨዋነት ለጎደለው ንግግርና ጨዋነት ለጎደለው አስተሳሰብ ያለው ጥላቻ እየጨመረ ይሄዳል። ክርስቶስ በልቡ ሲኖር፣ ሁል ጊዜ የአስተሳሰብና የባሕርይ ንፅህናና ማሻሻያ ይኖራል።*

*"ነገር ግን 'ልበ ንጹሐን የሆኑ ብፁዓን ናቸው' የሚለው የየሱስ ቃላት ጥልቅ ትርጉም አላቸው—ዓለም ንጽሕናን በሚረዳበት መንገድ ንጹሕ ማለት ብቻ ሳይሆን ሥጋዊ ከሆነ ነገር የራቀ፣ ከሥጋ ምኞትም የጸዳ እንዲሁም የነፍሱ ዓላማዎችና ዝንባሌዎች፣ ከኩራትና ከራስ ብቁነት የጸዳ፣ ትሑት፣ ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ፣ እንደ ሕጻን ልጅ የሆነ የሚል ትርጉም ያላቸዉ ናቸዉ።"*— Thoughts From the Mount of Blessing, pp. 24, 25.

### ለ. ለክርስቶስ ስንዘጋጅ ትኩረታችን ምን መሆን እንዳለበት አስረዳ። 1ኛ ዮሐንስ 3:2፣ 3

*"በእለት ተእለት ልምዳችን [የእግዚአብሔርን] ቸርነትና ርህራሄን በሚያደርግልን እንክብካቤ እናስተውላለን። በልጁ ባህሪይ እናውቀዋለን። መንፈስ ቅዱስ ስለ እግዚአብ ሔርና ስለ እርሱ የላከውን እውነትን ወስዶ ለማስተዋልና ለልብ ይከፍታል። ልበ ንጹሐን እግዚአብሔርን እንደ አዳኛቸው በአዲስና በሚያምር ግንኙነት ያዩታል፤ እንዲሁም የባህሪውን ንጽህናና ፍቅር ሲያውቁ፣ የእርሱን መልክ ለማንፀባረቅ ይናፍቃሉ። እርሱን ንስሐ የገባ ልጁን ለማቀፍ እንደሚናፍቅ፣ አባት ያዩታል እናም ልባቸውም በማይነገር ደስታና በክብር ተሞልቷል።*

*"ልበ ንጹሕ የሆኑ ፈጣሪን በኃይሉ የእጁ ሥራ፣ በዓለማት ዉስጥ ባለ ውበት ይገነዘባሉ። በጽሑፍ በቃሉ ውስጥ የምሕረቱን፣ የቸርነቱንና የጸጋውን መገለጥ ይበልጥ ግልጽ በሆነ መስመር ያነባሉ። ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች የተሰወረው እውነት ለሕፃናት ይገለጣል። በዓለማዊ ጥበበኞች የማይታወቁ የእውነት ውበትና ክቡርነት፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅና ለመፈጸም ለሚታመኑ፣ እንደ ሕፃን ያለ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች በየጊዜው ይገለጣል። እኛ እራሳችን የመለኮታዊ ተፈጥሮ ተካፋዮች በመሆን እውነትን እንገነዘባለን።*

*"ልበ ንጹሕ የሆኑ በእግዚአብሔር ፊት በዚህ ዓለም ውስጥ በከፋፈላቸው ጊዜ ዉስጥ ልክ እንደ እግዚአብሔር መገኘት ሆነዉ ይኖራሉ።"*—Ibid., pp. 26, 27

ሐሙስ ህዳር 19

## 5. ተጨማሪ አስፈላጊ ባህሪያት

## ሀ. ከንጽህና ቀጥሎ፣ ያለእነሱ ተጽእኖዋቸን ዋጋ የሚያጣባቸዉ አምስት የሰማይ ጥበብ ባህሪያትን ጥቀስ። ያዕቆብ 3፡17 (መካከለኛው ክፍል)።

"የክርስቶስ ደግነት፣ ጨዋነት፣ የዋህነትና ትሕትና ያስፈልጋችኋል። ለእግዚአብሔር ከተቀደስህ ለከፍተኛ አገልግሎት ሊዉሉ የሚችሉ ብዙ ጠቃሚ ብቃቶች አሉህ። በጭካኔና በሸካራነት ሳይሆን በደግነትና በአክብሮት ወደ ወንድሞችህ የመቅረብ አስፈላጊነት ሊሰማህ ይገባል። በእነሱ ላይ የበላይነትህን ለማስጠበቅ ብለህ በሚታሳየዉ ሰል መንፈስ የምታደርስባቸዉን ጉዳት መጠኑን አታስተውልምና። በዩኒየናችሁ ውስጥ ያሉ አገልጋዮች ክብርን፣ ደግነትን፣ መተማመንንና ፍቅርን ብትሰጣቸው ኖሮ ለማገልገል ድፍረትን በማጣት ተስፋ አይቆርጡም ነበር። በአድራጎትህ የወንድሞችህን ልብ ከአንተ ለይተሃል፤ ምክርህ በእነሱ ላይ በጎ ተጽዕኖ እንዳያሳድርባቸው አድርገሃል።"—Christian Leadership, pp. 6, 7.

"የምትጠብቀው ነገር ካልተሳካ፣ ተስፋ መቁረጥና እረፍት ማጣት እንዲሁም ለውጥን በመመኘት አደጋ ላይ ትወድቃለህ። ለማንቋሸሽ፣ ለማዋረድ ዝንባሌን ማስወገድ አለቦት። የመውገዝ መንፈስ እንዲቀሰቀስ ከሚያደርግ ነገር ሁሉ ራቅ። ይህ መንፈስ በማንኛውም የረጅም ጊዜ ልምድ ባካበቱ አገልጋዮቹ ውስጥ መገኘቱ እግዚአብሔርን አያስደስተውም። ወጣቶች በትህትናና በቅንነት ከሆነ ዉስጣዊ ፍላጎትንና ቅንዓትን መግለጥ ተገቢ ነው። ነገር ግን የችኮላ ቅንዓትና የውግዘት መንፈስ ገና የጥቂት ዓመታት ልምድ ባላቸዉ ወጣቶች ላይ ሲገለጥ በጣም ጥሩ ያልሆነና አጸያፊ ነው። እንደዚህ ያለ ወዲያውኑ የወጣቱን ተጽዕኖ ሊያጠፋ የምችል ምንም ነገር የለም። የዋህነት፣ ርህራሄ፣ ትዕግስት፣ መቻል፣ በቀላሉ አለመበሳጨት፣ ሁሉንም መሸከም፣ ሁሉን ተስፋ ማድረግ፣ ሁሉንም ነገር መታገስ - እነዚህ ሰማያዊ በሆነው የፍቅር ዛፍ ላይ የሚያፈሩ ፍሬዎች ናቸው። ይህንን ዛፍ፣ ከተንከባከብን፣ ዘዉትር የማይጠወልግ አረንጓዴ ዛፍ ይሆናል። ቅርንጫፎቹ አይደርቁም፣ ቅጠሎቹም አይረግፉም። ያለማቋረጥ በሰማይ ጠል ስለሚጠጣ፣ የማይሞት፣ ዘላለማዊ ይሆናል።"—Testimonies for the Church, vol. 2, pp. 134, 135.

አርብ ህዳር 20

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. በየትኞቹ ሁኔታዎች ውስጥ ነዉ፣ መሻታቸዉን መጠራጠርና ብልሃት ነዉ ብዬ ለመጥራት የሚፈተነዉ?
2. ሌሎችን የመተቸት ልማድ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጥሰው እንዴት ነው?
3. ሰዉ መርዛማ የሆነ ባህሪይ በእኔ ላይ ሲያሳይ ምን ማስታወስ አለብኝ?
4. "በንጹሕ ልብ" መሆን ሲባል ምን ማለት ነው?
5. በቀላሉ የሚቀረብና 'ለመጠይቅ' ይበልጥ ቀለል ያልኩ ሰዉ መሆን የምችለው እንዴት ነው?

# የመጀመሪያ ሰንበት ለኮሎምቢያ ዩኒየን ዋና መሥሪያ ቤት

ኮሎምቢያ በደቡብ አሜሪካ የሚገኝ ሀገር ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ከ51 ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎች አሉት። ኢንዱስትሪዎች ነዳጅ፣ ማምረቻ፣ ጨርቃጨርቅ፣ ኮንስትራክሽን፣ ግብርና፣ ባንክና አገልግሎቶችን በማቅረብ ይታወቃል። ከሕዝቡ መካከል 73% ካቶሊኮች፣ 9.1% የክርስትና እምነት ተከታዮች ያልሆኑት ሲሆን፣ 6.9% ወንጌላውያን፣ 6.5% ሃይማኖት የሌላቸውም፣ 2.9% ፕሮቴስታንቶች፣ እና 0.9% አምላክ የለሽ እንደሆኑ ይናገራሉ። ይህ ሁኔታ እዚህ ላለችው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ትልቅ ፈተና እንዳለባት ያሳያል።

በ1960ዎቹ የሦስተኛው መልአክ መልእክት ኮሎምቢያ ደረሰ። በዚህ ግርግር መሃል ቤተክርስቲያኑ በይፋ በተመዘገበበት በ1971 ዓ.ም 100 ያህል አባላት ደርሰናል። በዚያን ጊዜ ሠራተኞቹ ጥቂት ነበሩ፣ ነገር ግን ለሚወዱት ዓላማ ሁሉንም ነገር ለመስጠት ድፍረትና ቅንዓት ነበራቸው። ሀገራቸውንና የምቾት ኑሯቸዉን ትተው በሙሉ ልባቸው በኮሎምቢያ ያለውን ስራ ለመደገፍና እዚህ መልእክቱን ለማሰራጨት በደስታ የመጡትን ፓስተሮችና አገልጋዮችን ላደረጉት ነገር ሁለም እናመሰግናለን።

በእግዚአብሔር ቸርነት በ2006 የኮሎምቢያ ህብረት የተደራጀ ሲሆን ዛሬ ሶስት ፊልዶች አሉት። የእኛ ዩኒየን ዋና መስሪያ ቤት በባርቦሳ፣ ሳንታንደር ማዘጋጃ ቤት ገጠራማ አካባቢ ይገኛል።

ወንድሞቻችንንና ለእውነት ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ለማገልገል በዛሬው ጊዜ ያሉትን አገልግሎቶች ማስፋፋት አስፈላጊ መሆኑን እናስተውላለን። በአሁኑ ጊዜ፣ ቢሮዎቻችን፣ ሚሲዮናዊ ትምህርት ቤቶቻችንና መልቲሚዲያ ክፍል የሚሰሩበት መሬት አለን። እዚህ ለአባሎቻችንና ለመልእክቱ ፍላጎት ላላቸው አዲስ ጉባኤዎች፣ ሴሚናሮችና መንፈሳዊ ጉዞዎችን (Retreats) እናስተናግዳለን።

የመሠረተ ልማት አውታሩ በከፊል በዚህ ንብረት ላይ ተገንብቷል፣ እና ተጨማሪ መገልገያዎች ግንባታ በአሁኑ ጊዜ በሂደት ላይ ናቸው፣ ነገር ግን እነሱን ለመጨረስ የሚያስችል ግብዓቶች ይጎድሉናል። ለዚያም ነው በዓለማችን ላሉ ሰፊ ቤተሰብ ለሆኑት ቤተ ክርስቲያናት ልግስና የምንለምነው። የልግስና ሥጦታችዎ ድጋፍ የጌታን እውቀት የተራቡ ነፍሳትን ለማገልገል የበለጠ ተስማሚ መገልገያዎች እንዲኖረን ያስችለናል።

የእርስዎን ልገሳ በጣም እናደንቃለን። የእርስዎ ልገሳና ስጦታዎች ምን ያህል መልካም ነገር እንዳደረጉ ማየት የሚቻለው በፍርዱ ቀን ብቻ ነው።

ወንድሞቻችሁ እና እህቶቻችሁ ከኮሎምቢያ ዩኒየን

## 10ኛ ትምህርት ሰንበት፣ ህዳር 28፣ 2017

## *የአመለካከት ችግሮቻችንን ማሸነፍ*

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል።" ያዕቆብ 4፡7**

*"ንጹሕ፣ የሚቀድስ እውነትንና ውዱ ቤዛችንን መውደድ፣ የአሸናፊነት ጉዟችንን ያቀልልናል።"*—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 38.

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, **vol. 3, pp. 39–47.**

እሁድ **ህዳር 22**

### 1. ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ፍትሃዊነት

### ሀ. የሰማይ ጥበብ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱትን የመጨረሻዎቹን ሁለት ባሕርያት ጥቀስ። ያዕቆብ 3፡17 (የመጨረሻው ክፍል)።

*"ሐዋርያው ይሁዳ 'ልዩነትን ሲታደርጉ፣ ለአንዳንዶች ርህራሄ አሳዩ' ብሏል። ይህ ልዩነት በአድሎአዊነት መንፈስ መተግበር የለበትም። 'ከደገፊከኝ እደግፍሃለሁ' ለሚል መንፈስ ምንም ዓይነት ቦታ መስጠት የለብንም። ይህ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ያልተቀደሰ፣ ዓለማዊ አካሄድ ነው። ለጥቅም ሲባል ሞገስንና አድናቆትን መክፈል (መስጠት) ነው። በእነሱ በኩል ጥቅማጥቅሞችን እንደምናገኝ በማሰብ ለተወሰኑ ሰዎች አድልዎ ማሳየት ነዉ። ከሌሎች ይልቅ እኛን የተሻልን ብቁ አድርገዉ እንዲመለከቱን በትጋት በመመላለስ የእነርሱን በጎ ፈቃድ መፈለግ ነው።"*—Testimonies for the Church, vol. 4, pp. 221, 222.

*"እግዚአብሔር በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በሚደረገው ስንፍና ሥራ ደስ አይለውም። ተግሣጽና እርማት ለመስጠት የእርሱ መጋቢዎች እውነተኛና ታማኝ እንዲሆኑ ይጠብቃል። ስህተትን ማስወገድ ያለባቸው እግዚአብሔር በቃሉ በሰጠው አካሄድ መሠረት ነው እንጂ እንደራሳቸው ሃሳብና ስሜት አይደለም። ጠንከር ያለ መንገድ መጠቀም የለባቸዉም፣ ፍትሃዊ ያልሆነ፣ በጥድፊያ፣ በስሜት ስራ መሠራት የለበትም። ቤተ ክርስቲያንን ከሥነ ምግባር ርኩሰት ለማንጻት የሚደረገው ጥረት በእግዚአብሔር መንገድ መከናወን አለበት። ወገንተኝነት፣ ግብዝነት መኖር የለበትም። ኃጢአታቸው ከሌሎች ሰዎች ኃጢአት ያነሰ ኃጢአት ተደርጎ የሚቆጠርላቸዉ ተወዳጆች ሊኖሩ አይገባም። ኦ፣ ሁላችንም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምን ያህል ያስፈልገናል? ያን ጊዜ በክርስቶስ አእምሮ፣ በደግነት፣ በርኅራኄና በሀዘኔታ፣ ኃጢአትን ፍጹም በሆነ ጥላቻ እየጠላን ለኃጢአተኛው ፍቅር በማሳየት እንሠራለን።"*—The Ellen G. White 1888 Materials, p. 144.

## 2. ክርስቶስን በትክክል መወከል

### ሀ. በንግግራችን ውስጥ ክርስቶስ ብቻ በትክክል መወከል የምንችለው እንዴት ነው? ያእቆብ 3፡18

"በከንፈራችን ክርስቶስን መመስከርና በስራችን ደግሞ እርሱን መካድ ይቻላል። በሕይወታችን የሚገለጡ የመንፈስ ፍሬዎች ስለክርስቶስ ይናገራሉ። ሁሉን ለክርስቶስ የተውን ከሆነ ሕይወታችን ትሑት፣ ንግግራችን ሰማያዊ፣ ምግባራችንም ነውር የለሽ ይሆናል። በነፍስ ውስጥ ያለው ኃይለኛ፣ የሚያነጻው የእውነት ተጽእኖ፣ እና የህይወት ውስጥ ምሳሌ የሆነው ክርስቶስ ባህሪይ፣ ስለእርሱ ይናገራሉ። የዘላለም ሕይወት ቃል በልባችን ውስጥ ከተዘራ ፍሬው ጽድቅና ሰላም ነው። ምቾትን ወይም ራስን በመውደድ፣ በማሾፍና በመቀለድ፣ እንዲሁም የአለምን ክብር በመሻት ክርስቶስን በህይወታችን ልንክደው እንችላለን። ከዓለም ጋር በመስማማት፣ በኩራት መልክ ወይም ውድ ልብስ በመልበስ በውጫዊ መልካችን ልንክደው እንችላለን። በሕይወታችን ውስጥ የክርስቶስን ባሕርይ ወይም የእውነትን የመቀደስ ተጽዕኖ ማሳየት የምንችለው በማያቋርጥ ነቅቶ በመጽናትና በማያቋርጥ ጸሎት ብቻ ነው። ብዙዎች ክርስቶስን ከቤተሰቦቻቸው ያባረሩት ትዕግስት በሌለው፣ በጋለ መንፈሳቸዉ ምክንያት ነው። በዚህ ረገድ እንዲህ ያሉት ነገሮች ሊያሸንፉት የሚገባቸዉ አሉ።"—Testimonies for the Church, vol. 1, pp. 303, 304.

### ለ. በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚረጩትን፣ የትኞቹን የተለመዱ የሰዉ ልጅ ዝንባሌዎችን ነዉ በእርግጥ ማሸነፍ ያለብን—ለምን? ያእቆብ 4:1-3

"በዙሪያችን ወይም ተግባሮቻችን ተራና አስፈላጊ ያልሆኑ ወደሚመስሉበት ሁኔታ ላይ ባደረሱን ሁኔታዎች መበሳጨት በጣም አሳዛኝ ነገር ነው። የግልና ተራ (ዝቅ ያሉ) ተግባራት ለአንተ አስጸያፊ ሆነዉ ይታዩሃል፤ በዚህም እረፍት የለሽ፣ የተቸገርክና እርካታ አልባ ሆነሃል። ይህ ሁሉ የሚመለጨዉ ከራስ ወዳድነትህ ነው። . . .

"ያለማቋረጥ የሚያለቅሱና የሚያጉረመርሙ፣ ደስተኛነትና የደስታ ፊት ማሳየት እንደ ኃጢአት የሚሰማቸው ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች እውነተኛ የሃይማኖት ርዕስ (ልብ) የላቸውም።"—Ibid., vol. 3, p. 334.

"ስለሚጣፍጥ አሁንም በኋላም እጥፍ ድርብ (ከመጠን በላይ) እየበላሁ፣ ስለ ሆዳምነቴ ግንዛቤ ማግኘት ባልቻልኩበት ሁኔታ ዉሥጥ ሆኘ፣ በጽሑፍ ሥራዬ እንዲረዳኝ እንዴት ተንበርክኬ እግዚአብሔርን ልለምን እችላለሁ? በሆዴ ዉስጥ የወጠኩትን ምክንያታዊ ያልሆነ ሸክም እንዲንከባከበልኝ እግዚአብሔርን መጠየቅ እችላለሁን? ይህ እርሱን ማዋረድ ነው። ያ በገዛ ራሴን ባለመግዛት ኃጢአቴ እርሱ እንድተባበረኝ መጠየቅ ነው። አሁን ያሻኝን ያህል ግብስብስ በልቼ፤ ከዚያም እሱ እንድሠራው የሰጠኝን ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ኃይል እንዲሰጠኝ  መጠየቅ ትክክል አይደለም።"—Ibid., vol. 2, pp. 373, 374

"የክርስቶስ ሃይማኖት ልብን ሲገዛ ሕሊናችንም ይፈቅዳል፣ ሰላምና ደስታም ይነግሣል። ግራ መጋባትና ችግር ሊከብቡ ይችላሉ፣ ነገር ግን በነፍስ ውስጥ ሁል ጊዜ ብርሃን አለ።"—Ibid., vol. 4, p. 47.

### 3. የተለመዱ ወጥመዶችን ማምለጥ

### ሀ. በስም ብቻ ካለው እምነት በተቃራኒ ከክርስቶስ ጋር ባለው እውነተኛ ግንኙነት ውስጥ የትኛው ቁልፍ መሠረታዊ ሥርዓት አስፈላጊ ነው? ያእቆብ 4፡4።

*“ክርስቲያናዊ ሕይወታቸውን በግማሽ ተኩል የሚጀምሩት፣ መጀመሪያ ዓላማቸው ምንም ይሁን ምን በመጨረሻ ከጠላት ጎን ተሰልፈው ይገኛሉ። ከሃዲ፣ ከእግዚአብሔር መንገድ ተቃራኒ መሆን ከሞት የበለጠ ከባድ ነው። የዘላለም ሕይወት ማጣት ማለት ነውና።*

*“ሁለት አስተሳሰብ ያላቸው ወንዶችና ሴቶች የሰይጣን ምርጥ አጋሮች ናቸው። ለራሳቸው ምንም ዓይነት ጥሩ አስተያየት ቢኖራቸውም፣ ተቃዋሚዎች ናቸው። ለእግዚአብሔርና ለእውነት ታማኝ የሆኑ ሁሉ ለጽድቅ መቆም አለባቸው ምክንያቱም ትክክል ነውና። ካልተቀደሱ ጋር መቀላቀልና ለእውነት ታማኝ መሆን፣ በቀላሉ የማይቻል ነገር ነው። ራሳቸዉን ከሚያገለግሉት፣ ዓለማዊ እቅዶችን ከሚተገብሩት ጋር አንድነትን በመፍጠር፣ ከሰማያዊው መካሪ ጋር ያለንን ኅብረት ማጣት የለብንም። ከጠላት ወጥመድ እናመልጥ ይሆናል፣ ነገር ግን ተጎድተናል፣ ቆስለናል፣ እንዲሁም ልምዳችን ድንክዬ ወይም የደከመ ይሆናል።”*—The Review and Herald, April 19, 1898.

### ለ. እያንዳንዱን የቅናት ዝንባሌ አጥብቀን ነቅለን ማስወገድ ያለብን ለምንድን ነው? ያእቆብ 4:5፣ 6

*“በሳኦል ባህሪይ ውስጥ አንድ ትልቅ ጉድለት የመወደድ ወይም ጭብጨባ የመፈለግ ፍቅሩ ነው። ይህ ባህሪ በድርጊቶቹና በአስተሳሰቦቹ ላይ ሥልጣን ነበረው፤ ሁሉም ነገር ለመወደስና ራስን ከፍ ከፍ ለማድረግ ባለው ፍላጎት ያደርግ ነበር። ትክክል ወይም ስህተት የሚለውን ነገር የሚለካው በህዝብ ጭብጨባ መሠረት ነበር። ሰውን ደስ ያሰኘ ዘንድ በሕይወት የሚኖር ማንም ሰው አይድንም፤ አስቀድሞ የአምላክን ሞገስ ለማግኘት አልፈለገምና።”*—Patriarchs and Prophets, p. 650

*“ሳኦልን ያዳከመዉ እና ዙፋኑን አደጋ ላይ የጣለው ምቀኝነቱ ነው። ይህ ክፉ ባህሪይ በዓለማችን ላይ ምን ያህል ያልተነገረ ጥፋት ሰርቷል! የቃየንን ልብ በወንድሙ በአቤል ላይ የቀሰቀሰው ዐይነት በሳኦል ልብ ውስጥም ተመሳሳይ ጠላትነት ነበረ፣ ምክንያቱም የአቤል ሥራዉ ጻድቅ ነበር፣ እግዚአብሔርም አክብሮታል፣ ቃየን የገዛ ሥራው ክፉ ነበር፣ እግዚአብሔርም ሊባርከው አልቻለም። ምቀኝነት የኩራት ዘር ነው፤ በልብ ውስጥ ከተንከባከቡት ደግሞ ወደ ጥላቻ፣ በመጨረሻም ወደ በቀልና ወደ መገዳደል ይመራል።”*—Ibid., p. 651

*“ለእግዚአብሔር መገዛት፣ ፍቅርና ምስጋና፣ ቀኑ ምንም ያህል በጣም ደመናማ ቢሆንም በልብ ውስጥ ብርሃንን ያፈነጥቃሉ። ራስን መካድና የክርስቶስ መስቀል በፊትህ ናቸውና። መስቀሉንስ ታነሳለህን?”*—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 47.

## 4. ትኩረት እና መገዛት

### ሀ. በክርስቶስ እውነተኛና ዘላቂ የሆነ ድል እንድናገኝ የሚረዳን የትኛው አስፈላጊ ነገር ነው? ያእቆብ 4፡7

*“አንዳንዶች የኃጢያት ክፍያ እንደሚያስፈልጋቸው ይሰማቸዋል፣ ይህን ፍላጎት ሲያስተዉሉና የልብ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ሲያዉቁ፣ ትግሉ ይጀምራል። የራሳቸውን ፈቃድ ለመካድ ጥረትን ይጠይቃል፣ እዚህጋ ሲደርሱ ብዙዎች ያመነቱና ይወድቃሉ ወይም ወደ ኋላ ይመለሳሉ። ሆኖም ይህ ጦርነት በእውነት በተለወጠ ልብ ሁሉ ዉስጥ መኖር አለበት። ከውጪም ከውስጥም ፈተናዎችን መዋጋት አለብን። በራሳችን ላይ ድልን ማግኘት አለብን፣ ሰበአዊ መሻቶችንና ምኞቶችን መስቀል አለብን፤ በዚያን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር የነፍስ አንድነት ይጀምራል። የጠወለገውና ህይወት የሌለው የሚመስለው ቅርንጫፍ በህያው ዛፍ ግንድ ላይ ተሰክቶ ሕይወትን እንደሚያገኝ ሁሉ፤ እኛም የእውነተኛው ወይን ህያው ቅርንጫፎች እንሆናለን። ክርስቶስ ያፈራው ፍሬም በሁሉም ተከታዮቹ ይፈራል። ይህ አንድነት ከተመሰረተ በኋላ ሊጠበቅ የሚችለው ቀጣይነት ባለው፣ በትጋትና በቅን ጥረት ብቻ ነው። ክርስቶስ ይህን የተቀደሰ ትስስር ለማቆየትና ለመጠበቅ ኃይሉን ይጠቀማል፤ ረዳተ አልባና አቅመ ቢስ የሆነዉ ኃጢአተኛ በትጋት የድርሻውን መወጣት አለበት፣ አለዚያ ሰይጣን በጨካኙና ተንኮለኛ ኃይሉ ከክርስቶስ ይለየዋል።*

*“እያንዳንዱ ክርስቲያን ሰይጣን የሚደርስበትን የነፍስን መንገድ ለመጠበቅ ያለማቋረጥ ነቅቶ መቆም አለበት። ለመለኮታዊ እርዳታ መጸለይ እና በተመሳሳይ ጊዜ ማንኛውንም የኃጢአት ዝንባሌ በቆራጥነት መቃወም አለበት። በድፍረት፣ በእምነት፣ በጽናት በመታገል ማሸነፍ ይችላል። ነገር ግን ድልን ለማግኘት ክርስቶስ በእርሱና እርሱም በክርስቶስ መኖር እንዳለበት አስታውስ።”*— Testimonies for the Church, vol. 5, p. 47.

### ለ. ጳውሎስ በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ መንፈሳዊ ጥንካሬን በተመለከተ ያዕቆብ የሰጠውን ማብራሪያ የሚያስተጋባው እንዴት ነው? ሮሜ 6፡6-11

*“ዓለማዊ አስተሳሰብ፣ ራስ ወዳድነትና መጎምጀት የአምላክን ሕዝቦች መንፈሳዊነትና ሕይወት እየበሉ ናቸዉ።”*—Ibid., vol. 1, p. 141.

*“በጣም የጠነከረ እምነትና የበለጠ ቅን አምልኮ ያስፈልገናል። እናም በአእምሯችንና በልባችን ለአዳኛችን ያለውን ፍቅር ለመንከባከብ፣ ለራሳችን መሞት (ራስ ወዳድነትን መግደል) አለብን። ጌታን በሙሉ ልብ ስንፈልግ እሱን እናገኘዋለን፣ እንዲሁም ልባችን በፍቅሩ ይቃጠላል። እራስ ወደ ኢምንትነት ይወርዳል፣ የሱስ በነፍሳችን ሁሉ በሁሉ ይሆናል። . . .*

*“ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለብን። ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ መሆን አለብን፣ ካልሆነ ግን በምናደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ድክመትና ስህተቶች ይታያሉ።”*—Ibid., vol. 6, p. 51.

ሐሙስ **ህዳር 26**

## 5. ለቅን ጸሎት ቆም ማለት

### ሀ. ከክፉ ዝንባሌዎቻችን ጋር በምናደርገው ውጊያ ለእያንዳንዳችን የሚያስተጋባ ምን ማረጋገጫና ተማጽኖ አለን? ቆላስይስ 3:1-3፤ ያእቆብ 4:8፣ 9

*"የዓለም ፍቅር ያለበት ማንም ሰው እውነትን ሊያውቅ አይችልም። ዓለም በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ይገባል፣ እይታቸዉ እየደበዘዘና ቅዱሳን ነገሮችን ለመለየት እስከማይችሉ ድረስ ስሜቶቹ እያደነዘዘ ይሄዳል። እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናግሯል፦ "እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ። ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ ልባችሁን አንጹ። ተጨነቁና እዘኑ አልቅሱም፤ ሳቃችሁ ወደ ኀዘን ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ።" በአለም ብክለት እጆቻቸውን ያረከሱ ሰዎች እራሳቸውን ከቆሻሻው ማጽዳት ይጠበቅባቸዋል። ዓለምን እያገለግሉ እግዚአብሔርን እንወዳለን የሚሉ ሁሉ ሁለት አሳብ ያላቸው ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሔርንና ገንዘብን* (mammon) *ማገልገል አይችሉም። ዓለምን የሚወዱ ከዚህም የተነሳ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ግዴታ የዘነጉ፣ ነገር ግን የክርስቶስ ተከታዮች እንደሆኑ የሚናገሩ ሁሉ ሁለት ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ናቸው። የሁለቱም አይደሉምና። ንጹሕ የእውነት መሠረታዊ ሥርዓቶችን በመታዘዝ እጃቸውን ካላጸዱና ልባቸውን ካላጸዱ በስተቀር ሁለቱንም ዓለም ያጣሉ።"*—Testimonies for the Church, vol. 1, pp. 530, 531.

### ለ. በትሕትና በእግዚአብሔር ፊት ስንሰግድ ምን ይሆናል? መዝሙረ ዳዊት 34:18፤ 1ኛ ጴጥሮስ 5:6፣ 7

*"አሁን ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ካዋረድክ፣ በደልህን ከተናዘዝክና በሙሉ ልብህ ወደ እሱ ከተመለስክ፣ የደስተኛ* (*የእግዚአብሔር*) *ቤተሰብ አካል መሆን ትችላለህ። ይህን ካላደረግክ ግን የራስህ መንገድ ከመረጥክ በደስታህ ፍጻሜ* (*መጨረሻ*) *ላይ ነህ።"*—Ibid., vol. 2, p. 304.

አርብ **ህዳር 27**

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. *ውስጣዊ ስሜቴን በጥልቀት ሲመረምር፣ በየትኞቹ አካባቢዎች ነዉ ግብዝ ሊሆን የምችለዉ?*
2. *ቃሎቻችን ብዙ ጊዜ ክርስቶስን በተሳሳተ መንገድ የሚገልጹባቸውን አንዳንድ መንገዶች ጥቀስ።*
3. *ምቀኝነት እምነትን መካድና አምላክን መሳደብ ነዉ የሚባለው ከምን አንጻር ነው?*
4. *በክርስቶስ ሕያው ለመሆን ለራሴ መሞት ለምን አስፈለገኝ?*
5. *ይህ ትምህርት ማሸነፍ ያለብኝ አንዳንድ እውነተኛ ጉዳዮችን እንዴት ያጠቃልላል?*

## 11ኛ ትምህርት ሰንበት ታህሳስ 05፣ 2017

## ትሁት አመለካከትን ማዳበር

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል" (ያዕቆብ 4፡10)።**

*"በመታዘዝ የትህትና ጎዳና ስንራመድ ሌሎችም ይራመዱበት ዘንድ ወደ ሰማይ የሚያቀና ብሩህ ጎዳና እናመቻቻለን። በእግዚአብሔር ዓላማዎች ላይ ጥልቅ ተሞክሮ ይኖረን ዘንድ ለእኛ መታደል ነው።"*— The Science of the Times, March 17, 1890.

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡-** Testimonies for the Church, vol. 2, pp. 41–44, 678–686

እሁድ ህዳር 29

### 1. የሐሰት ማስተዋልን ማስወገድ

### ሀ. ወንድሞቻችንን እንወዳለን ከሚሉት ከሁሉም ዘንድ ምን በጣም ጎጂ ልማድ ነው ጨርሶ መወገድ ያለበት— ለምን? ያዕቆብ 4፡-11.12

*" በሌሎች ላይ ክፉ መናገር ወይም በእነርሱ ዓላማ ወይም ድርጊት ላይ ራሳችንን ፈራጅ ማድረግ እንደ ቀላል ነገር ተደርጎ መቆጠር የለበትም።"*— Patriarchs and Prophets, p. 385.

*"የግብረ ገብነት (የሞራል) እውነተኛ ዋጋ ክፉ በማሰብም ሆነ በመናገር፣ ሌሎችንም በማቃለል ለራሱ ቅድሚያ አይወስድም። እያንዳንዱ ምቀኝነት፣ ቅንዓት፣ ክፉ ንግግር (ሀሜት) ከማንኛውም ዓይነት አለማመን ጋር ተጠራርጎ ከእግዚአብሔር ልጆች ዘንድ መወገድ ይኖርበታል።"*—Our High calling, p. 234

*"በቤተክርስቲያናት ላይ አደገኛ ክፋትን በማስከተሉ ረገድ ውጤታማ ከሆኑት ኃጢአቶች መካከል በመሆናቸው፣ ሀሜትና የትችት መንፈስን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ በእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን እልህ አስጨራሽ ጥረት መካሄድ ይኖርበታል። ግትርነትና አቃቂረኛነት (እንከን ፈላጊነት) ሰይጣን እንደሚሰራባቸው መሳሪያዎች ተደርገው ሊወገዙ ይገባል። የጋራ ፍቅር እና መተማመን በቤተክርስቲያን አባላት መካከል መበረታታትና መጠናከር ይገባቸዋል። ሁሉም፣ በፈሪሃ እግዚአብሔር እና ለወንድሞቻቸው ባላቸው ፍቅር ለሀሜት እና ለትችት ጆሮቻቸውን ይዝጉ። ሀሜተኛውን ሰው ወደ ቃለ እግዚአብሔር ትምህርት በቀጥታ አመላክቱት። መጽሐፍ ቅዱስን እንዲታዘዝ በመጠየቅ አለኝ የሚለውን ቅሬታ ተሳስተዋል ብሎ ላሰባቸው ሰዎች በቀጥታ አቅርብ ብላችሁ ሞግቱት። ይህ የተባበረ ተግባር በቤተክርስቲያን ላይ የብርሃን ጎርፍ እንዲጎርፍ ሲያደርግ በአንፃሩ የክፋትን ጎርፍ ይገድባል። ይህ ሲሆን እግዚአብሔር ይከብራል ፤ በጣም ብዙ ነፍሳትም ይድናሉ።"*—Testimonies for the Church, vol. 5, pp. 609–610

## 2. ብርሃንን በአንክሮ መውሰድ

### ሀ. እቅድ ስናቅድ ሁልጊዜም ቢሆን በልባችን መያዝ ያለብን ነገር ምንድን ነው? መዝ 16:8; ያዕ 4፡- 10፣ 13-16

"በማለዳ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ቀድሳችሁ አስረክቡ ፤ ይህ የመጀመሪያ ተግባራችሁ እንዲሆን አድርጉ። ፀሎታችሁ፡- "አ ! ጌታ ሆይ ውሰደኝ ሙሉ በሙሉ የራስህ አድርገኝ እቅዶቼን ሁሉ በእግርህ ሥር አስቀምጣለሁ። ዛሬ ለአገልግሎትህ ተጠቀምብኝ። ከእኔ ጋር ሁንና የማደርገውን ነገር ሁሉ በአንተ እንዳደርገው እርዳኝ" የሚል ይሁን። በየማለዳ ለዚያ ቀን ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ቀድሳችሁ ስጡ። የእርሱ ምሪት በሚያሳችሁ መሰረት ወይ እንዲከናወኑ አልያም እንዲከሸፉ እቅዶቻችሁን ሁሉ ለእርሱ ስጡ። በዚህም መሰረት ዕለት በዕለት ሕይወታችሁን ለእግዚአብሔር እጆች ትሰጣላችሁ ፤ ሕይወታችሁም ክርስቶስን ወደ መምሰል እየተለወጠ ይሄዳል።"— Steps to Christ, p. 70.

### ለ. በሁሉም የሕይወት ጉዳዮች ለተሰጠን ሰማያዊ ብርሃን እያንዳንዳችን ያለብንን የከበረ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ይግለፁ? ያዕቆብ 4፡-17 ፤ ማቴዎስ 12፡- 31፣32

"የሰዎችን ዓይን የሚያሳውርና ልባቸውንም የሚያደነድን እግዚአብሄር አይደለም። ይልቁንም በአስተማማኝ መንገድ እንዲሄዱና ስህተታቸውንም እንዲያርሙ ብርሃን ይልክላቸዋል። ይህን ብርሃን ችላ በማለት ነው ዓይን የሚታወረው ልብም የሚደነድነው። ሂደቱ ብዙውን ጊዜ አዝጋሚና ጎልቶ የማይታወቅ ነው። ብርሃን ወደ ነፍሳት የሚደርሰው በእግዚአብሄር ቃል፣ በአገልጋዮቹ ወይም በቀጥታ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው። ነገር ግን ከሚሰጠው ብርሃን አንዲት ጨረር እንኳን ችላ ከተባለች፣ መንፈሳዊ ነገርን የማስተዋል ችሎታ በከፊል ስለሚቀንስ ለሁለተኛ ጊዜ የሚገለፀው ብርሃን የደበዘዘ ይሆናል። በዚህ አኳኋን ጨለማው እየጨመረ ሲሄድ ነፍስ ጥቅጥቅ ጨለማ ውስጥ ትሆናለች።"—The Desire of Ages, p. 322.

"የጥርጣሬ ቃል መናገር፣ ስለ መለኮታዊ ብርሃን ጥያቄ ማንሳት ወይም ያን ብርሃን መንቀፍ አደገኛ ነው። በግድየለሽነትና አክብሮት በጎደለው መንፈስ የሚደረግ የትችት ልምድ ንቀትና አለማመን ሥር እንዲሰዱ በማድረግ በጠባይ ላይ ለውጥ ያስከትላል። ለዚህ ዓይነት ልምድ ተገዥ የሆነ ሰው ያለበትን አደገኛ ሁኔታ ባለመገንዘብ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለመተቸትና ችላ ለማለት የተዘጋጀ ይሆናል።" —Ibid, p. 323.

"ሰዎች ስለ ጤና ርዕስ ጉዳይ ሲናገሩ ብዙ ጊዜ 'ማወቅ ካለብን ነገር የበለጠ ብዙ እናውቃለን' ይላሉ። አካላዊ ደህንነታቸውን በተመለከተ ለእያንዳንዱ የብርሃን ጨረሮች ተጠያቂ መሆናቸውን እና እያንዳንዱ ልማዳቸው ለእግዚአብሔር ምርመራ በግልጽ የሚታይ መሆኑን አይገነዘቡም።"—Testimonies for the Church, vol. 6, p. 372

## 3. ከሚገባው በላይ የተጋነነ ኃብት (Riches overestimated)

### ሀ. ከሌሎች በላይ በቁሳዊ ኃብት የተባረኩ ሰዎች የከበቧቸውን ፈተናዎች አስመልክቶ ምን ማስጠንቀቂያ ተሰጠ ? ያዕቆብ 5፡-1

*“አገልጋዮች (ሚነስተሮች) የሙገሳ ቃላትን የሚያጎርፉ ወይም ፊትን አይተው የሚያዳሉ መሆን የለባቸውም። ለሀብታሞች በትንሹም ቢሆን ልዩነት የመፍጠር ካልሆም እነርሱን በቃል ደረጃ የማድነቅ አደጋ ድሮም፣ እስካሁን ድረስ የመሳሳት ከፍተኛ አደጋ እዚህ ላይ ተደቅኖአል። ለጥቅም ሲባል ‘ለሰዎች አድናቆት የማጉረፍ’ አደጋ አለ ፤ ዳሩ ግን ይህን በማድረግ ዘላለማዊ ፍላጎታቸው (ሕይወታቸው) አደጋ ላይ ይወድቃል። አንድ አገልጋይ (ሚኒስቴር) ምናልባት ከተወሰኑ ባለጸጋ ሰዎች የተለየ ሞገስ በማግኘት ልግስና ተችሮት ሊሆን ይችላል ፤ በዚህም አገልጋዩ የልቡ ደርሶ ሊደሰትና፣ በፋንታው ደግሞ ላደረገለት በጎ አድራጎት ለሰጪው የውዳሴ ቃል እንዲያጎርፍ ሊያደርገው ይችላል። ምናልባት የሰጪው ስም በህትመት ውጤቶች ሊወጣ ይችላል ፤ ይሁን እንጂ ያ በልግስና የለገሰው ሰው ለጎረፈለት ምስጋናና ለተሰጠው መልካም ስም ጨርሾ ያልተገባ ሊሆን ይችላል። ልግስናው የተበረከተው፣ በገንዘቡ (በንብረቱ) መልካም ነገር ለማድረግ ወይም፣ አድናቆት ስላለው የእግዚአብሔርንም ዓላማ ለማስፋፋት ከሚል እጅግ ጥልቅና ህያው መርህ የመነጨ አይደለም ነገር ግን ከአንድ ከሆነ የራስ ወዳድነት ስሜት፣ ለጋስ ነው የሚል ስም ለማግኘት ካለው ጽኑ መሻት ተነስቶ ሊሆን ይችላል። ምናልባት በስሜት ተነሳስቶ ሊለግስና በመርህ ደረጃ ልግስናው ጥልቀት የሌለው የታይታ ብቻ ሊሆን ይችላል። ምናልባት ስጥ ስጥ የሚያሰኝ ልብን የሚያላውሰውን እውነት በመስማት በወቅቱ የገንዘብ ቦርሳውን ከፍቶ ሊሆን ይችላል ፤ ይሁን እንጂ፣ ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ ልግስናው ጥልቅ ዓላማ የለውም፡ ፡ በድንገት ይሰጣል ፤ ቦርሳውም እንዲሁ ድንገት ይከፈታል ከዚያም በጥንቃቄ ክርችም ብሎ ይዘጋል። ስለዚህ ይህ ሰው አንዳች የምስጋና ቃል አይገባውም ፤ ምክንያቱም በማንኛውም የቃሉ መረዳት ቢታይ ገብጋባ (ስስታም) ነውና ፤ በመሆኑም በገንዘቡም ይሁን በሁሉም ነገር ሙሉ በሙሉ ካልተለወጠ በቁሙ የሚያደርቀውን (የሚያጠወልገውን) ውግዘት ተገዶ ይሰማል፦ ‘እንግዲህ እናንተ ባለ ጠጎች ስሙ፥ ስለሚደርስባችሁ መከራ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ፤ ሀብታችሁ ሻግቶአል ፤ ልብሳችሁንም ብል በልቶታል’። እንዲህ ያሉ ሰዎች በስተመጨረሻ እግጅ ዘግናኝ ከሆነው መታለል የሚነቁ ይሆናል። አልፎ አልፎ የሚለግሱ ሰዎችን የሚያሞግሱ ሰዎች ይሸነግላቸው (ያታልላቸው) ዘንድ ሰይጣንን ያግዙታል ፤ እንዲሁም የልግስናን ወይም መስዋዕት የመክፈልን የመጀመሪያ መርሆዎች ምንም የማያውቁ ሆነው ሳሉ፣ ነገር ግን በጣም ለጋሶች፣ ከፍተኛ መስዋእት ከፋዮች እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን እንዲቆጥሩ ያደርጓቸዋል። ”*—Testimonies for the Church, vol. 1, pp. 475, 476.

### ለ. ገንዘብን በበተመለከተ በቅድሚያ የሚያሻንን ነገር እንዴት ነው ማሻሻል የምንችለው ? ምሳሌ 11:4.

*“የበጎ አድራጎት ልግስናን መለማመድ፣ (የሕይወት) መርህ እስኪሆንና የነፍስንም ዙፋን እስኪቆጣጠር ድረስ ዘወትር እየጎለበተና እየጠናከረ ይሄዳል። በልብ ውስጥ ራስ-ወዳድነትና ስግብግብነት ትንሽ ሥፍራም እንዲያገኝ መፍቀድ ለመንፈሳዊ ሕይወት እጅግ በጣም አደገኛ ነገር ነው። ”*—Ibid., vol. 3, pp. 548, 549.

## 4. ጣኦትን ጨርሶ ማስወገድ

### ሀ. ሰዎች ኃብትን የሚያገኙት በአብዛኛው በምን ምክንያት ነው? ያዕቆብ 5:-2 (የመጀመሪያው ክፍል)

*"የዚህ ዘመን ትውልድ ሃብት በማፍራት ጥልቅ ፍቅር ውስጥ ወድቋል። ብዙ ጊዜ ሀብት የሚገኘውም በማጭበርበር ነው። ለትንሽ ደመወዝ ላባቸውን ጠብ አድርገው ለመሥራት የተገደዱ፣ መሰረታዊ የኑሮ ፍላጎትን እንኳ ማሟላት አዳግቷቸው በድህነት እየተቀራመዱ የሚኖሩ ሥፍር ቁጥር የላቸውም፡ ፡ በእጦት ተቸግረው፣ በጥረት ግረት እየለፉ ተስፋ በማጣታቸው ቀንበራቸውን አክብዶባቸዋል። በኑሮ አሳብ ተጨንቀውና ተጨቁነው እፎይታ ለማግኘት አቤት ለማለት ወደ ማን እንደሚዞሩ ግራ ገብቷቸዋል። በዚህ ሁሉ ታዲያ ሃብታሞች በምቾትና በመንፈላሰስ ያላቸውን ማካበት ብቻ !*

*"ገንዘብን መውደድና ሃብትን ማካበት ይህችን ዓለም የሌቦችና የቀማኞች ዋሻ አድርጓታል። ከክርስቶስ ዳግም ምፃት በፊት የሚሆነውን ስግብግብነት (ሆዳምነት) እና ጭቆና መጽሐፍ ቅዱስ ቁልጭ አድርጎ ገልፆታል።"*—Prophets and Kings, p, 650,651 (*ነቢያትና ነገሥታት ገጽ* 650,651)

### ለ. ዛሬ ዓለምን በአብዛኛው የሚያነሳሳቸው ምንድን ነው? በገንዘብ ፍቅር ለሚነዱ ሰዎች ምን ተማጽኖ ነው መቅረብ ያለበት? 1ኛ ጢሞ 6:- 9፣10 ፤ ዘዳ 8: 18፣19

*"ኃብቱን በሀቅ እስካገኘው ድረስ አንድ ሰው ሃብታም ስለሆነ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስ አይዘልፈውም። የክፋት ሁሉ ሥር የሆነው ገንዘብ ሳይሆን ለገንዘብ ያለው ፍቅር ነው። ሀብት እንዲያገኝ ለሰው ጉልበትን የሰጠ እግዚአብሄር ነው ፤ በመሆኑም ሀብቱን እየተጠቀመ ገንዘቡን እንደ የእግዚአብሄር መጋቢነት ለሚሰራ ሰው ለባለ ገንዘቡም ሆነ ለዓለምም ጭምር በረከት ነው። ነገር ግን ብዙዎቹ ዓለማዊ ሀብት በማግኘት ፍቅር ተመስጠው እግዚአብሔር ለሚጠይቃቸው መጠየቅና የባልንጀሮቻቸውንም ፍላጎት ለማሟላት ህሊናቸው ደንዝዟል። ገንዘባቸውን ራሳቸው ለማስከበሪያነት ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ነገር አድርገው ይቀጥሩታል። ቤቶቻቸውን በቅንጦት እቃዎች ይሞላሉ ፤ ነገር ግን በዙሪያቸው ሰብዓዊ ዘር በሰቀቃ፣ በወንጀልና በበሽታ እየማቀቁ በሞት እየተቀጠፉ እነርሱ ግን በቤት ላይ ቤት፣ በመሬት ላይ መሬት ይጨምራሉ። እነዚህ በዚህ መልኩ ራሳቸውን ለማገልገል ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ሰዎች በህይወታቸው ላይ የእግዚአብሔር ባህርይ ሳይሆን ነገር ግን የእርጉሙን ባህርይ ይገነባሉ።*

*" ለእነዚህ ወንጌል በጣም ያሻቸዋል። አይኖቻቸውን ከንቱ ከሆነው አላፊ ጠፊ ቁስ አንስተው እጅግ ክቡር ወደሆነው ዘላለማዊ ሃብት ማዞር አለባቸው።* …

*" አንዳንዶች ከፍ ላለው የሕብረተሰብ ክፍል ለመሥራት የሚያስችል የተለየ ብቃት አላቸው። እነዚህ ወገኖች ወደ ታለሙት አባላት እንዴት መድረስ እንዳለባቸው እንዲያውቁ እግዚአብሄር ጥበብ ይሰጣቸው ዘንድ እርሱን መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡ ፡ ከእነርሱ ጋር የሚፈጥሩት ትውውቅ ተራ መሆን የለበትም ፤ ይልቁንም በየሱስ ወዳለው የእውነት እውቀት የሚመራውንና ግላዊ ጥረት የታከለበትን ሕያው እምነት ተጠቅመው ለነፍሳቸው የሚያስፈልገውን እንዲያውቁ ካንቀላፉበት መቀስቀስ ይኖርባቸዋል።"*—The Ministry of Healing., pp. 212,213.

ሐሙስ ታህሳስ 03

## 5. ከቁሳዊው ዓለም ባሻገር መመልከት

### ሀ. በወንጀል የተገኘ ሀብት የሚያመጣውን መዘዝ ይግለፁ። ያዕቆ 5፡- 2 (የመጨረሻው ክፍል)

*"ሀብት በማጭበርበር ማግኘት፣ በንግድ ማጭርበር፣ መበለቶችና አባት የሌላቸውን መጨቆን፣ ወይም ለራስ ማከማቸትና የተቸገሩ ድሆችን ችላ ማለት የኋላ ኋላ በመንፈስ በተነሳሳው ሐዋሪያ የተገለፀው ፍትሃዊ ፍርድ እንዲወርድ ያደርጋል።"*—Testimonies for the Church, vol. 2, p. 682.

### ለ. ሃብትን በተመለከተ የእግዚአብሔር ልዩ መልዕክት ምንድን ነው? 1ኛ ጢሞቴዎስ 6:17–19.

*"እጅግ ትሁትና ድሆች የሆኑ፣ በመልካም ሥራ ግን የበለፀጉ እውነተኛ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት፣ ባላቸው ታላቅ ሀብት ከሚኩራሩ ሰዎች ይልቅ በእግዚአብሔር እይታ እጅግ የተባረኩና የከበሩ (ክቡር ዋጋ ያላቸው) ናቸው፡ ፡ እነርሱ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለፀጋ ካልሆኑት እጅግ ከተከበሩት ነገሥታት ይልቅ፣ እነርሱ በሰማይ አደባባ እጅግ የተከበሩ ናቸው።. . .*

*"እነዚያ የቤተሰባቸው ማግኘት ያለባቸውን ደስታና ምቾት አራቁተው (ነፍገው) ገንዘብን የሚያከማቹ ወይም በመሬት ግዥ ላይ በስፋት እያፈሰሱ ያሉ ሰዎች እብዶች እንደሚያደርጉት እያደረጉ ናቸው። እግዚአብሔር በብልጽግና አትረፍርፎ የሰጣቸውን በረከት ቤተሰቡ ይደሰቱበት ዘንድ አይፈቅዱላቸውም። ምንም እንኳ በጣም ብዙ ሀብት ቢኖራቸውም፣ የቤተሰቡ አባላት ብዙ ንብረት ያከማቹ ዘንድ፣ አሁንም ገና ብዙ ገንዘብ ለመቀጠብ አቅማቸው ከሚፈቅደው በላይ አዘውትረው ለመስራት ይገደዳሉ። ሀብት ለማካበት፣ አዕምሮ፣ አጥንት፣ እንዲሁም ጡንቻ እስከ መጨረሻው በሥራ ብዛት ይወጠራሉ ፤ በአንፃሩ ኃይማኖት ክርስቲያናዊ ግዴታዎች ተረስተዋል። ከጠዋት እስከ ማታ የነፍሳቸው ምኞት ሥራ፣ ሥራ፣ ሥራ የሚል ነው።*

*"ብዙዎቹ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመማር እና ከእነርሱ የሚሻውንም ነገር ለማስተዋል ቀን ፍላጎት እያሳዩ አይደለም። እውነትን ለሌሎች ለማስተማር እየጣሩ ያሉ አንዳንዶቹ የጌታን ቃል ራሳቸው አይታዘዙትም። እንደነዚህ ያሉ አስተማሪዎች ተጽዕኖ በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ ባረፈ ቁጥር፣ የሚገኘው ውጤትም እጅግ ያነሰ ይሆናል።"*— Ibid., pp. 682, 683

አርብ ታህሳስ 04

## የግል ክለሳና የመወያያ ጥያቄዎች

1. በሌሎች ስህተት ላይ በማተኩርበት ጊዜ ምን እያደረኩኝ ነው ?
2. ሰማይ የላከውን ብርሃን ችላ ስል፣ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚያዝን ግለፁ ?
3. ሀብታሞች እና ሚኒስተሮች (ፓስተሮች) ወደ ወጥመድ እንዴት ሊወድቁ ይችላሉ ?
4. ስስታምነት ለምንድነው እየጨመረ ያለው፣ ከመቼውም ይልቅ አሁን ማስወገድ ያለብን ለምድን ነው?
5. በክርስቶስ ራስን ማዋረድ (ትህትና) የተላበሰውን ውበትና ጥቅም ይግለፁ።

**12ኛ ትምህርት ሰንበት ታህሳስ 12/ 2017**

## በሰማይ ላይ ማተኮር

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “እናንተ ደግሞ ታገሡ፤ ልባችሁን አጽኑ፤ የጌታ መምጣት ቀርቦአልና” (ያዕቆብ 5፡-8)።**

“*ዘወትር ያለማቋረጥ በክርስቶስ ጽድቅ መጎናፀፍ ይኖርባችኋል። የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችሁና ሩህሩህ፣ ደግና ትዕግስተኛ መንፈስ መያዝ (ማካበት) እንዳለባችሁ በልቦናችሁ መያዝ ያስፈልጋችኋል። ራስ ወዳድነትና ስግብግብነት በነፍሳችሁ ላይ ጨርሶ ማደር እንደማይገባው ይወታችሁን በጥልቀት መርምሩ፡*፡”— Manuscript Release, Volume 13, p 288

**ለጥናት የተመረጠው መጽሐፍ፡-** Early Writings, p 72,73

እሁድ ታህሳስ 06

**1. ጊዜው እንደገና ህይወትን በጥልቀት የመመርመር ነው**

**ሀ. ከጥንት ጀምሮ እጅግ በጣም የላቀ ዋጋ ከተሰጣቸው አልፎም እንደጣኦት በተቆጠሩ ዕቃዎች ላይ በቅርቡ ምን ይፈጠራል—ይህስ ምን ያስታውሰናል (ያስገነዝበናል ? ኢሳ 31፡-6፣7**

“*የክፋት ሁሉ ሥር የሆነው በማይሆን (በተሳሳተ) አጠቃቀም ላይ የዋለው የገንዘብ ፍቅር ነው። በምስጋና ተቀብለን ለሰጪውም በአመስጋኝነት መልሰን መስጠት ያለብን የጌታ ንብረት አድርገን ከቆጠርነው ሀብት በረከት መሆኑ በተግባር ያረጋግጣል። ነገር ግን ይህ ሀብት እጅግ ወድ (ቅንጡ) ቤቶችን ለመገንባት ወይም ለባንክ አክሲዮን (ሽርክና) ግዥ ቢከማች ምን ዋጋ ይኖረዋል ? የወሰን የለሹ ልጅ ከሞተለት (ከሞተላት) አንድ ነፍስ መዳን ጋር ሲመዛዘን ይህ የተከማቸ ገንዘብ ምን ያህል ሊተመን ነው* ?”—Testimonies for the Church, vol. 6, p. 453.

“*እነዚያ ሰበብ ማብዛትን የሚመርጡ፣ ከኃጢአታቸው እና ከዓለም ጋር በመስማማት የሚቀጥሉ ለጣኦቶቻቸው ተላልፈው ይተዋሉ። . . . ክርስቶስ በራሱ ክብርና በአባቱም ክብር ከሰማይ ሲወርድ፣ የሰማይ ሰራዊት በሙሉ በድል ነሺነት ዜማ እያጀቡት ሲወርዱ፣ ተወዳዳሪ የሌለው የሙዚቃ ድምጽ ለጆሮ ሲሰማ በዚያኔ ሁሉም ፍላጎት ይኖረዋል። በዚያኔ አንድ ግድየለሽ ተመልካች እንኳ አይኖርም። በዚያኔ መላምት (ጭፍን ሃሳብ) ነፍስን የሚቆጣጠር አይሆንም። የአይን አዋጅ ሆኖበት የነበረው የወርቅ ክምር ለንፉጉ (ለስግብግቡ) ሰው ከዚያ በኋላ ሊያጓጓው አይችልም። የምድር ኩሩ ሰዎች የገነቧቸው ጣዖቶቻቸው ሆነው የኖሩት ቤተ-መንግስታት በጥልቻና በአስቀያሚነት ችላ ይባላሉ።* ”—Ibid., vol. 2, p. 41.

## 2. ጊዜው ከመርፈዱ በፊት

### ሀ. ዛሬ ነገ በማለት ንብረት ያላቸው ሰዎች በገንዘባቸው እግዚአብሔርን ማስከበር የሚችሉበትን እድል እንደሚያጡ እንዴት ነው መጽሐፍ ቅዱሳት በጥልቀት የገለፁት ? ሆሴዕ 4:17 ፤ ማቴዎስ 25:11፣ 12.

### ለ. የወቅቱን እውነት እናምናለን የሚሉትን ጨምሮ በራስ ወዳድነት ከምድራዊ ቁስ ሃብታቸው ጋር የተጣበቁትን ሁሉ በመጨረሻ የሚገጥማቸውን ውጤት ይግለፁ፡፡ ያዕቆብ 5:3.

*"[ያዕቀብ 5:1–3 የተጠቀሰ]። እነዚህ አስፈሪ ቃላት በተለይም የወቅቱን እውነት የሚያምኑ ሀብታሞችን እንደሚመለከቱ ተመልክቻለሁ። በንብረታቸው (በገንዘባቸው) የእርሱን ዓላማ ወደፊት እንዲገሰግስ ለማድረግ ጌታ ጥሪ ያቀርብላቸዋል። አጋጣሚው ቀርቦላቸው ነበር ፤ ነገር ግን በዓላማው ላይ ዓይናቸውን ጨፈኑ ፤ ከምድራዊ ኃብታቸው ጋር በፍጥነት ተጣበቁ። ለዓለም ያላቸው ፍቅር፣ ለእውነት ካላቸው ፍቅር ወይም ለባልንጀሮቻቸው ካላቸው ፍቅር ወይም ደግሞ ለእግዚአብሔር ካላቸው ፍቅር ይበልጣል። ንብረታቸውን (ገንዘባቸውን) እንዲለግሱ የጥሪ ግብዣ አደረገላቸው ፤ ሆኖም ግን በራስ ወዳድነትና በስግብግብነት ያላቸውን ሁሉ አንለቅም አሉ። የህሊና ወቀሳቸውን ፀጥ ለማድረግ አለፍ ቀደም እያሉ ትንሽ ትንሽ ጠብ ያደርጋሉ ፤ ነገር ግን ለዚህ ዓለም ያላቸውን ፍቅር ማሸነፍ አልቻሉም። ስለ እግዚአብሔር ብለው መስዋዕት አይከፍሉም። ለዘላለማዊ ሕይወት ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጡ፣ ነፍስ ሊኖራት ስለሚችለው ዋጋ ሃሳብና ግንዛቤ ያላቸውን፣ የእግዚአብሔርን ዓላማ ወደፊት እንዲገሰግስ ለማድረግ ገንዘባቸውን በሙሉ ፈቃዳቸው ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑትን ሌሎችን በምትካቸው ጌታ አስነሳ። ሥራው በፍጥነት እየተዘጋ ነው ፤ በመሆኑም በቅርቡ ገንዘባቸውን፣ ግዙፍ የእርሻ ማሳቸውን፣ ከብቶቻቸውን እና ሌላም ንብረታቸውን ሁሉ ሙጭጭ አድርገው የያዙ ሰዎች ገንዘብ ጨርሶ የማይፈለግ ይሆናል። ጌታም ወደ እነዚህ ንፉጋን ፊቱን በቁጣ በማዞር፡- ''እናንተ ባለጠጎች ዘወር በሉ (ከፊቴ ጥፉ)'' ሲላቸው ተመለከትኩ። እርሱ ጠርቶአችኋል ፤ ነገር ግን ማዳመጥ አልፈለጋችሁም። ለዚህ ዓለም ያላችሁ ፍቅር ድምፁን አፍኖ አስቀርቶባችኋል። ስለዚህ አሁን አትጠቅሙትም (ከእናንተ የሚሻው ነገር የለም)። ስለዚህ ገለል በሉ እንዲህ ሲል ያዛችኋል፡- 'እናንተ ባለፀጎች ከፊቴ ጥፉ'።*

*"ኦህ፣ በዚህ ሁኔታ በጌታ መተፋት በጣም አስፈሪ መሆኑን አይቻለሁ።— ንብረታችንን ሸጠን ስጦታ ብንሰጥ ኖሮ፣ በሰማይ መዝገብ ማከማቸት እንደምንችል እርሱ ነግሮን እያለ፣ ነገር ግን አላፊ ጠፊውን ምድራዊ ቁስ አለቅም ብሎ መያዝ በጣም አስፈሪ ነገር ነው። ሥራው እያበቃ ሲሄድ፣ እውነትም በታላቅ ኃይል ወደፊት እየተፋጠነ ሲሄድ፣ እነዚህ ሀብታሞች ገንዘባቸውን ወደ ጌታ አገልጋዮች እግር ስር በማስቀመጥ ይቀበሏቸው ዘንድ ሲማፀናቸው አየሁ። የጌታ አገልጋዮች መልስ እንዲህ የሚል ነው፡- 'ሂዱ እናንተ ባለፀገጎች። ገንዘባችሁ በቃ አይፈለግም። የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማስፋፋት በገንዘባችሁ መልካም ነገር ማድረግ ስትችሉ ይዛችሁ አስቀራችሁት፡ ፡ ድሆች በጣም ተሰቃዩ። በገንዘባችሁ ሊባረኩ አልቻሉም። አሁን እግዚአብሔር ገንዘባችሁን አይቀበላችሁም። ስለዚህ ሂዱ እናንተ ባለፀጎች ዘወር በሉ' "*—Testimonies for the Church, vol. 1, pp. 174, 175.

### 3. ወርቃማውን ሕግ (መመሪያ) መማር

**ሀ. ሀብታሞች (በሀብት የበለፀጉ ሰዎች) የቀጠሯቸውን ወይም ከእነርሱ የሚገዟቸውን ሰዎች ብዙ ጊዜ እንዴት ነው የሚመለከቷቸው—እኛስ ሁልጊዜ በልባችን መያዝ ያለብን ነገር ምንድን ነው ? ያዕቆብ 5፡-4–6 ፤ ማቴዎስ 7፡-12.**

*“በተከማቸው ሀብት ሁሉ እግዚአብሔር አለበት ማለት አይደለም። እንዲያውም ሰይጣን ከእግዚአብሔር ይልቅ ገንዘብ በማከማቸት ብዙ ነገር ያደርጋል። ከተከማቸው ሀብት መካከል አብዛኛው ሊገኝ የቻለው የሰራተኞችን ደመወዝ በመጨቆን ነው። በተፈጥሮው ስግብግብ የሆነው ሀብታሙ ሰው የሰራተኛውን ዋጋ እንዳይነሳ አድርጎ በማድቀቅ እንዲሁም አጋጣሚውን ተጠቅሞ ግለሰቦችን በልጦ የበላይነቱን በመውሰድ በእሳት እንደሚበላ እንዲሁ ስጋውን የሚበላውን ሀብት ያከማቻል።*

*“በአንዳንዶች ዘንድ ጥብቅ ሐቀኝነትና የተከበረ መንገድ እየተተገበረ አይደለም። እንደነዚህ ያሉት ከዚህ የተለየውን መንገድ መከተልና ጊዜውን ለመዋጀት በፍጥነት ሊሰሩ ይገባል። ብዙዎቹ ሰንበት ጠባቂዎች እዚህ ላይ ይሰታሉ። በድሀ ወንድሞቻቸው ላይ እንኳ ያገኙትን አጋጣሚ ይጠቀሙባቸዋል ፤ እነዚህ ወንድሞቻቸው ገንዘብ በማጣት በሀፍረት ተሳቀው፣ በእጦትም ተጨንቀው ሳሉ፣ እነርሱ ግን አንድ እቃ (ንብረት) ሊያወጣ ከሚችለው ትክክለኛ ዋጋው የበለጠ ይጭኑባቸዋል። እነርሱ ለመክፈል ከሚችሉት የበለጠ ይጠይቋቸዋል። እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያውቃቸዋል። እያንዳንዱ የራስ ወዳድነት ተግባር፣ እያንዳንዱ በስግብግብነት ዋጋ አንገሮ የማስከፈል ተግባር የዘራውን የራሱን ዋጋ ያጭዳል።*

*“አንድ ወንድም ያለበትን የችግር ሁኔታ አለማሰብ ጭካኔና መጥፎ ተግባር መሆኑን ተመልክቻለሁ። በጭንቀት ከተወጠረ፣ ድኃም ከሆነ፣ ሆኖም የተቻለውን ሁሉ እያደረገ ከሆነ፣ የገንዘብ ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል ፤ እንዲያውም ከሀብታሞች የሚገዛቸው እቃዎች ላይ ሙሉ ዋጋ ሊተመንበት አይገባም ፤ ነገር ግን ለእርሱ ልባቸው በርህራሄ ሊሞላ (አንጀታቸው ሊንሰፈሰፍለት) ይገባል። እግዚአብሔር እንዲህ አይነቱን የደግነት ተግባር እውቅና ይሰጠዋል ፤ አድራጊውም የተዘጋጀለትን ሽልማት አያጣም። ዳሩ ግን በብዙዎቹ ሰንበት ጠባቂዎች ላይ ጥብቅና የስስታምነት ድርጊታቸው ላይ በጣም አስፈሪ መዝገብ (ሂሳብ) ለምስክር ይቀምባቸዋል።”*—Testimonies for the Church, vol. 1, pp. 175, 176

**ለ. በጥንት ጊዜያት አማኞች ያላቸውን ገንዘብ እንዴት ነበር በነጻ ይካፈሉ የነበሩት? 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡-1፣ 2**

*“እውነትን ከልባቸው በማዳመጥ የተቀበሉ በጣም ጥቂት ምእመናን ወደነበሩበት ጊዜ ተጠቁሜ ነበር። እነርሱ የዚህ ዓለም ንብረት ያን ያህል አልነበራቸውም። ዓላማው (ወንጌሉ) የሚያስፈልገው ነገር በጥቂቶች መካከል ተከፋፍሎ ነበር። በዚህም ሀብታቸው በነፃነት በልግስና ለጌታ ለመስጠት፣ እውነትንም ለማሳተም፣ ካልሆነም በሌላ መንገድ የጌታን ዓላማ እንዲስፋፋ ለማድረግ ቤቶቻቸውንና መሬቶቻቸውን መሸጥና እንደ መጠለያ ሊገለገሉበት የሚችሉትን ረከስ ያለ ዋጋ ያላቸውን ቤቶች መግዛት ለአንዳንዶች አስፈላጊ ሆኖ ነበር። ራሳቸውን የሰውትን እነዚህን አማኞች ስመለከት፣ ለዓላማው ጥቅም (መስፋፋት) ሲሉ ማጣትንና ችግርን ችለው ማለፋቸውን ተመልክቻለሁ። መልዓክ በጎናቸው ቆሞ፣ ወደላይ ወደሰማይ በማመላከት ፡- ‘እናንተ በሰማይ ግምጃቤት (ቦርሳ) አላችሁ ! ሊያረጅ የማይችል የገንዘብ ካዝና (ቦርሳ) በሰማይ አላችሁ ! እስከመጨረሻ ፀንታችሁ ቆሙ፣ ሽልማታችሁም ታላቅ ይሆናል። ’ ”*—Ibid., p. 176

## 5. ለዛሬ አስፈላጊ የሆነው መልካም ባህርይ

### ሀ. ባህርያችንን ለማዳበር ትዕግስት በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምድን ነው ? ያዕቆብ 5:7.

"'ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እየታገዘ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል' [ያዕቀብ 5፡-7]። ስለዚህ የእግዚአብሔር በሕይወቱ ለፍሬ እንዲደርስ ክርስቲያን መታገስና መጽናት አለበት። በተደጋጋሚ ሲሆን እንደሚታየው የመንፈስ ቅዱስን ፀጋ ለመቀበል ስንፀልይ እግዚአብሔር ደግሞ እነዚህን ፍሬዎች ለማፍራት በምንችልበት ሁኔታ ውስጥ እኛን በማስገባት ለፀሎታችን ምላሽ በመስጠት ይሰራል። እኛ ግን የእርሱን ዓላማና ሃሳብ ስለማናስተውል ግራ በመጋባት ተስፋ እንቆርጣለን። ነገር ግን ማንም ቢሆን በማደግና ፍሬ በማፍራት ውስጥ ካላለፈ በስተቀር እነዚህን የፀጋ (ስጦታዎች) ማዳበር አይችልም። ስለዚህ የእኛ ድርሻ እግዚአብሔርን ቃል መቀበልና በእርሱም መጽናት ነው ፤ ሕወይታችንን እንዲቆጣጠር ስንፈቅድለት የቃሉ ዓላማ በእኛ ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል።

"'የሚወደኝ ቢኖር' አለ ክርስቶስ ሲናገር 'ቃሌን ይጠብቃል ፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን' ዮሐንስ 14:23። ኃይልን በሚሰጠን ሁሉን ቻይ ከሆነው ጋር ህያው ግንኙነት ሲኖረን ፍፁም፣ የበረታና የላቀ አሳብ (አዕምሮ) የእኛ ስብዕና ይሆናል። በመለኮት ሕይወት ስንሆን ለየሱስ ክርስቶስ እንማረካለን። በመሆኑም ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ከዚህ በፊት የኖርነውን ተራና የራስወዳድነት ኑሮ አንኖረውም፡ ፡ የእርሱ ባህርይ በእኛ ተፈጥሮ ውስጥ እንደገና ይፈጠራል (ይወለዳል)። ይህ ሲሆን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እናፈራለን —'አንዱ መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ' ይሆናል።"—Christ's Object Lessons, p. 61 (አማርኛው ገጽ 29)

### ለ. በምኖርባት በዚች ፕላኔት በክፉው መባባስ (ማየል) የተነሳ ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ ሲፈትነን ሳለ፣ መታመንና ትግስት በጣም ጠቃሚ የሆነው ለምድን ነው ? ያዕቆብ 5፡- 8 ፤ ሉቃስ 21፡- 19

"ዓለም የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍ ደፋር ሆናለች። ከረጅም ትዕግሥቱ የተነሳ ሰዎች የእግዚአብሄርን ሥልጣን ረግጠዋል። 'እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል? በልዑልም ዘንድ እውቀት አለን? (መዝሙረ ዳዊት 73:11) በማለት የእርሱ ርስት (ቅርስ) በሆኑት ላይ ግፍና ጭካኔን በማሳየት አንዱ አንዱን አበርትተዋል። ነገር ግን ማለፍ የማይችሉበት መስመር አለ። የተወሰነው ገደብ ላይ የሚደርሱበት ጊዜ ቅርብ ነው። አሁን እንኳን የእግዚአብሔርን ትግስት፣ የጸጋውን ገደብ፣ የምሕረቱን ወሰን ሊያልፉ ምንም አልቀራቸውም። ክብሩን በግልጽ ያሳይ ዘንድ፣ ሕዝቡንም ያድንና የዓመፅንም ጎርፍ ይገታ ዘንድ ጌታ ጣልቃ ይገባል።"—Christ's Object Lessons, p. 177, 178

## 5. ሊያበረታን የሚችል ምሳሌ

## ሀ. በቤተክርስቲያን አጠቃላይ አባላት በአብዛኛው የምናተኩረው በምን ላይ ነው—ነገር ግን በዚህ ምትክ ምንድን ነው በልቦናችን መያዝ ያለብን? ዘለዋዊያን 19፡-18 ፤ ያዕቆብ 5፡-9፣ 10.

*“ከአዳም ልጆች መካከል የመጀመሪያ ክርስቲያን የነበረው አቤል የሰማዕትነት ሞት ሞተ። ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር ተራመደ ፤ ዓለም ግን አላወቀውም። ኖህ እንደ አክራሪና አስደንጋጭ ተቀጥሮ መሳቂያ መሳለቂያ ሆነ። ‘ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በውኅኒ ተፈተኑ’ ፤ ‘ሌሎችም ነፃ ሳይወጡ የሚበልጠውን ትንሳኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ’* [*ዕብራዊያን* 11፡- 36፣35]*። በእያንዳንዱ ዘመን የተመረጡ የእግዚአብሔር መልዕክተኞች መዘባበቻ ሆነዋል፣ ተሳደዋል፣ ተጨፍጭፈዋልም ፤ ሆኖም በስቃያቸውና በመከራቸው የእግዚአብሔር እውቀት ወደ ውጭ ሀገራት ተዳርሷል። የእርሱ ጠላቶች ስለ እውነት እንጂ በእውነት ላይ አንዳች ነገር ማድረግ እንደማይችሉ በማወቅ እያንዳንዱ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ወደ ሰራዊቱ ተመልምሎ* (*ምልምል ወታደር ሆኖ*) *መግባት እና ተመሳሳዩን ሥራ ወደ ፊት ማስፋፋት ይኖርበታል። እውነት ምንም እንኳ ጥላቻ ቢለጠፍበትም፣ በይፋ ወደ አደባባይ* (*ወደ ሰዎች ፊት ቀርቦ*) *የምርመራና የውይይት ርዕሰ ጉዳይ እንዲሆን እግዚአብሔር ወስኗል። የሰዎች አዕምሮ መናወጥና መነሳሳት አለበት ፤ እያንዳንዱ ውዝግብ* (*ጥል*)*፣ እያንዳንዱ የስም ማጥፋት ነቀፋ ፣ የህሊና ነፃነትን ለመገደብ የሚደረግ እያንዳንዱ ጥረት ሁሉ፣ በሌላ በምንም መንገድ ሳይነቃ ተኝቶ ይቀር የነበረውን አዕምሮ የሚያነቃበት የእግዚአብሔር መሳሪያዎች ናቸው።*

*“ይህ ውጤት በእግዚአብሔር መልዕክተኞች ታሪክ ውስጥ መታየት የቻለው ምን ያህል ነው ! እጅግ የከበረውና በአንደበተ ርቱዕነት የታወቀው እስጢፋኖስ በአይሁድ መማክርት ሸንጎ አነሳሽነት በድንጋይ ተወግሮ በሞተ ጊዜ በወንጌሉ ዓላማ ላይ አንዳች ኪሳራ አልደረሰም። ፊቱን በክብር የሞላው የሰማይ ብርሐን፣ በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ሲፀልይ የተነፈሰው መለኮታዊ ርህራሔ፣ በጎን ቆሞ ለነበረው አክራሪና አሳዳጅ ፈሪሳዊ ለነበረው ለሳዑል በስቶ እንደሚወጋ ስለታም ቀስት ነበረ ፤ አሳዳጁ ፈሪሳዊ የክርስቶስን ስም በአህዛብ፣ በነገሥታት እንዲሁም በእስራኤል ልጆች ፊት ለመሸከም የተመረጠ እቃ ሆነ።”*—Thoughts From the Mount of Blessing, pp. 33, 34.

**አርብ** **ታህሳስ 11**

### የግል ክለሳና የመወያያ ጥያቄዎች

1. *የራሴ ገንዘብ ስላለው ዋጋ ምንድን ነው መገንዘብ ያለብኝ* ?
2. *በያዕቆብ* 5፡-1 *ላይ ክርስቶስ ያቀረበው መፈተኛ ማለት ምን ማለት ነው*?
3. *በገንዘብ የሚከናወን ግዥና ሽያጭን በተመለከተ በምን ደካማ ጎን ነው ጥፋተኛ ልሆን የምችለው*?
4. *በመጨረሻ ትግስት መልካም ባህርይ ሆኖ በጌታ ሕዝቦች መካከል ማብራት የሚችለው እንዴት ነው* ?
5. *በታሪክ ዘመናት ሁሉ ክርስቲያን ሰማዕታት በትኩረታቸው ላይ ማነጣጠር የቻሉት እንዴት ነው* ?

**13ኛ ትምህርት** **ሰንበት፣ ታህሳስ 19፣ 2017**

*በኃይማኖት እስከመጨረሻ መጽናት*

**መታሰቢያ ጥቅስ፡- "እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ ፤ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይፀልይ። የጻድቅ ሰው ፀሎት በሥራዋ እጅግ ታደርጋለች" (ያዕቆብ 5፡-16)።**

"*ትሁትና ትጋት የሞላበት ፀሎት፣ ነፍስን ከሞት ያድናል ፤ መናዘዝና የህይወት መመለስ (ወደመጀመሪያው መመለስ) የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል።* "— The Review and Herald, December 16, 1902.

**ለጥናት የተመረጠው መጽሐፍ፡- The Ministry of Healing, pp. 225–233; Testimonies for the Church, vol. 3, pp. 271–293.**

እሁድ **ታህሳስ 13**

**1. ተስፋ**

**ሀ. በየትኛው የባህርይ መገለጫ ነው ኢዮብ በተለየ ሁኔታ የታወቀው—ይህስ ስለ እግዚአብሔር ምን ይነግረናል ? (ያዕቆብ 5፡- 11)**

"*የአስቸጋሪውን ሰው የኃጢአት ኑዛዜ ለመስማትና ንስኃውን ለመቀበል ጌታ በማይታክት ፍቅር እየተጠባበቀ ነው። እናት ከምትወደው ልጇ ለእናትነቷ የእውቅና ፈገግታ ለማየት እንደምትናፍቅ ሁሉ እርሱም ለውለታው የአመስጋኝነት መልስን ለማግኘት ከእኛ ይጠብቃል። ለእኛ ምን ያህል ልቡ እንደሚራራና ሰፍሰፍ እንደሚል እንናስተውል ዘንድ ይናፍቃል። በፈተናዎቻችን የእርሱን ርህራሄ፣ በድካማችን ጥንካሬውን፣ በባዶነታችን ሙሉነቱን እንወስድ ዘንድ ይጋብዘናል። ወደ እርሱ መጥቶ በሐዘን የተመለሰ አንድ ሰው እንኳ የለም።*

"*ወደ እርሱ ተመለከቱ ገጽታቸውም አበራ ፤ ፊታቸውም በሀፍረት አልተከደነም።' "ለጌታ በሚስጥር መሻታቸውን በመንገር እና እርዳታውንም በመማፀን፣ እግዚአብሔርን የፈለጉ ሁሉ፣ ተማጽኗቸው ከንቱ ሆኖ አልቀረም፡ ፡*"—Thoughts From the Mount of Blessing, pp. 84, 85.

**ለ. ያዕቆብ ታማኝነትን (እውነተኛነትን) አስመልክቶ የክርስቶስ ቃላት ያስተጋባው እንዴት ነው ? ያዕቆብ 5:12 ፤ ማቴዎስ 5:37.**

"*ክርስቲያናት የሚያደርጉት እያንዳንዱ ነገር ልክ እንደ ፀሐይ ብርሃን የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት።*"—Ibid., p. 68.

## 2. እውነተኛ እምነት ከድፍረት ጋር ሲነፃፀር (FAITH VS. PRESUMPTION)

### ሀ. በበሽታ ብንሰቃይ፣ እንዴትና ለምንድን ነው ወደ ህይወት ሰጪያችን ለመምጣት የምንደፋፈረው? ያዕቆብ 5:13–15 ፤ መዝሙር 103:1–3.

*“ እግዚአብሔር በሽተኛውን ወደ ሙሉ ጤንነት ለመመለስ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ቃላት በዘማሪው አማካይነት በተናገረበት ጊዜ ፈቃደኛ የሆነውን ያህል አሁንም ፈቃደኛ ነው። እንዲሁም ክርስቶስ ያኔ በምድራዊ የአገልግሎቱ ጊዜ እንደነበረው ዛሬም እንደዚያው ሩህሩህ ሃኪም ነው። በእርሱ ዘንድ ማንኛውንም ጉዳት ወደ ሙሉ ጤንነት መመለስ የሚችል ለእያንዳንዱ በሽታ የተዘጋጀ ፈዋሽ መድሃኒት (ቅባት) አለው። በዚህ ጊዜ የሚገኙ ደቀመዛሙርት፣ በጥንት ጊዜ የነበሩ ደቀመዛሙርት እንደፀለዩት እነርሱም ለበሽተኞች መፀለይ ይኖርባቸዋል። ከዚያም ፈውስ ይከተላል ፤ ምክንያቱም ‘የእምነት ፀሎት ድውዩን (በሽተኛውን) ያድናልና’። እኛ የእግዚአብሔርን ተስፋ ይገባናል ብለን መጠየቅ የምንችልበት፣ የተረጋገጠ የእምነት ማረጋገጫ፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አለን።። ‘እጃቸውንም በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ’ (ማርቆስ 16:18) በማለት ጌታ የገባው የተስፋ ቃል በሐዋሪያት ጊዜያት እንደነበረው ዛሬም የታመነ ነው።”*—The Ministry of Healing, p. 226.

### ለ. ጤንነትን ስንሻ ከምን ሚዛናዊነት ነው መጠንቀቅ ያለብን? መዝሙር 66:18.

*“እኛ [ለጌታ] ምህረት የተገባን አይደለንም ፤ ነገር ግን ራሳችንን ለእርሱ ስንሰጥ እርሱ ይቀበለናል። እርሱን በሚከተሉት በእነርሱና በእነርሱ በኩል ሥራውን ይሰራል።*

*“ነገር ግን ቃሉን በመታዘዝ ስንኖር ብቻ ነው ተስፋዎቹ እንዲፈፀሙልን መጠየቅ የምንችለው። . . . ለእርሱ የምንሰጠው ታዛዥነት በከፊል፣ በሁለት ልብ ከሆነ፣ ተስፋዎቹ ሊፈፀሙልን አይችሉም።”*—Ibid., p. 227.

*“ክርስቶስ ይሰራበት የነበረው መንገድ ቃሉን መስበክና በተዓምራት ድውያንን መፈወስ ነበር። ነገር ግን አሁን በዚህ መንገድ መስራት እንደማንችል መመሪያ ተሰጥቶኛል ፤ ምክንያቱም ሰይጣን ተዓምትራን በመስራት ኃይሉን ይጠቀማልና። የእግዚአብሔር አገልጋዮች አሁን በተዓምራት አማካይነት መሥራት አይችሉም ፤ ምክንያቱም መለኮታዊ ናቸው በማለት አስመሳይ የሆኑ የፈውስ ተዓምራቶች ይፈፀማሉና።*

*“በዚህ ምክንያት ሕዝቡ አካላዊ የፈውስ ስራን ከቃሉ ትምህርት ጋር አጣምረው የሚሰሩበትን መንገድ ጌታ ቀይሷል። የጤና ማገገሚያ የህክምና ጣቢያዎች* (Sanitariums) *መገንባትና በእነዚህ ተቋማት እውነተኛውን የህክምና ሚሽነሪ ስራን ወደጊት እንዲገፋ የሚያስችሉ ሰራተኞች ሊመደቡ ይገባል። ይህም ሲሆን ለህክምና ወደ እነዚህ የጤና ተቋማቱ (ጣቢያዎች) በሚመጡ ህሙማን ዙሪያ አስተማማኝ ተጽዕኖ ማሳደር ይቻላል።*

*“የወንጌል ህክምና አገልግሎት ለብዙ ሰዎች ይከናወን ዘንድ ጌታ ያዘጋጀው አቅርቦት ይህ ነው።”*—Medical Ministry, p. 14.

## 3. ሁለት የተለያዩ የድፍረት አይነቶች

### ሀ. በአሳዛኝ ሁኔታ ቸላ ተብሎ ወደ ጎን የተገፈተረውን በጣም አስፈላጊውን ፈውስ ይጥቀሱ፡፡ ያዕ 5:16.

" *የኃጢአት ኑዛዜ ማድረግ ክብራችንን ያዋርዳል፣ በባልንጀሮቻቸውም መካከል ያላቸውን ተጽዕኖ ያዳክማል ብለው የሚያስቡ ሰዎች በጣም በጣም ተሳስተዋል። ከዚህ የተሳሳተ አስተሳሰብ ጋር በመጣበቅ፣ ስህተት መስራታቸውን ማየት እንኳ ቢችሉም፣ ነገር ግን ብዙዎቹ ከመናዘዝ ተደናቅፈው ይቀራሉ ፤ ይቁንም በሌሎች ላይ ያደረሱትን በደል እንዳላዩ ሁነው በማለፍ፣ የራሳቸውን ህይወት ክፉኛ መራራ ያደርጉታል ፤ በሌሎችም ሕይወት ላይ መጥፎ የጥላ ግርዶሽ ያሳርፉበታል። ኃጢአታችሁን መናዘዛችሁ ክብራችሁን አያወርደውም፡ ፡ ይህን የውሸት ክብር አሽቀንጥራችሁ ወዲያ ጣሉት። በአለቱ ወድቃችሁ ተሰበሩ ፤ ክርስቶስ ደግሞ እውነተኛውንና ሰማያዊውን ክብር ይሰጣችኋል። የተሰፋ ቃሉ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችል ዘንድ ኩራት፣ የራስ ክብር፣ ወይም የራስ ጽድቅ ኃጢአቱን ከመናዘዝ ማንንም ቢሆን አይከልክለው። 'ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምህረት ያገኛል'* (ምሳሌ 28:13)። *አንዳች ነገር ከእግዚአብሔር አትሰውሩ ፤ የሰራችሁትንም ጥፋት* (በደል) *ለወንድሞቻችሁ መናዘዛችሁን ቸላ አትበሉ። 'እርስ በርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ ፤ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይፀልይ'* (ያዕቆብ 5:16)። *መዝገቡ በመጨረሻው ቀን ኃጢአተኛውን ይጋፈጠው ዘንድ ብዙ ኃጢአት ንስኃ ሳይገባበት ቸላ ተብሎ ቀርቷል ፤ የሚያስተሰረየው መስዋዕት ስለ አንተ* (ስለ አንቺ) *እየተማፀነ ባለበት አሁን፣ ኃጢአቶቻችሁን ፊት ለፊት ተጋፍጣችሁ ብትናዘዙትና ጨርሶም ብታስወግዱት በጣም የተሻለ ነው። በዚህ ርዕስ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመማር አትውደቁ። የነፍሳችሁ ጤንነት እንዲሁም የሌሎችም ድነት* (መዳን) *በዚህ ነጥብ ላይ በምትከተሉት መንገድ ላይ የተማከለ ነው።*"—Selected Messages, bk. 1, pp. 326, 327.

### ለ. ስለ ህዝቡ መንፈሳዊ ክህደት በጣም ባሰበ ጊዜ፣ ኤልያስ ምን እርምጃ ነበር መውሰድ የቻለው —እግዚአብሔርስ የጠበቀው እንዴት ነው? 1ኛ ነገሥት 17፡-1–3.

" *በአንድ ወቅት ተወዳጅ የነበሩ ሕዝቦቹን ከክፉ መንገዳቸው ይገታቸው ዘንድ፣ ከሰማይ ምን ያህል እንደራቁ በእውነተኛው ብርሃን ማየት እንዲችሉ ካስፈለገም በፍርድ እንዲጎኛቸው ኤልያስ በንፍስ ጭንቀት* (ልቡን ጭንቀት ከብዶት) *ፀለየ። በክፉ የኃጢአት ተግባራቸው መመለስ የማይችሉበት ርቀት በመድረስ እግዚአብሔር ፈጽሞ ያጠፋቸው ዘንድ ቁጣው እንዲቀጣጠል ከማድረጋቸው በፊት ንስሐ ሲገቡ ለማየት ነፍሱ አጥብቃ ናፈቀች።*. . . .

"*የሰማይን የፍርድ መልዕክት ለአክዓብ የማድረስ ተልዕኮ ለኤልያስ ተሰጠው*. .። *ከቤተመንግስቱ እንደደረሰ መምጣቱ እንዲነገርለት ወይም በይፋ ግባ እስኪባል አልጠበቀም። በዚያን ጊዜ የነበሩ ነብያት የሚለብሱትን ተራ ልብስ ለብሶ፣ ዘበኞቹ ልብ ሳይሉት አልፎ በደነገጠው ንጉሥ ፊት በድንገት ቆመ፡ ፡* "—Prophets and Kings, pp. 120, 121.

## 4. ከኤልያስ መማር

### ሀ. ከሐዲ የሆነውን የገዛ ህዝቡን ለመማነቃቃት ወደ እግዚአብሔር ያደረገው የኤልያስ ጸሎት ለእኛ ምሳሌ ሆኖ የተሰጠን ለምንድን ነው? ያዕቆብ 5:17

*"ተማጽዕኖ፣ ምክርና ማስጠንቀቂያ በተደጋጋሚ ቢቀርብም እስራኤልን ወደ ንስሐ መመለስ አልቻለም። እግዚአብሔር በፍርድ አማካይነት መናገር የግድ የሚልበት ጊዜ ደረሰ። የበዓል አምላኪዎች የሰማይ ሐብት፣ ዝናብና ጠል ሁሉ የሚወርዱት ከጅሆባ ሳይሆን ነገር ግን ተፈጥሮን በሚቆጣጠሩ ኃይላት አማካይነት ነው ብለው ያምኑ እንደመሆናቸው፣ እንዲሁም ምድር በሐብቷ የበለፀገችውና የተትረፈረፈች ምርቷን በገፍ እየለገሰች ያለችው በፀሐይ የመፍጠር ኃይሏ ነው ብለው ሸንጣቸውን ገትረው እስከሞገቱ ድረስ፣ የእግዚአብሐር እርግማን በተበከለችው ምድር ላይ ክፉኛ ሊወርድ ነበር። ከሐዲዎቹ የእስራኤል ነገዶች ለጊዜያዊ በረከት ሲሉ በበዓል ኃይል መታመናቸው ምን ያህል ከንቱ እና ገልቱ (ሞኝነት) እንደሆነ ማየት ነበረባቸው። ተፀጽተው ወደ እግዚአብሔር ካልተመለሱና የበረከት ሁሉ ምንጭ እርሱ መሆኑን ካላመኑ በምድር ላይ ጠልም ሆነ ዝናብ አይወርድም።"*—Prophets and Kings, p. 120.

### ለ. እስራኤላዊያን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ታማኝነት ካደሱ በኋላ፣ የኤልያስ ፀሎት በድጋሚ አርዓያ ሊሆነን የሚችለው እንዴት ነው? ያዕቆብ 5:18፤ 1ኛ ነገሥት 18:39–45.

*"[ኤልያስ] ስድስት ጊዜ በታላቅ ትጋት ፀለየ ፤ ሆኖም ተማጽዕኖው ተቀባይነት ስለማግኘቱ የታየ ምልክት አልነበረም ፤ ነገር ግን ወደ ፀጋው ዙፋን ተማጽዕኖውን በጠንካራ እምነት ማቅረቡን ቀጠለ። ተስፋ በመቁረጥ ፀሎቱን በስድስተኛው ዙር ቢያቆም ኖሮ፣ ተማጽዕኖው ባልተመሰለት ነበር። እርሱ ግን መልሱ እስኪመጣለት ድረስ ፀንቶ ቀጠለ። ለምናቀርበው ተማጽዕኖ ጆሮዎቹ በፍፁም የማይዘጉ አምላክ አለን ፤ እናም የቃሉን እውነታነት ማረጋገጥ (መፈተን) ከቻልን፣ እርሱ እምነታችንን ያከብረዋል። ፍላጎቶቻችንን ከእርሱ ፍላጎቶች ጋር ድርና ማግ አድርገን እናስተሳስራቸው ዘንድ ይሻል ፤ ያኔ ያለ አንዳች ስጋት ይባርከናል ፤ ምክንያቱም በረከቶቹ የእኛ በሚሆኑበት ጊዜ ክብሩን ለራሳችን መውሰድን ትተን ውዳሴን ሁሉ ለእርሱ የምናቀርብ እንሆናለንና። እግዚአብሔር በጸሎታችን ስሙን በጠራንበት በመጀመሪያ ሁልጊዜ አይመልስልንም ፤ ምክንያቱም ይህን ቢያደርግ እርሱ በእኛ ላይ አትረፍርፎ የቸረንን ባርኮቶችና ጸጋውን እንደ መብት የምንቀጥረው እንሆናለንና። ይህ ከሆነ፣ ያስተናገድነው አንዳች ክፉ ነገር (ክፋት) ይኖር ይሆን ብለን ልባችንን መመርመር ሲገባን፣ ግድየለሾች እንሆናለን ፤ እርዳታው እንደሚያሻንና በእርሱ ላይ መተማመን እንዳለብን መገንዘብ ይሳነናል።*

*"ኤልያስ ክብሩን ለራሱ መውሰድ እንደሌለበት ጨርሶ መገንዘብ ወደሚችልበት ሁኔታ እስኪደርስ ድረስ ራሱን ዝቅ አደረገ። ጌታ ለጸሎት መልስ የሚሰጥበት ቅድመ ሁኔታ ይህ ነው ፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ውዳሴን ለእርሱ እናበረክታለንና።"*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 2, pp. 1034, 1035.

## ሐሙስ ታህሳስ 17

## 5. ክርስቶስን መሳይ ደግነት ማጎልበት (ማስፋፋት)

### ሀ. በጠማማ ሰዎች አማካይነት በወደቀው ዓለም መከፋትና ሐዘን በላያችን ላይ ቢወረድም፣ ያዕቆብ ለእኛ የሚያስተላልፈውን ደብዳቤ (መልእክት) በምን ተማጽዕኖ ነው የዘጋው? ያዕቆብ 5፡ -19፣ 20.

" በስህተት ለወደቁ ሰዎች ምንም ቢሆን ተስፋ አስቀራጭ ምክንያት መሆን የለብህም። በፈሪሳዊ ልበ-ደንዳናነት ወንድምህን ከመጉዳት መቀጠብ አለብህ። ልብን የሚያደማ መራራ አሽሟጣጭነት በአዕምሮና በልብ ውስጥ ብቅ እንዲል መፈቀድ የለበትም። ስትናገር በድምጽህ ውስጥ ትንሽም ቢሆን የንቀት ወይም የማንቋሸሽ ድምጽ መሰማት የለበትም። የራስህን ንግግር የምታደርግም ከሆነ ትንሽም እንኳን የቸልተኝነት፣ የጥርጣሬ ወይም ያለማመን ሁኔታ ካሳየህ የአንድ ነፍስን መጥፋት የሚያረጋግጥ ይሆናል። ምክንያቱም ይህ ወንድም እንደ ታላቁ ወንድሙ (ክርስቶስ) ልብ ዓይነት ርኅራኄ በማሳየት የእርሱን ሰብዓዊ ልቡን የሚነካ ወንድም ነው የሚፈልገው። በመሆኑም ይህን ወንድህን በርህራሄ በተሞላ አጥብቆ በሚጨብጠው እጅና በሹክሹክታ እንጸልይ በሚል ድምጽ እንዲሰማ አድርገው። እግዚአብሔር ለሁለታችሁም የበለፀገ የህይወት ተሞክሮ ይሰጣችኋል፡ ፡ ፀሎት እርስ በእርስ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር እንድንቀራኝ ያደርገናል፡ ፡ ፀሎት የሱስ ከጎናችን እንዲቆም በማድረግ፣ ለደከመውና ለተጨነቀው ነፍስ ዓለምን፣ ሥጋን እና ዲያብሎስን ማሸነፍ የሚችልበት አዲስ ብርታት ይሰጠዋል፡ ፡ ጸሎት የሰይጣንን የጥቃት ኃይል አሽመድምዶ ያባርረዋል።

"አንድ ሰው፣ ከሰብዓዊ ፍጡር ጉድለቶች ዘወር ብሎ፣ ወደ የሱስ የሚመለከት ከሆነ በባህሪይው ላይ ፍፁም መለኮታዊ ለውጥ ይፈጠራል። በልብ ላይ የሚሰራው የክርስቶስ መንፈስ ከራሱ ከየሱስ ምስል ጋር ያስማማዋል። እንግዲያውስ ጥረታችን ሁሉ የሱስን ከፍ ከፍ ለማድረግ ይሁን። የአይምሯችንን አይኖች ሁሉ 'የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ እግዚአብሄር በግ' (ዮሐ 1፡-29) ላይ የሚያነጣጥሩ ይሁኑ። በዚህ ዓይነቱ ላይ ሥራ ስንጠመድ 'ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልስ ሰው ነፍሱን ከሞት ያድነዋል ፤ ብዙ ኃጢአትንም ይሸፍናል' የሚለውን ቃል ልናስታውስ ይገባል (ያዕ 5:20) . . .።


"በእግዚአብሔር ይቅርታ ስህተት ፈፃሚው ፍቅር ወደሆነው ወሰንየለሽ አምላክ ልብ እየቀረበ ይመጣል። መለኮታዊ የርህራሄ ሞገድ ወደ ኃጢአተኛው ነፍስ ያልፍል ፤ ከእርሱም ወደሌሎች እየተላለፈ ይሄዳል። "—Christ's Object Lessons, pp. 250, 251.

## አርብ ታህሳስ 18

### የግል ክለሳና የመያያ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔርን አትረፍርፎ ያበዛልኝን ምህረቱን በህይወቴ ማየት የቻልኩት መቼ ነው
2. የራሴን ጤንነት አስመልክቶ በምን ሁኔታ ነው በመዳፈር ጥፋተኛ ልሆን የምችለው?
3. ኤልያስ ስለ ሕዝቡ የፀለው ፀሎት እንዴት (በምን ሁኔታ) ነበር ሊመለስለት የቻለው ?
4. ኤልያስ ዝናቡ ይመለስ ዘንድ ኤልያስ ብዙ ጊዜ መፀለይ ያስፈለገው ለምንድን ነው ?
5. ለማን ነው ብዙ የርህራሄ አመለካከት ሊኖረኝ የሚገባው ለምን?

# የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታዎች




የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ በረድንግ፣ ፔንሰልቬንያ፣ ዩኤስኤ ውስጥ ለሚገኝ የጸሎት ቤት መሥሪያ ይውላል




የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ ለጄነራል ኮንፈራንስ ሥነ ጽሑፍ ክፍል




የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ ለኮሎምቢያ ዩኒየን ዋና መሥሪያ ቤት ይውላል